# ከአስቸጋሪ ሰው ጋር



## አብሮ መኖር፣ መጎራበት፣ መሥራት፣ ማምለክ... ይቻላል?

ዶክተር መለሰ ወጉ

# ከአስቸጋሪ ሰው ጋር



አብሮ መኖር፣ መጎራበት፣ መሥራት፣ ማምለክ... ይቻላል?

ዶክተር መለሰ ወጉ

# ከእስቶች ጋሪ ሰው ጋር

## መኖር፣ መጎራብት፣ መሥራት፣ ማምለክ... ይቻላል?

ዶክተር መለሰ ወጉ

# መግቢያ

አስቸጋሪ ሰዎች የሌሉበት ሥፍራ የለም። በአንድ ጣራ ሥር አብረውን የሚኖሩ፣ አንድ መሥሪያ ቤት አብረውን የሚሠሩ፣ በአንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አብረውን የሚያመልኩና የሚያገለግሉ፣ እንዲሁም የተጎራበቱን ሊሆኑ ይችላሉ። እነዚህ አስቸጋሪ ሰዎች ተለይተው የሚታወቁበት የራሳቸው የሆነ የተለያየ ባሕሪ አላቸው። ከቁጥጥር ያለፈ ቁጣ፤ ጎጂ የሆነ ምላስ ያላቸው ናቸው። በቀላሉ የመከፋትና የማዘን ባሕሪ ይታይባቸዋል። የራሳቸውን ማንነት የሚጠራጠሩ፤ ነገር ሁሉ ተወላግዶ የሚገባቸውና የሚታያቸው ናቸው። ለሚሰሙት ንግግር ሁሉ ልዩ ትርጉም የሚሰጡ፣ "የስሜት ኸርዋኸርዌ" (emotional roller coaster) የሚታይባቸው፣ አሁን ስቀውና ተጫውተው እንደሆነ ባልታወቀ ምክንያት ወዲያው የሚያለቅሱና የሚያኮርፉ ናቸው። ዛሬ ያመሰገኑትና ያደነቁትን ሰው፤ በሌላ ጊዜ የሚነቅፉና የሚተቹ፣ አሁን በጣም የወደዱትን፤ ትንሽ ቆይተው በጣም የሚጠሉ ናቸው። ስለ ራሳቸው ፍላጎትና ፈቃድ እንጂ ስለ ሌላው ሰው ፍላጎት ፍጹም ግድ የላቸውም። ተጠራጣሪዎች፣ ሰጉዎች፣ እንዲሁም በየጥቃቅኑ ምክንያት ብዙ ጊዜ የሚነጫነጩ፣ የሌላው ሰው ጉዳት የማይሰማቸውና የማይቆረቁራቸው፣ "የእኔ ፍላጎትና ፈቃድ ብቻ ይሁን" የሚሉ፣ "እሺ!" እንጂ "እምቢ!" መባልን ፈጽሞ መቀበል የማይሆንላቸው ናቸው። አብሮአቸው የሚኖረው ሰው፤ በመካከላቸው ግጭት እንዳይፈጠር በመፍራት የሚይዛቸው ሁልጊዜ እንደሚሰበር ዕንቁላል በጥንቃቄ ነው። ምንም ያህል ቢጠነቀቅ፤ ምክንያት ፈልገው ግጭት መፍጠራቸው የማይቀር ነው።

የመሠረታችሁት ግንኙነት (relationship) ከላይ የገለጽነውን ዓይነት ባሕሪ ከሚታይባቸው ሰዎች ጋር ከሆነ፤ በሰላም መኖር ቢያቅታችሁ *"የችግሩ ምክንያት እኔ እሆን?"* ብላችሁ ግራ በመጋባት ራሳችሁን አታስጨንቁ። የመሠረታችሁት ግንኙነት አስቸጋሪ ከሆነ ሰው ጋር እንደሆነ እወቁ። በመካከላችሁ ተደጋጋሚ የሆነ ግጭት ሲፈጠር፤ በሁኔታው ግራ በመጋባትና በመጨነቅ፤ "ይህን ሰው ከሕይወቴ ፍጹም ላስወግደው ወይም ልሸሽ ስለማልችል፤ አብሬው በሰላም መኖር የምችለው እንዴት ነው?" ብላችሁ መጠየቃችሁ አይቀርም። አስቸጋሪ ከሆነባችሁ ሰው ጋር መኖር የምትችሉት፤ የአስቸጋሪውን ሰው ጠባይ በመለወጥ መሰሏችሁ ብዙ ጥረት አድርጋችሁ ልትለውጡት እንዳልቻላችሁ ራሳችሁ ምስክሮች ናችሁ። አስቸጋሪውን ሰው መለወጥ ካልቻላችሁ፤ ሌላ ያላችሁ አማራጭ፤ ስለ አስቸጋሪው ሰው ያላችሁን የግል አቋምና አስተሳሰብ መለወጥ ብቻ ነው። *"የአስቸጋሪውን ሰው ጠባይ መለወጥ ካልቻ*

ልኩ፤ እንግዲያውስ ስለ አስቸጋሪው ሰው ያለኝን አቋምና አስተሳሰብ መለወጥ
የምችለው እንዴት ነው?" ብላችሁ መጠየቃችሁ አይቀርም። የዚህም መጽ
ሐፍ ዓላማ ይህንኑ ማድረግ የምትችሉበትን አንዳንድ መመሪያዎችንና አሳቦ
ችን ለመስጠት ስለሆነ፤ ጊዜ ወስዳችሁ በጥንቃቄ አንብቡት።

እግዚአብሔር የሰጣችሁን የመምረጥና የመፍቀድ ነጻነታችሁንና እንዲ
ሁም መብታችሁን ገፍፎ በራሱ ቁጥጥር ሥር ሊያውላችሁ የሚሞክር፤ "አስቸ
ጋሪ ሆነብን" በምትሉት ሰው ምክንያት በሚፈጠረው ተደጋጋሚ ግጭት ተማ
ርራችሁ፤ ከመኖር ይልቅ ሞትን እንድትመርጡ አድርጓችሁ ይሆን? ልታስወ
ግዱት ወይም ልትሸሹት የማትችሉት አስቸጋሪ የሆነ ሰው በሕይወታችሁ
ይኖር ይሆን? ከላይ በገለጽነው ዓይነት ኑሮአችሁን መራራና ከባድ ያደረገባችሁ
አስቸጋሪ የሆነ ሰው በሕይወታችሁ ካለ፤ ይህ መጽሐፍ ታስቦ የተዘጋጀው
ለእናንተ ነውና በጥንቃቄ አንብባችሁ ተጠቀሙበት። እዚህ ላይ በቅድሚያ
መግለጽ የምንወደው ነገር ቢኖር፤ "ይህን መጽሐፍ ካነበባችሁ በኋላ፤ አስቸጋ
ሪው ሰው ከሚፈጥርባችሁ ችግር ሁሉ ፍጹም ነጻ ሆናችሁ መኖር ትችላላችሁ"
ብለን ለመናገር የማንደፍር መሆናችንን ነው። የአስቸጋሪውን ሰው ክፉ ባሕሪ
ተቋቁማችሁ ለመኖር፤ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የሰጠናቸውን አንዳንድ መመሪ
ያዎች በተግባር ላይ ብታውሉም የጠበቃችሁትን ዓይነት ውጤት ወዲያው
ማየት አትችሉም ይሆናል። የአስቸጋሪውን ሰው ጎጂ ባሕሪ ተቋቁሞ ወይም
ችሎ ለመኖር በቂ ልምምድ፤ ድፍረትና ቆራጥነት ስለሚጠይቅ፤ የጠበቃችሁ
ትን ዓይነት ውጤት ቶሎ ባታዩም ተስፋ አትቁረጡ። ይህ መጽሐፍ ከአስቸጋሪ
ሰዎች ጋር ለሚኖሩት ጠቃሚ የሆነ ምክርና አሳብ የያዘ ስለሆነ፤ እንደሚገባው
አንብባችሁ በውስጡ የያዘውን መመሪያ በተግባር ላይ ማዋል ከቻላችሁ፤ አስ
ቸጋሪው ሰው ባይለወጥም፤ እናንተ ግን ራሳችሁን ከጉዳት መጠበቅ ትችላላ
ችሁ። ሁኔታዎችን አጨልማችሁ በማየት ዓለም በላያችሁ ላይ የተደፋ ባይመ
ስላችሁ፤ ያጋጠማችሁን ክፉ ነገር ለበጎ ለመጠቀም ራሳችሁን ካለማመዳችሁት፤
ፍሬያማ የሆነ ሕይወት መኖር ትችላላችሁ።

አስቸጋሪ ከሆነባችሁ ሰው ጋር ያላችሁን ግንኙነት ሰላማዊ ለማድረግ፤ በየ
ጊዜው በመካከላችሁ የሚፈጠሩትን ግጭቶች በተለያየ መንገድ ለመፍታት
የተቻላችሁን ሁሉ ሞክራችሁ አቅቷችሁ ይሆናል። የራሳችሁን ፍላጎት ትታ
ችሁ አስቸጋሪው ሰው የጠየቀውን ሁሉ "እሺ!" በማለት ሰላም ለመፍጠር ሳት
ሞክሩ እንዳልቀራችሁ እንገምታለን። "እሺ! አንተ እንዳልክ" በማለት የራሳች
ሁን ፈቃድ መስዋዕት ብታደርጉም በመካከላችሁ ያለውን ግጭት ማቃለል
እንዳልቻላችሁ ስትረዱ፤ "ሰላም ማምጣት የሚቻለው በደካማነት ሳይሆን በብ
ርቱነት ነው" ብላችሁ በማመን ኮስተር ብላችሁ ጽኑ የሆነ አቋም ለመያዝ ሞክ
ራችሁም፤ ያም የምትፈልጉትን ዓይነት ውጤት ስላላስገኘላችሁ፤ "አሁንስ



አልቻልኩም! አቃተኝ!" ብላችሁ ተስፋ ቆርጣችሁ ይሆን? ሁኔታው የበለጠ
እየከፋ ሲመጣባችሁ፤ ያ አስቸጋሪ የሆነባችሁ ሰው፤ የእናንተን ሕይወት መራራ
በማድረግ እናንተን ለመቅጣት ታስቦ የተፈጠረ፤ እናንተ ደግሞ የእርሱን ሕይ
ወት ለማመቻቸት ብቻ እግዚአብሔር "የመስዋዕት በግ" አድርጎ የፈጠራችሁ
መስሎ ይሰማችሁ ይሆን? በቀመሳችሁት መራራ ሕይወት ምክንያት ከላይ
የጠቀስነውን ዓይነት ስሜት ቢሰማችሁ፤ ከአስቸጋሪው ሰው በስተቀር የሚፈር
ድባችሁ ሌላ ሰው ይኖራል ብለን አንገምትም።

አስቸጋሪ ሰዎች እንዴት ዓይነት ናቸው? ተለይተው የሚታወቁበትስ ምል
ክታቸው ምንድነው? አስቸጋሪ ሰዎች ተለዋዋጭ ባሕሪ ስላላቸው፤ ምን እንደ
ሚወዱና ምን እንደሚጠሉ፣ ምን እንደሚያስደስታቸውና እንደማያስደስታ
ቸው ለይቶ ማወቅ በጣም አስቸጋሪ የሚሆንበት ጊዜ አለ። አስቸጋሪ ሰዎች
እውነተኛ ማንነታቸው እንዳይታወቅባቸው በቀልጣፋ ንግግራቸው ራሳቸውን
የመደበቅ ልዩ ችሎታ ያላቸው በመሆናቸው ቀረብ ብለው ካላዩአቸው በስተቀር
ሰላማዊ ሰው በመምሰል ብዙዎችን ያስስታሉ። "አስቸጋሪ" የምንላቸው ሰዎች
በባሕሪያቸውና እንዲሁም የአስቸጋሪነታቸው መጠን የተለያየ ይሁኑ እንጂ
ሁሉም የሚመሳሰሉበት አንድ ነገር አላቸው። ያም፤ ከእነርሱ ጋር ተቀራርቦ
መኖር፣ አብሮ መሥራትም ሆነ በአንድ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አብሮ ማምለ
ክና ማገልገል በጣም ከባድ መሆኑ ነው። ይህ መጽሐፍ አስቸጋሪ ሰዎች አብረ
ውን የሚኖሩ፣ አብረውን የሚሠሩ፣ የሚጎራበቱን፣ በአንድ ቤተ ክርስቲያን
ውስጥ አብረውን የሚያመልኩና አብረውን የሚያገለግሉ ሊሆኑ እንደሚችሉ
ያሳያል። እንዲሁም አስቸጋሪ ሰዎች ምን ዓይነት አስተሳሰብና ጠባይ እንዳላ
ቸው ለማሳየት፤ ጎልቶ የሚታዩትን ዘጠኝ ጠባዮችን (...ተጠራጣሪነት፣ ንዴ
ተኛነት፣ ነቃፊነት፣ ስለ ሌላው ሰው ስሜት ግዴለሽነት፣ አኩራፊነት፣ ለእኔ
ብቻ ይደረግልኝ ባይነት፣ ተለዋዋጭነት፣ ሌላውን የመቆጣጠር ፍላጎትና ተበ
ቃይነትን) ዘርዝሮ ያሳያል። እያንዳንዱን ጠባይ እንደሚገባው በመግለጽ፤
አንባቢው ሳይሰለቸው እንዲያነብና ሀሳቡን የበለጠ መረዳት እንዲችል በማለት
እውነትነት ያላቸው ብዙ ምሳሌዎች ታክለውበታል። ምናልባት እናንተን ያጋ
ጠሟችሁ አስቸጋሪ ሰዎች በመጽሐፉ ላይ የዘረዘርናቸውን ጠባዮችን ሁሉንም
ባታዩባቸውም፤ አስቸጋሪ የሆኑባችሁን ሰዎች ለይታችሁ እንድታውቋቸው
መጠነኛ መረዳትን ይሰጣችኋል ብለን እናምናለን። በተጨማሪ አስቸጋሪውን
ሰው እንደ ጠባዩ ለመያዝ እንድትችሉ፤ አራቱን ዓይነት የሰው ተፈጥሮአዊ
ባሕሪዎች (Temperament) በአጭሩ ተገልጸዋል። ይህን መጽሐፍ አንድ ጊዜ
አንብባችሁ የምታስቀምጡት ሳይሆን፤ የተሰጡት መመሪያዎችና ሀሳቦች ከሕ
ይወታችሁ ጋር እንደሚገባው እስኪዋሃዱ ድረስ ደጋግማችሁ ማንበብ አለባ
ችሁ።

ግጭትን በመፍራት ብቻ ከሰው ሁሉ ሸሽተን ለብቻችን መኖር ችግራችንን አያቃልለውም። ባለን ግንኙነት ውስጥ አስቸጋሪው ሰው ሕይወታችንን በቁጥጥሩ ውስጥ እንዲያውል ልንፈቅድለት አይገባም። አስቸጋሪው ሰው፥ ዕለታዊ ኑሮአችንን መራራ እንዲያደርግብን እግዚአብሔር የሰጠንን የመምረጥና የመፍቀድ ነጻነታችንን እንዲገፍ ልንፈቅድለት አይገባም። የአስቸጋሪውን ሰው ጠባይ መለወጥ ባንችልም፥ ከአስቸጋሪው ሰው ጋር ያለንን አቋምም ሆነ መውሰድ የሚገባንን እርምጃ ግን መለወጥና ማስተካከል እንችላለን። ይህ መጽሐፍ፥ከአስቸጋሪው ሰው ጋር በሚኖረን ግንኙነት ውስጥ የራሳችንን አቋም እንዴት እንደምናስተካክል፣ እንዲሁም ከአስቸጋሪ ሰው ጋር እንዴት መኖር እንደምንችል መጠነኛ የሆነ ሀሳብ ይሰጣል ብለን እናምናለን። በቂ ጊዜ ወስዳችሁ መጽሐፉን በጥንቃቄ እንድታነቡትና በተግባር ላይ እንድታውሉት እግዚአብሔር የበለጠ ማስተዋሉን እንዲሰጣችሁ የዚህ ጸሐፊ ምኞትና ጸሎት ነው።

በመጨረሻ፥ ይህን በጣም ጠቃሚና ወቅታዊ የሆነውን መጽሐፍ አዘጋጅቼ ማቅረብ እንድችል በገንዘባቸው፣ በጸሎታቸውና በምክራቸው አስፈላጊውን እገዛ ያደረጉልኝን የአገልግሎታችን ተባባሪ የሆኑትን፣ ብዙ ሰዓት ወስደው ረቂቁን በጥንቃቄ አንብበው ጠቃሚ የሆነ አስተያየት የሰጡኝን፣ እንዲሁም ከጎኔ የተሰለፉትን የአገልግሎት ባልደረባዎቼን ከልብ አመሰግናለሁ።

1

# አስቸጋሪ ሰው እንዴት ይታወቃል?

የምንኖርበት ዓለም የእርስ በርስ ጦርነት የበዛበት፥ በቤተሰብ አባላት መካከል እውነተኛ የሆነ ሰላም፣ ፍቅርና አንድነት የጠፋበት፥ አንዱ ሌላውን በክፉ ድርጊቱና በክፉ ምላሱ የሚጎዳበት ዓለም ነው። ከምንጊዜውም የበለጠ በአሁኑ ጊዜ የሰዎች አንድነትና ሕብረት የደፈረሰበት፥ በአብዛኛው አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ የአማኞች መለያየትና መከፋፈል ጎልቶ የሚታይበት፥ ከፍቅር ይልቅ ጥላቻ ያየለበት ዘመን ነው። በሁኔታው ተደንቀን "ምክንያቱ ምን ይሆን?" ብለን መጠየቃችን አይቀርም። ይሁን እንጂ፥ ለዚህ ጥያቄ ሁሉን የሚያረካ መልስ መስጠት ቀላል አይደለም። እግዚአብሔር ሰውን የመፍቀድም ሆነ የመምረጥ ሙሉ ነጻነት ሰጥቶት እንደ ፈጠረው ቢረዳም፥ ተፈጣሪ የሆነው ሰው በማወቅም ሆነ ባለማወቅ፣ እግዚአብሔር መጀመሪያ ሰውን ሲፈጥረው የሰጠውን የመምረጥና የመፍቀድ መብቱንም ሆነ ነጻነቱን ለመግፈፍ፥ እንዲሁም በራሱ ቁጥጥር ሥር እንዲውል ለማድረግ ሲሞክር ይታያል። በግለሰብም ሆነ በአገር ደረጃ ጤናማ የሆነ ግንኙነትና አንድነት መመሥረት

የሚቻለው፥ አንዱ የሌላውን ምርጫ ሲያከብር፣ እንዲሁም ሁለቱም ወገን የፈቀደውን ለማድረግም ሆነ ላለማድረግ ሙሉ መብትና ነጻነት ሲኖረው ብቻ ነው። ለዚህ ነው ሰው ነጻነቱን ከሚገፍፈውና ፈቃዱን ከሚጫ ነው ሰው ጋር ተቀራርቦ ለመኖር ፈቃደኛ የማይሆነው። በሰዎች መካከል ሊኖር የሚገባውን ጤናማ የሆነ ግንኙነትና አንድነት ሊያበላሹ ከሚችሉት ዋና ዋና ምክንያቶች መካከል ከላይ እንደገለጽነው አንደኛው፥ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ አንዱ ሌላውን ሰው በቁጥጥሩ ሥር ለማዋል ወይም ነጻነቱን ለመጋ ፋፍ ሲሞክር ነው።

"ክፉ ናቸው" ከምንላቸው አንዳንድ ሁኔታዎች፥ እንዲሁም ከማንወዳቸውና ከማይወዱን፥ ወይም አስቸጋሪ ከሆኑብን ሰዎች ሁልጊዜ ሸሽተን ወይም ተደ ብቀን መኖር እንደማንችል የታወቀ ነው። በተለይ አስቸጋሪ የሆኑብን ሰዎች ቅርባችን የሆኑ፥ ወይም አብረውን የሚኖሩ ከሆኑ፥ በቀላሉ ከሕይወታችን ልናስወግዳቸው ወይም ልንሸሻቸው አንችልም። ይህ እውነት ከሆነ፥ "የስሜ ስብራት ወይም በሕይወታችን ከፍተኛ ጉዳት ሳይደርስብን እንዴት አብረና ቸው መኖር እንችላለን?" ይህ የብዙዎቻችን ጥያቄ ነው። የዚህም ጸሐፊ ዋና ዓላማ፥ ለዚህ ጥያቄ ሁሉንም የሚያረካ መልስ ለመስጠት ሳይሆን፥ ለአንባብ ያን የውይይት መድረክ ለመክፈት ነው። አንዳንድ አስቸጋሪ ሰዎች በሕይወ ታችን የሚፈጥሩትን ውዥንብር ተቋቁመን ፍጹም ሰላማዊ የሆነ ሕይወት ሁልጊዜ መኖር እንደማንችል ግልጽ ነው። ለሕይወታችን አቅጣጫ ወሳኞቹ እኛው ራሳችን ብንሆንም፣ አንዳንድ አስቸጋሪ ሰዎች በሕይወታችን ከፍተኛ ኃይል የሚኖራቸው ጊዜ አለ። ለምሳሌ፥ አስቸጋሪ ባል ያላት ሴት፥ ኑሮ ሲከብ ድባት፥ "አሁንስ አቃተኝ!.. በቃኝ!..." በማለት ትዳሯን አፍርሳ ለመሄድ የሚ ቃጣት ጊዜ ቢኖርም፣ "ልጆቼ ያለአባት እንዲያድጉ አልፈልግም..." በማለት ለልጆቿ ስትል ብቻ አስቸጋሪ በሆነ ኑሮ ውስጥ ለመቀጠል ራሷን መስዋዕት አድርጋ ትሰጣለች። ለልጆቿ ያላትን ፍቅር የተረዳው ያ አስቸጋሪ ባል፥ ሁኔ ታዎችን በማስተካከል ፈንታ፥ "የፈለግሁትን ባደርግ የትም አትሄድም" በማ ለት ኑሮዋ የበለጠ ከባድና መራራ እንዲሆንባት ማድረጉን ይቀጥላል። "ለል ጆቿ ስትል.." ስንል ችግሩ ልጆቹ ላይ አይፈናጠቅም ማለታችን አይደለም። እንዲሁም አስቸጋሪ የሆነ የሥራ አለቃ ያለውም ሠራተኛ በየቀኑ የሚኖረው ኑሮ ከባድ ሲሆንበት፥ ሥራውን ለቅቆ በመሄድ ፈንታ፥ "ሥራዬን ጥዬ ብሄድ ሌላ ሥራ በቀላሉ ማግኘት ስለማልችል ልጆቼን ምን አበላቸዋለሁ?" በማለት፥ ስለ ልጆቹ ሲል የአስቸጋሪው ሰው ባርያ ሆኖ መኖርን የሚመርጥበት ጊዜ አለ። ከአስቸጋሪ ሰው ጋር የሚኖሩ አንዳንድ ሰዎች፥ "ሁሉን ችዬ ዝም ብል፥ አሁን ከማደርገው የበለጠ በጎ ነገር ባደርግ፥ ራሴን ከምንጊዜውም የበለጠ መስ ዋዕት አድርጌ ብሰጥ፥ ምናልባት የአስቸጋሪው ሰው ሁኔታ ተለውጦ መልካም



ነገር ይፈጠር ይሆናል" ብለው በማሰብ ራሳቸውን ለመለወጥ ከፍተኛ ጥረት የሚያደርጉ አሉ። ይሁን እንጂ ምንም ያህል ቢጥሩ የአስቸጋሪውን ሰው ባሕሪ ለመለወጥ እንደማይችሉ፥ ሁኔታቸውም እየከፋ እንጂ እየተሻሻለ እንደማይ መጣ ግልጽ ነው።

## 1. አስቸጋሪዎቹ እኛ እንሆን?

በሁለት ሰዎች መካከል ያለው ግንኙነት (relationship) ጤናማ መሆኑ ንና አለመሆኑን በቅድሚያ ለይቶ ማወቅ፥ አስቸጋሪው ሰው ማን እንደሆን ለይ ተን እንድናውቅ ይረዳናል። ብዙ ጊዜ ጤናማ ባልሆነ ግንኙነት ውስጥ ታግሶ መቆየት ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ የበለጠ የሚያመዝንበት ጊዜ አለ። ከአስቸጋ ሪው ሰው ጋር ያለንን ግንኙነትን ጤናማ ለማድረግ ፈጽሞ የማይቻል ከሆነ፥ በቃል ኪዳን ጋብቻ ከተሳሰሩት በቀር፥ ለጊዜውም ሆነ እስከ መጨረ ሻው ድረስ ራስን አስቸጋሪ ከሆነው ሰው ገለል ማድረጉ የሚመረጥበት ጊዜ አለ። ለመሆኑ ጤናማ ያልሆነ ግንኙነት ምን ይመስላል?

- በሁለት ሰዎች መካከል የተመሠረተው ግንኙነት፥ አንደኛው ወገን ከመ ጠን በላይ በሌላው የሚደገፍ፥ ወይም "ያለእርሱ ምንም ነገር ማድረግ አልችልም"የሚል ከሆነ፥
- በሁለት ሰዎች መካከል የተመሠረተው ግንኙነት፥ ሁለቱንም ወገን በሚ መለከት ጉዳይ ላይ፥ የሁለቱም ፍላጎትና ምርጫ መጠበቅ ሲገባው፥ ሁል ጊዜ በአንደኛው ሰው ፍላጎትና ምርጫ ብቻ ላይ ያተኮረ ሲሆን፥
- በሁለት ሰዎች መካከል የተመሠረተው ግንኙነት፥ አንዱ ሌላው ባደረ ገው ወይም ባላደረገው ነገር ላይ ብቻ የሚያተኩር ከሆነ፥ ወይም አንዱ በሌላው ላይ "አጸፋዊ መልስ" የማሳየት ባሕሪ (reactive behavior) ካለው፥
- በሁለት ሰዎች መካከል የተመሠረተው ግንኙነት፥ አንዱ ሌላውን ልክ እንደ ባሕሪው በመቀበል ፈንታ ለመለወጥ ሲፈ ጊዜ፥ ብርቱ ጉልበትና ልዩ ልዩ ዘዴ ለመጠቀም የሚሞክር ከሆነ፥
- በሁለት ሰዎች መካከል የተመሠረተው ግንኙነት፥ አንዱ ሌላውን ከመጠን በላይ የሚያማርር ወይም ሁልጊዜ የሚወቅስ ከሆነ፥ ግንኙነታቸው ትክ ክለኛ ወይም ጤናማ እንዳልሆነ መረዳት እንችላለን።

በሁለት ሰዎች መካከል ያለው ግንኙነት የተበላሸበት ምክንያት፥ አንዱ ከሌላው ብዙ ነገር በመጠበቁ ይሆን? ወይስ በእርግጥ አብሮት የሚኖረው ሰው

የባሕሪ ችግር (personality disorder) ይታይባቸው እንጂ፥ እንደላይኞቹ የከፉ አይደሉም። ከነርሱ የበለጠ አስቸጋሪ የሆነውን ሰው የመከተል ባሕሪ ቢኖራቸውም፥ ለመለወጥ ፍላጎት ያላቸው ናቸው። ማንኛውም ሰው አልፎ አልፎ የአስቸጋሪነት ጸባይ የሚያሳይበት ጊዜ አለ። ይኸውም፥ አልፎ አልፎ የራስ ወዳድነት ባሕሪ የሚታይበት፥ እንዲሁም በማወቅም ሆነ ባለማወቅ በማልማት ፋንታ የሚያጠፋበት ጊዜ አለ። በሕይወቱ አንዴ ወይም ሁለቴ ይህን ዓይነት ባሕሪ የሚታይበትን ሰው ሁሉ "አስቸጋሪ ነው" ማለቱ ትክክል አይደለም። ትክክለኛው አስቸጋሪ ሰው ግን፥ አንዳንድ ጊዜ ብቻ ሳይሆን ብዙ ጊዜ በሌላው ሰው ሕይወት ውስጥ ችግር የሚፈጥር ነው። አስቸጋሪ ሰው ለሚፈጠረው ግጭት (conflict) ምክንያት ይሁን እንጂ፥ ማንኛውም ግጭት ሁልጊዜ መጥፎ ነው ማለት አይደለም። መጥፎ ግጭት እንዳለ ሁሉ፥ ጥሩ ግጭትም አለ። በየትኛውም ኅብረተሰብ ውስጥ አልፎ አልፎ አጥፊም ሆነ ገንቢ ግጭት ሊኖር ይችላል። ግጭት በሰዎች መካከል የሚፈጠረው አስቸጋሪ ሰዎች ስላሉ ብቻ ሳይሆን፥ አስቸጋሪ ሰዎች በሌሉበትም ሊኖር እንደሚችል ማወቅ ይገባናል። አስቸጋሪ የሆኑትን ሰዎች ለይቶ ማወቅ፥ በሀሳብ ከእኛ ጋር ያልተስማማውን ሁሉ "አስቸጋሪ ሰው" ብለን እንዳንጠራው ይጠብቀናል።

## 6. አስቸጋሪ ሰዎችን ቀረብ ብለው ካላዩአቸው በቀላሉ አይታወቁም

"አስቸጋሪ" ሰዎች ለመሆኑ ምን ዓይነት ባሕሪ የሚታይባቸው ናቸው? አስቸጋሪ ሰዎች፥ "አስቸጋሪ" የሚያሰኛቸውን ባሕሪያቸውን የመደበቅ ልዩ ችሎታ ያላቸው በመሆናቸው፥ ቀረብ ብለው ካላዩአቸው በስተቀር ለላማዊ ሰው በመምሰል ብዙዎቹን እንደሚያሳስቱ የታወቀ ነው። ያም ሆነ ይህ፥ አስቸጋሪ የሆኑ ሰዎች የሌሉበት ሥፍራ የለም። በአንዳንድ የተፈጥሮ ባሕሪያቸውና አስቸጋሪ በሆነው ጠባያቸው የሚመሳሰሉበት አንዳንድ ሁኔታዎች ይኑራቸው እንጂ፥ አስቸጋሪ ሰዎች ሁሉም ተመሳሳይ ባሕሪ ያላቸው አይደሉም። አንዳንድ "አስቸጋሪ" ሰዎች፥ ምን ዓይነት መጥፎ ባሕሪ እንዳላቸውና በሌላው ሰው ሕይወት ላይ ሊያደርሱ የሚችሉት ጉዳት ምን ያህል ከባድ እንደሆነ ከማንም ሰው የበለጠ ሊያውቁ የሚችሉት፥ አብረዋቸው የሚኖሩ፥ ወይም ቅርብ የሆነ ግንኙነት ያላቸው ሰዎች ብቻ ናቸው። እነዚህ አስቸጋሪ የሚባሉ ሰዎች፥ ከማንኛውም ሰው ጋር በቀላሉ ተስማምተውና ተቻችለው መኖር የሚሆንላቸው አይደሉም። እንዳይስማሙም ከሚያደርጋቸው ምክንያቶች መካከል መሠረታዊ የሆኑትን ሦስቱን እንመለከታለን።



1ኛ) አስቸጋሪ ሰዎች፥ "የጠራ አመለካከት" ያላቸው አይደሉም። ማየት የሚፈልጉትን ብቻ እየመረጡ የሚያዩ ይመስላሉ። ይኸውም፥ የሌሎችን ድካም፥ ክፋትና ሽንፈት እንጂ፥ ብርታታቸው፥ በጎነታቸውና አሸናፊነታቸው ፈጽሞ አይታያቸውም። በሌላው ሰው ሕይወት ውስጥ ያለውን ጥሩ ነገር ማየት ስለማይችሉ፥ ሁልጊዜ መንቀፍ እንጂ፥ ማመስገንና ማደነቅ አይሆንላቸውም።

2ኛ) አስቸጋሪ ሰዎች፥ "አጥርተው መስማት የሚችሉ" አይደሉም። ይህን ስንል ጆሮአቸው አይሰማም ማለት ሳይሆን፣ ትክክለኛ የሆነውን አሳብ የመረዳት ችሎታቸው አነስተኛ ነው ማለታችን ነው። በትክክል መረዳት፥ ወይም አጥርተው መስማት የማይሆንላቸው መሆናቸውን የምንረዳው፥ ሌላው ሰው የሚናገረውን ንግግር ትክክለኛ አሳቡን፥ ወይም ልክ እንዳለ የተባለውን በመስማት ፈንታ የሚሰሙት ያልተባለውን፣ ለተነገረው ነገር ሁሉ ልዩ ትርጉም የሚሰጡት መሆናቸውን ስናይ ነው። መስማት የሚፈልጉትን ብቻ እየመረጡ የሚሰሙ መሆናቸው ብቻ ሳይሆን፥ የሚረዱትም ትክክል ባልሆነ መንገድ ነው።

3ኛ) አስቸጋሪ ሰዎች ጤናማ ምላስ ያላቸው አይደሉም። ጊዜውን ያልጠበቀና ልክ ያልሆነ ነገር የመናገር ዝንባሌ ያላቸው ናቸው። ሌላውን ምንም ያህል ቢጎዱ፥ "ጎዳሁህ! ...አዝናለሁ! ...አንተ ልክ ነህ፣ ...ስህተቱ የእኔ ነው" ማለት ፈጽሞ አይሆንላቸውም። እንደነዚህ ዓይነት ሰዎች የማንንም ሰው ሕይወት መራራ ወይም አስቸጋሪ የማድረግ ዝንባሌ እንዳላቸው የታወቀ ነው።

### 6.ሀ. "አስቸጋሪ ሰዎች" የተቃወሰ ገጸ ባሕሪ የሚታይባቸው ናቸው

"አስቸጋሪ ናቸው" የምንላቸው ሰዎች፥ "የተቃወሰ ገጸባሕሪ" (character disorder) በግልጽ የሚታይባቸው ናቸው። ገጸባሕሪ (character) የሚለው አሳብ በቅድሚያ በትክክል ካልገባን፥ "የተቃወሰ ገጸባሕሪ" ምን እንደሆነ፥ እንዲሁም የአስቸጋሪ ሰው የድካሙ ምክንያት ከምን የመጣ እንደሆነ መረዳት ያስቸግረናል። ገጸባሕሪ (character) ለመሆኑ ምንድነው?

- ገጸባሕሪ የአንዱን ሰው የአዕምሮና የሥነ-ምግባር አቋም የሚያሳይ፥ አንዱ ከሌላው ሰው ተለይቶ የሚታወቅበት፥ ወይም የአንዱ ሰው ትክክለኛ ማንነት የሚለይበት እውነተኛው ጸባይ ነው።

| | | |
|---|---|---|
| | ለሥራ ፈቃደኝነትን ያሳያል | የዓላማ ሰው ነው |
| | አዳዲስ ሥራዎችን ያመነጫል | ሁኔታዎችን በስፋት ማየት ይችላል |
| | ከውጪ ሲታይ ያማረ ይመስላል | የማደራጀት ችሎታ አለው |
| | የፈጠራ ችሎታ አለው | በተግባር ላይ የሚውል መፍትሄ ይሰጣል |
| **ለሥራ ያለው አቋም** | ጉልበትና መነቃቃት አለው | አሳብን በተግባር ላይ ለማዋል ፈጣን ነው |
| | አጀማመሩ ከውጪ ያማረ ነው | ሥራ ያከፋፍላል (ይወክላል) |
| | ሌሎችን የማነቃቃት ችሎታ አለው | ውጤት ላይ ትኩረት ይሰጣል |
| | ሌሎች ደስ ብሏቸው እንዲሠሩ ያደርጋል | ግብ ያወጣል |
| | | ሌሎች ለሥራ ማነቃቃት ይችላል |
| | | ተቃውሞን ለዕድገቱ ያውላል |

| | | |
|---|---|---|
| | በቀላሉ ወዳጅ ያፈራል | ጓደኛ ባይኖረውም ግድ የለውም |
| | ሰው ይወዳል | በማኅበር መሥራት ይወዳል |
| | የሰዎች ምስጋና ይፈልጋል | መምራትና ማደራጀት ይችላል |
| | የተነቃቃ ሰው ነው | ብዙ ጊዜ ትክክል ነው |
| **ከሰው ጋር ያለው ግንኙነት** | ሌሎች ይቀኑበታል | በችግር ጊዜ ብርቱ ሆኖ ይታያል |
| | ቂም አይዝም | |
| | ቶሎ ይቅርታ ይጠይቃል | |
| | የቸከ ጊዜ እንዳይኖር ያደርጋል | |
| | ያልታቀደ ነገር ሲያጋጥመው ደስ ይለዋል | |



## ጠንካራ ጎን...

| | ሜላንኮሊ | ፍላግማቲክ |
|---|---|---|
| | የአሳብ ሰው ነው | በተፈጥሮ ባሕሪው ረጋ ያለ ነው |
| | የማስላሰል ችሎታ አለው | ተግባቢና ተዝናንቶ የሚኖር ሰው ነው |
| | ኮስታራና የዓላማ ሰው ነው | ረጋ (ዝግ) ያለ ሰው ነው |
| | የተፈጥሮ ችሎታ ያለው ነው | ትዕግስተኛና ሚዛኑን የጠበቀ ነው |
| **ስሜት** | የሥነ ጥበብ ሰው ነው | ተለዋዋጭነት የሌለው ሰው ነው |
| | የፍልስፍናና የቅኔ ሰው ነው | ሩሕሩህና ደግ ሰው ነው |
| | የተፈጥሮን ውበት አድናቂ ነው | ዝምተኛና የጥበብ ሰው ነው |
| | ስለ ሌሎች ስሜት ግድ ይለዋል | ስሜቱን ገልጾ አያሳይም |
| | ራሱን መስዋት ያደርጋል | ኑሮውን በደስታ የሚኖር ነው |
| | ታታሪ ሰው ነው | ዓላማ ያለው ሰው ነው |
| | በፕሮግራም የሚሄድ ነው | ችሎታ ያለውና ጽኑ ሰው ነው |
| | "ፍጹም ይሁን" ባይ ነው | ሰላማዊና ተስማሚነት ያለው ነው |
| | ለጥቃቅኑ ነገሩ ሁሉ ጠንቃቃ ነው | የአስተዳደር ችሎታ አለው |
| | የጠለቀ አሳብ ያለውና ጽኑ ነው | ግጭትን ይሸሻል |
| **ሥራ** | ሥርዓት የጠበቀና የተደራጀ ነው | በውጥረት ውስጥ ጥሩ ውጤት ያመጣል |
| | ንጹህና ያማረ ነው | ቀለል ያለ መንገድ ያገኛል |
| | ቆጣቢ ነው | |
| | ችግሩ የት እንዳለ ያውቃል | |
| | ጥሩ መፍትሄ የማግኘት ችሎታ አለው | |
| | የጀመረውን ይጨርሳል | |

| | | |
|---|---|---|
| ***ከሰው ጋር ያለው ግንኙነት*** | ወዳጅ ለመያዝ ጠንቃቃ ነው | በቀላሉ መስማማት የሚችል ሰው ነው |
| | ጎልቶ ባይታይም ግድ የለውም | የደስ ደስ ያለው ነው |
| | ልታይ ባይነት ባሕሪ የለውም | ማንንም ማስከፋት አይፈልግም |
| | ታማኝነትና ራሱን የሰጠ ሰው ነው | ጥሩ አድማጭ ነው |
| | የሌሎችን ቅሬታና ስሞታ ያዳምጣል | ቀልዱ ደረቅ (የማይጥም) ነው |
| | የሌሎችን ችግር መፍታት ይችላል | ሰዎችን ማየት ደስ ይለዋል |
| | ለሌሎች በጣም አሳቢ ነው | ባለ ብዙ ወዳጅ ነው |
| | በርህራሄ የተሞላ ነው | ስለ ሌሎች ይራራል፣ ግድ ይለዋል |

# አስቸጋሪ ሰዎች የሚያሳዩት ጠባይ

ሰዎች በትዳራቸው ውስጥ፣ አስቸጋሪ በሆኑ የኑሮ ጓደኞቻቸው ምክንያት ጋብቻቸው ሊያልፉት የማይችሉት ልዩ ልዩ ችግሮች ሲያጋጥማቸው፣ ዕለታዊ ኑሮአቸው ፍጹም መራራ ሲሆንባቸው፣ የሚያሰሙት የራሳቸው የሆነ ዕሮሮ ወይም ብሶት አላቸው። አስቸጋሪ የሆነ ባል ያላት ሴት፣ *"...ባሌ በጣም አስቸጋሪ ሰው ሆነብኝ፣...ችግሩ ይሄና ያ ነው ብዬ በቀላሉ መናገር ባልችልም፣ አንድ ባለ ያልሆነ አስቸጋሪ ባህሪ እንዳለበት ግን አውቃለሁ..."* ትላለች። "ችግሬ ሚስቴ ናት" የሚለውም ባል፣ *"....በፍጹም ላውቃት አልቻልኩም... ተለዋዋጭ የሆነ ባሕሪ ያላት ሴት ናት!... አሁን ስቃና ተጫውታ እንደሆነ፣ ከጥቂት ደቂቃ በኋላ ስትበሳጭና ስትቆጣ ኢያታለሁ.."* ይላል። እንዲሁም አስቸጋሪ ጎረቤት ያጋጠማቸው ሰዎች የሚያሰሙት የራሳቸው የሆነ ዕሮሮ አላቸው። ቤተ ክርስቲያንም ከአስቸጋሪ ሰዎች ፍጹም ነጻ ስላልሆነች፣ በአማኞች መካከል በአንዳንድ አስቸጋሪ ሰዎች ምክንያት የሚካሄደውን የማያቋርጥ ጦርነት፣ መለያ

እንጂ ከመጠን በላይ ራሳቸውን የሚወዱ ሰዎች ናቸው። አብዛኞዎቹ ይህን ዓይነት ጠባይ የሚያሳዩት የራሳቸውን ድካም ለመሸፈን እንደሆን ማወቅ አለብን። "ሳይቀድሙኝ፣ ልቅደም" በማለት ራሳቸውን ለመከላከል የሚወሰዱት እርምጃ እንደሆነ የሥነ አዕምሮ ምሁራን ይናገራሉ። ሌላውን በመሰደብና በማዋረድ ከዚያ ከሚሰድቡት ሰው በልጠው ለመታየት ስለሚፈልጉ ነው። "ሌላ ሰው አልፈልግም፤ ለብቻዬ ብቁ ነኝ" የማለት ጠባይ ይታይባቸዋል። የማንንም ምክር፣ አስተያየትና ድጋፍ የሚፈልጉ አይደሉም። ከእነርሱ የተሻለ አሳብ ያለው ሰው ይኖራል ብለው ስለማያምኑ፣ የማንንም ሰው አስተያየት ለማዳመጥ የተዘጋጁ አይደሉም። በራሳቸው አሳብ ብቻ የሚመሩ ከመሆናቸው ሌላ ብዙ ጊዜ ኃላፊነትን ለመውሰድ ፈቃደኞች አይደሉም። ስለሆነም፣ አንድ ነገር የተበላሸ ከመሰላቸው ግን፣ በሌላው ሰው ላይ የማመካኘት ወይም ሌላ ነገር ምክንያት የማድረግ ባሕሪ አላቸው። አንድ አሳብ አፍልቀው ውጤቱ ልክ ካልመጣ፣ "አሳቡን በትክክል ተግባር ላይ ስላላዋሉት ብቻ ነው" በማለት ሁልጊዜ ጣታቸውን በሌሎች ላይ ይጠቁማሉ። ራሳቸውን ሁልጊዜ ፍጹም፣ ሌሎችን ግን ዝቅ አድርገው ስለሚመለከቱ፣ "የእኔን ምክር ወይም አሳብ ብትቀበል ኖሮ እንዲህ ዓይነቱን ስህተት አትፈጽምም ነበር" ይላሉ። ይህን ዓይነት አስተያየት ሲሰጡ፣ በዕድሜ የገፋውን ሰው፣ በዕውቀቱ የላቀውን ሰው ያለአግባብ የትንሽነት መንፈስ እንዲሰማው ማድረጋቸው እንደሆነ ፈጽሞ አይታወቃቸውም።

ስለ ሌላው ሰው ስሜት ግድ የሌላቸው አስቸጋሪ ሰዎች፣ የሕይወታቸው ዋና ዓላማ ሁልጊዜ አሸናፊዎች መስለው ወይም ሆነው መታየትን ነው። በአካባቢያቸው ማን ኃይልና ሥልጣን እንዳለው፣ ወይም የሥልጣኑ ቁልፍ ማን ዘንድ እንዳለ ያውቃሉ። አንዳንዶቹ ሰውን የሚጠጉት ለግል ጥቅማቸው ሲሉ እንደሆነ ግልጽ ነው። ከሌሎች ቀድመው መሄድ፣ ወይም ለመብለጥ የሚያስችላቸውን ሁሉ ለማድረግ ወደ ኋላ አይሉም። ራሳቸውን አተልቀው ለማሳየት ደካማ መስሎ ለሚታያቸው ሰው ራሳቸውን ከፍ አድርገው ማሳየት ከባህሪያቸው አንደኛው ነው። እንዲህ ዓይነቶቹ ብዙ ጊዜ ባሕሪያቸው ከሁኔታዎች ጋር ቶሎ ቶሎ ይለዋወጣል። በብዙ ነገር ውስጥ እጃቸውን ስለሚያስገቡ፣ የአካባቢውን ሰላም በቀላሉ ያደፈርሳሉ። ከማንም ጋር የማያስማማቸው አመጸኛ ጠባያቸው በግልጽ ስለሚታይ፣ አስቸጋሪ ሰዎች መሆናቸው በቀላሉ ይታወቃል። እነርሱ በሚገኙበት አካባቢ ሁኔታዎች ቶሎ ቶሎ ሲለዋወጡ ይታያሉ። የሰዎች ሰላምና አንድነት በቀላሉ ይደፈርሳል። የራሳቸውን ፍላጎት ብቻ ለመፈጸም እንጂ ስለ ሌላው ፍላጎት ግድ የላቸውም። በአንድ ነገር ላይ ዓይናቸውን ካሳረፉ፣ "እንዲህ ነው" ብለው ካመኑ፣ ተከራክሮ ሊያሳምናቸውና አሳባቸውን ሊያስለውጣቸው የሚችል ማንም የለም። ሌላው ሁሉ የተሳሳተ፣ እነርሱ ብቻ ልክ የሆኑ ስለሚመስላቸው ከእነርሱ ጋር መደራደር ፈጽሞ አይቻልም። አንዳንድ ጊዜ ከአፋቸው የሚወጣው መጥፎ ቃል፣ አዕምሮ ካለውና ማሰብ ከሚችል ሰው አፍ የወጣ ነው ብሎ ማመን ያስቸግራል። እናንተን ያጋጠማችሁ አስቸጋሪ ሰው፣ ከላይ እንደገለጽነው፣ ስለ ሌላው ሰው ስሜት ፍጹም ግድ የሌለው ሰው ይሆን? ከእንደዚህ ዓይነቱ ሰው ጋር "ስሜቴ ሳይጎዳ፣ ራሴን ሳልጠላ መኖር የምችልበት መንገድ ወይም ዘዴ ይኖር ይሆን?" የሚል ጥያቄ በውስጣችሁ ይመላለስ ይሆናል። ለዚህ ጥያቄያችሁ ምዕራፍ ሰባት ላይ፣ "ሁሉንም እንደ ጠባያቸው መያዝ ነው" በሚለው ነጥብ ሥር መጠነኛ አሳብ ያሰፈርን ስለሆነ፣ ያንን ክፍል መመልከት ይጠቅማችኋል።

# 5 ~ አኩራፊነት

~ "...ምን ብዬ ይሆን?...ሳላውቅ ምን ብዬ ተናግሬ... ምን አድርጌ አስቀይሜው ይሆን?..."

~ "...ባኮረፈች ቁጥር ሁልጊዜ እርሷን መለማመጡ አሁንስ ሰለቸኝ?..."

~ "...አሁንስ ኩርፊያው ሊገድለኝ ነው..."

ይህን ዓይነቱ አነጋገር ብዙዎች በየቤታቸው የሚያሰሙት እሮሮ ነው። መጠኑና ዓይነቱ ይለያይ እንጂ፣ ደስ የማይል ነገር ሲያጋጥማቸው ስሜታቸውን ዝም በማለት መግለጽ የሚፈልጉ አንዳንድ ሰዎች እንዳሉ የታወቀ ነው። የዝምታቸው ርዝመት እንደ ሰው የተለያየ ነው። የአንዳንዶቹ ከጥቂት ደቂቃዎች ወይም ሰዓቶች አያልፉም። የሌሎች ደግሞ በወራት ይቆጠራል። ለረጅም ጊዜ "አስቀየመን" ብለው ከሚሉት ሰው ጋር በአካል መሸሽ፣ የስልክ ግንኙነታቸውን ማቋረጥ፣ በአካል የሚገናኙበት አጋጣሚ ሁኔታ የተፈጠረ እንደሆን ደግሞ በተቀየሙት ሰው ላይ ፊታቸውን ሲያዞሩ፣ ወይም ዝም ሲሉት ይታያል። "አስቀየመን" ከሚሉት ሰው ጋር አብረው የሚኖሩ፣ አብረው የሚሠሩ ከሆነ፣ በአካል መሸሽ ስለማይችሉ ስሜታቸውን የሚገልጹት፣ ከተቀየሙት ሰው ጋር ያላቸውን ሰላምታም ሆነ ንግግር በማቆም ነው። የአኩራፊነት ጠባይ ያላቸው ሁሉም የራሳቸው የሆነ የተለያየ ምክንያቶች አሏቸው፣

## (5.ሀ) <u>*ባልታወቀ ምክንያት የሚሸሹና የሚያኮርፉ ሰዉ*</u>

በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ገንቢ ያልሆነ ቃል ተናግሮ አንዱ ሌላውን ሰው የሚያስቀይምበት ጊዜ አለ። ፊት ለፊት *"...እንዲህ ዓይነት ቃል ተናግረህ ለምን ትጎዳኛለህ?"* በማለት ፊንታ፣ ማኩረፍ የሚቀናቸው ሰዎች አሉ። ባልና ሚስት

አልፎ አልፎ በሀሳብ መገናኘት ወይም መስማማት ሲያቅታቸው፥ ከሁለቱ አንደኛቸው ሌላውን የሚጎዳ፥ ወይም አግባብ ያልሆነ ክፉ ቃል የሚወረውሩበት ጊዜ አለ። በተወረወረው ቃል የተጎዳው ሰው አጸፋውን በመመለስ ፈንታ፥ ሁለቱም በረድ አስከሚሉ ድረስ በንግግሩ ሳለመቀጠል በወቅቱ የተጎዳው ሰው ዝም ቢል ወይም ከመናገር ራሱን ቢቆጥብ፥ ብልህነት እንጂ አኩራፊነት አይደለም። አልፎ አልፎ በሚቀራረቡ ሰዎች መካከል አንዳንድ ግጭት መፈጠሩ አይቀርም። ወዳጆች በመሆናቸው ብቻ ሁልጊዜ አንድ ዓይነት አስተሳሰብ፥ አንድ ዓይነት ምርጫ ይኖራቸዋል ማለት አይደለም። ወዳጅነታቸው ዘላቂነት እንዲኖረው ይህን አውነት ማመንና መቀበል ይኖርባቸዋል። በአሳብ ሰንስማማ ብቻ ወዳጆች፥ ካልተስማማን ግን እንደ ጠላቶች መተያየት ትክክል አይደለም። "ላለመስማማትም" መስማማት አለባቸው። ይህንን ባለመረዳት ሌላው ሰው በአሳብ ከእነርሱ የተለየ ሲሆን፥ የተሰማቸውን ስሜት በመግለጽ ፈንታ በቀላሉ የሚያኮርፉ ከሆነ፥ ወዳጅነታቸው ዕድሜ ሲኖረው አይችልም።

ዘገየና ዋሲሁን የትምህርት ቤት ጓደኛማቾች ናቸው። ትምህርታቸውን ጨርሰው ወደ ሥራው ዓለም ከገቡም በኋላ ጓደኝነታቸው አልቀረም። ከሥራ ሲወጡ ብዙ ጊዜ የሚያመሹት አንድ ላይ ነው። ሌላው ቢቀር በስልክ በቀን ውስጥ ቢያንስ ቢያንስ ሁለት ጊዜ ይገናኛሉ። ትዳር ሲይዙ አንዱ የሌላው ሚዜ ነበር። ወዳጅነታቸው በእነርሱ መካከል ብቻ ሳይሆን በቤተሰብ ደረጃም እንዲቀጥል ፍላጎት ነበራቸው። በሁለቱም ወገን ከሞት በስተቀር ሊለያያቸው የሚችል ነገር ይኖራል ብለው አያምኑም ነበር። ይሁን እንጂ፥ በመካከል አንዳንድ ለውጦች መታየት ጀመሩ። ዘገየ ራሱን ከዋሲሁን ማሸሽ ጀመረ። ሌላው ቀርቶ ለስልክ ጥሪው እንኳን መልስ አይሰጥም ነበር። "ምነው ተጠፋፉን" ሲለው፥ ዘገየ ቀና አይመልስለትም። "ሥራዬን ትቼ ሁልጊዜ አንተን መፈለግ አለብኝ እንዴ!..." የሚል መልስ ይሰጠዋል። ወዳጅነት የሚጸናው ሁለቱም ወገን ሲፈላሰግ እንጂ፥ የአንዱ ወገን መፈለግ ብቻ ሊያቀራርባቸው ስለማይችል፥ ቀስ በቀስ ዘገየና ዋሲሁን እየተራራቁ መጡ። በዋሲሁን አዕምሮ ውስጥ ልዩ ልዩ ጥያቄዎች መፈጠር ጀመሩ፥ *"ምን ተናግሬ አስቀይሜው ይሆን?... ምን አድርጌው ይሆን?..."* በማለት ራሱን ይጠይቅ ነበር። ለነዚህ ጥያቄዎች መልስ ሲያገኝላቸው ስላልቻለ፥ በአዕምሮው ውስጥ ትልቅ ውጥረትን ፈጠሩበት። እንዲህ ዓይነት ሁኔታ ብዙዎቻችን ደርሶብን አይተነዋል። በጣም የቀረብናቸው፥ የወደድናቸውና ራሳችንንና ገበናችንን ገላልጠን ያሳየናቸው ወዳጆቻችን እኛ በማናውቀው ምክንያት ድንገት ተለዋውጠው ሲሸሹን፥ ሲያኮርፉን ስላየን፥ የኩርፊያ ጠባይ ካለባቸው አስቸጋሪ ሰዎች ጋር የሚኖሩ ሰዎች ምን ዓይነት ስሜት እንደሚሰማቸው በመጠኑም ቢሆን እናውቃለን።



እንዲህ ዓይነቱ መራራቅ (ኩርፊያ) ሁለት ዓይነት መልክ አለው። አንደኛው፥ ከላይ በዘገየና በዋሲሁን መካከል ተፈጥሮ እንዳየነው ድንገት የሚሆን፥ ምክንያቱ በግልጽ ያልታወቀ መራራቅ ነው። ከአንዳንድ ሰዎች ጋር ትላንትና ማታ አብረን በልተን፥ ተሳስቀን፥ አብረን አምሽተን፥ ዛሬ ባልታወቀ ምክንያት ድንገት ግንኙነታችን የሚቋረጥበት ጊዜ አለ። መሸሽ የመረጠው አንደኛው ወገን ለመራቅ የፈለገበት የራሱ ምክንያት ይኖረዋል። ምክንያቱን ግን ገልጾ መናገር ፈቃደኛ አይሆንም። በዚህ መካከል ልቡን የሚከብደው፥ የራሱ ምክንያት ኖሮት የሸሸው ሰው ብቻ ሳይሆን፥ ምክንያቱን ያልተረዳው፥ በሌላው ወገን ያለውም ሰው ጭምር ነው። ይህን ዓይነቱ ኩርፊያ በአንድ ቤት ውስጥ የማይኖሩ በመሆናቸው፥ ግንኙነታቸውን ከሌሎች ሰዎች ጋር በማድረግ ቀስ በቀስ ሊረሱት ስለሚችሉ፥ የሚያስከትለው ጉዳት ይህን ያህል አሳሳቢ ላይሆን ይችላል። ሁለተኛው ዓይነት ኩርፊያ ግን አብረው በአንድ ጣራ ሥር በሚኖሩ፥ አንዳንዴም አንድ የብርድ ልብስና አንሶላ ለብሰው አንድ አልጋ ላይ በሚተኙ ባልና ሚስት መካከል የሚፈጠረው ነው። ይሄኛው ከመጀመሪያው የበለጠ ከባድ ነው።

## *(5.ለ) <u>ሌላው በሚናገረው ንግግር "ተጎዳሁ" በማለት የሚያኮርፉ አሉ</u>*

ኃይሉና በላይነሽ ቅዳሜ ማታ ወዳጆቻቸውን ዕራት ጋብዘው ስለ ነበረ ቀኑን ሙሉ ቤታቸውን ሲያሳምሩ፥ ምግብ ሲያዘጋጁ ዋሉ። በተባለው ሰዓት ተጋባዦቹ መጡ። ምግቡ ተበላ፤ ጨዋታው፥ ሳቁ፥ ሌላ ነበር። ተጋባዦቹ ብቻ ሳይሆኑ፥ ኃይሉና በላይነሽም ደስ አላቸው። ወደ መጨረሻው ገደማ፥ ቁጭ ብለው ሲጫወቱ፥ በላይነሽ አንዳንድ ነገር እያነሳች ማውራት ጀመረች። ገና ንግግሯን ሳትጨርስ ኃይሉ አቋረጣትና "ታሪኩ እንደዚያ አይደለም" በማለት እያስተካከለ ማውራት ጀመረ። በላይነሽ ያ ቀይ ፊቷ በርበሬ መሰለ። በተቻላት መጠን በውስጧ የተሰማትን ስሜት እንግዶቹ እንዳያውቁባት ከፍተኛ ጥረት አደረገች። በላይነሽ ፊት ላይ አንዳንድ ሁኔታዎችን ቢያዩም፥ ኃይሉም ሆነ የተጋበዙት ሰዎች ስሜቷን ምን እንደለወጠው፥ ምን ቅር እንዳሰኛት አልተረዱም ነበር። ሰዓቱ መምሸቱን በመመልከት ሁሉም ጋባዦቹን እያመሰገኑ ወደ ቤቱ ሄደ። በበላይነሽ ልብ ውስጥ ምን እየተካሄደ እንደሆነ ያላወቀው ኃይሉ፥ "በጣም ጥሩ ጊዜ ነበረን አይደል?...." ሲል በላይነሽን ጠየቃት። በላይነሽ ግን የጠበቀውን ዓይነት መልስ አልሰጠችውም። ልክ እንግዶቹ እንደወጡ መናገሯን አቆመች። ኃይሉ መልስ በማጣቱ "...ምነው? ምን ሆንሽ?..." ብሎ ጠየቃት። "...ምንም!.." የሚል አጭር መልስ ሰጠችው። አሁንም በመደጋገም "...ምን ተናግሬ አስቀይሜሽ ይሆን?..." በማለት ቢጠይቃት መልስ ከለከለችው። ብዙ ጊዜ እንግዶች ተጋብዘው ሲሄዱ፥ ዕቃውን አነሳስተውና አጥበው

ሙብት ሰው ሁልጊዜ ከአጠገባቸው እንዳይርቅ የተቻላቸውን ያህል ከፍተኛ ጥረት ያደርጋሉ። ያ መጠቀሚያ ያደረጉት ሰው በአንድ ምክንያት አጠገባቸው ባልተገኘበት ወቅት ጥቂት በጎ ያልሆነ ነገር ድንገት ካጋጠማቸው፣ በቀላሉ ይበረግጉና በአካባቢያቸው ካለው ሁሉ ዕርዳታ ለማግኘት ለሚሰማቸው ሁሉ ጉዳታቸውን ያውጃሉ። በዚህ ዓይነት ሁኔታ ሁሉም የእርዳታ እጁን ስለሚዘረጋላቸው፣ አንዳንድ አስጊ ሁኔታ (crisis) ሲፈጠር ደስ የሚላቸው ጊዜ አለ። ሰዎችን ወደ እነርሱ የሚስብላቸው ስለሚመስላቸው፣ ችግረኛ (needy) ሆኖ መታየት ደስ ይላቸዋል። ይሄም ሌላውን ሰው መጠጋት የሚችሉበት አንዱ መንገዳቸው ነው። ተረጂነታቸው (ችግረኛነታቸው) ቁሳቁሳዊ ነገር ብቻ ሳይሆን፣ ሥነ-ልቦናዊ (psychological) ነገር ጭምር ነው። ይሄም ከውስጣቸው የሰው ዕርዳታ የመፈለግ ኃይለኛ የሆነ ጥማት እንዳላቸው የሚያሳየን ነው። ከውጪ በሚያዩዋቸው ሰዎች ዘንድ ትልቅ መስለው ለመታየት ይሞክሩ እንጂ፣ ከውስጣቸው ግን የዝቅተኛነት ስሜት ያጠቃቸው እንደሆነ ግልጽ ነው። ሰው ስለ እነርሱ የሚሰጠውን አስተያየት ስለሚፈሩ፣ ራሳቸውን ችሰው መቆም አለመቻላቸውን፣ ሁልጊዜ ሌላውን ሰው መፈለጋቸውን ማንም ሰው በምንም ዓይነት እንዲያውቅባቸው አይፈልጉም።

"ለዚህ ዓይነቱ ባሕሪያቸው ምክንያት የሆነው ምን ይሆን?" ብለን መጠየቃችን አይቀርም። ኃላፊነት ሳይማሩ ያደጉ ልጆች ከመጠን በላይ የሚፈሩት ነገር ቢኖር አንደኛው፣ ሥራ ሠርተው፣ ራሳቸውን ችሰው መኖርን ነው። እንደእነዚህ ዓይነቶቹ ቢሠሩ ሥጋቸው የሚፈራርስ ስለሚመስላቸው ከሥራ የሚሸሹበትን ምክንያት ይፈልጋሉ። አንዳንዶቹ ደግሞ ከወላጆቻቸው ስለ ሥራ ክቡርነት እየተነገራቸው ያደጉ አይደሉም። የሚፈስ ውሃ ቀና ሳታደርግ፣ ተቀምጣ አሽከር እያዘዘች ብቻ የኖረችውን እናትዋን እያየች ያደገች ሴት፣ አግብታ በተራዋ ቤተ ሰብ ስትመሠርት፣ ሥራ መሥራት ውርደት መስሎ ስለሚታያት፣ ተቀምጣ ሁሉን ነገር ሌላው ሰው እንዲሠራላት እያዘዘች መኖር ትፈልጋለች። አልፎ አልፎ ጥቂት የሠራች እንደሆነ የተበደለች ስለሚመስላት በቤተ ሰቡ ላይ ትነጫነጫለች። እንዲሁም ቁጭ ብላ "ወይኔ! ገረድ ሆንኩ አኮ!" እያለች ለራሷ ታለቅሳለች። እንደነዚህ ዓይነቶቹ አብረዋቸው ለሚኖሩ ሰዎች አስቸጋሪና ሸክም መሆናቸው ብቻ ሳይሆን፣ ላሉበትም ሕብረተሰብ ሸክም እንደሚሆኑ ግልጽ ነው።

ስንፍናቸውን ለማስቀምና ለሕብረተሰቡ ጠቃሚ አካል እንዲሆኑ ምክር ቢሰጣቸው፣ የሰደቧቸውን ያህል የሚቆረቁራቸው ናቸው። ብዙ ሳይሠሩና ብዙ ሳይለፉ፣ የሌሎችን ሰዎች ጉልበት በልዩ ልዩ ዘዴ ተጠቅመው የተሳካላቸው ከሆነ ደግሞ፣ "ምንም ሳልደክም የእኔ ጌታ ከሰው ሁሉ በላይ አንቀባሮ ያኖረኛል" በማለት እውነት ያልሆነ ምስክርነት ይሰጣሉ። ይህን ሲሉ እግዚአብሔር ስንፍናን የሚደግፍ አስመስለው ማቅረባቸው እንደሆነ ያወቁት ግን አይመስሉም። ሌላው ያልተረዱት ነገር ቢኖር፣ "አለን" የሚሉት ነገር፣ እንዲሁ የበቀለ ሳይሆን፣ የተጠጉት ሰው የለፋበት መሆኑን ነው። እነርሱ አይሥሩ እንጂ፣ ሌላው ሰው ለፍቶበታል። ምንም ሳይሠሩ፣ በሰዎች ተጠቅመው ባገኙት ፍሬ የሚታበዩ መሆናቸው የበለጠ ያሳዝናል። በራሳቸው ማፈር ሲገባቸው፣ በትጋት የሚሠራውን ሰው "እንዲሁ ትደክማለህ...." ብሎ መንቀፍ ሌላው የሚያስገርም ጠባያቸው ነው። እነዚህ ሁልጊዜ እንዲደረግላቸው ከሌሎች ሰዎች የሚጠብቁ፣ የሚፈልጉትን ለማግኘት፣ ሰው እንዲያዝንላቸው ራሳቸውን ምስኪን አድርገው ማቅረብ የሚያውቁበት ናቸው። ለራስ ቁጭ ብሎ በማዘን፣ የተጎዱ መስለው በመታየት፣ በአካባቢያቸው ያሉት ሰዎች ለጊዜው የእርዳታ እጃቸውን እንዲዘረጉላቸው ያድርግ እንጂ፣ ቀስ በቀስ ሁኔታቸውን ሰዎች እየተረዱ ሲመጡ እንደሚሸሿቸው የታወቀ ነው። ጊዜያዊ ዕርዳታ ማግኘታቸውን እንጂ፣ የሰው ሸክም መሆናቸውን ግን የተረዱት አይመስሉም። በሕይወታቸው የደረሰባቸውንም ሆነ፣ ያልደረሰባቸውን ክፉ ነገር ለሚሰማቸው ሰው ሁሉ እያስተዛዘኑ ያወራሉ። "...ባሌ ጨቁኖኝ፣...አስርቦኝ... ...ከለበስኩት ልብስ በስተቀር መቀየሪያ እንኳን የለኝም... የማደርገው ጫማ የተጣመመና የወለቀ ነው..." በማለት እሮሮአቸውን ያሰማሉ። ይህን የሚያደርጉት እነርሱ ሳይደክሙ፣ ሌሎች የደከሙበትን ነገር "በወርቅ ሳህን" ዕርዳታ ለመቀበል አስበው ነው። ቁሳቁሳዊ ነገር እንኳን ባይጠብቁም፣ የሞራል ድጋፍ እንዲያገኙ፣ ሰው እንዲያዝንላቸው፣ ከውስጥ ያልተረጋጋ ስሜታቸውን (insecurity) እንዲደግፉላቸው በማሰብ ነው።

እንደነዚህ ዓይነት ሰዎችን ለመርዳት በጣም ያስቸግራል። ሳያውቁት እግዚአብሔር የሰጣቸውን ችሎታ የሚጠራጠሩ የሥነ-ልቦና ሰንካላዎች ሆነዋል። እንዲህ ዓይነቶቹ ትዳር ይዘው እንደሆነ፣ ትዳራቸውን ለማቆም የራሳቸውን ኃላፊነት በመወጣት ፈንታ፣ ሁሉን ነገር ለኑሮ ጓደኛቸው ጥለው የሚኖሩ ናቸው። የሚያስደንቀው የኑሮ ጓደኛቸውን በማገዝ ፈንታ፣ ያ አንዱ ሰው የሁለት ሰው የሥራ ድርሻ ለመፈጸም እየታገለ፣ ምናልባት አንድ ነገር የጎደለ እንደሆነ፣ "ይሄ እንዲህ ሊሆን ያልቻለው እኔ ኃላፊነቴን ባለመወጣቴ ነው" በማለት ፈንታ "...ይሄ የለኝም...ያ የለኝም... ይሄ አልተሳካልኝም..." ብለው ሁልጊዜ እያጉረመረሙ የሚኖሩ መሆናቸው ነው። ለምሳሌ፣ "...እከሌ ለሚስቱ የሚገዛላትን ልብስና ጫማ አታይም... እኔ ከእርሷ ጋር ስታይ፣ ከገረድ እንኳን አንሳለሁ..." በማለት ባሏ "ማድረግ የሚገባኝን አላደረግሁም" በማለት የበደለኛነት ስሜት (guilt) እንዲያጠቃው ለማድረግ ትሞክራለች። የጠቀሰችው ሰው ያንን ማድረግ የቻለው እንዴት እንደሆነ ቢያውቅም፣ "መልስ ብሰጣት የበለጠ ሰላም ትነሳኛለች..." በማለት ነቀፋውን ሰምቶ ዝም ይላል። የሚያሳ

ውን ከሁለት አንዳቸው፥ ወይም ሁለቱም እየደበቁ የሚኖሩ ባልና ሚስቶች ሊሆኑ ይችላሉ። እንዲህ ዓይነቱ ባህሪያቸው ለጊዜው ችግራቸውን ያስወገደላቸው ይምስላቸው እንጂ፥ በውስጣቸው የሚያጠራቅሙት ቅሬታ ሲሞላ አንድ ቀን ፈንድቶ ሁለቱንም እንደሚጎዳቸው የታወቀ ነው። ጤናማ ለሆነ ቤተሰብ ግጭት (አለመስማማት) በመካከላቸው የሚፈጠርበት ምክንያት፥ አንዱ ሌላውን ለመጉዳት አስቦ የሚያደርገው ሳይሆን፥ ሁለቱም ወገን በምርጫ፥ በአሳብ ሁልጊዜ አንድ ዓይነት መሆን ስለማይችሉ ልዩነታቸው ሊያመጣ የሚችለው ሁኔታ ብቻ ነው። በጋብቻ አንድ መሆን "እንካ!... አምጣ!..." ወይም "መስጠትና መቀበል" ያለበት ሕይወት እንጂ፥ ሁልጊዜ የአንድ ሰው ፍላጎት ብቻ የሚጠበቅበት አይደለም።

በመሠረቱ ስው ቤቱ ከሌላ ሥፍራ የበለጠ ምቾት የሚያገኝበት፥ ከውጪ ያለውን ክፉ ነገር ሸሽቶ የሚጠለልበት፥ በሰላም የሚኖርበት፥ ሌላ ቦታ የማ ይናገረውን መናገር የሚችልበት፥ ሌላ ቦታ የማይጠይቀውን ጥያቄ የሚጠ ይቅበት ሥፍራ ነው። ጤናማ የሆነ ቤተሰብ፥ "ግጭት ያመጣ ይሆናል" ብሎ በመፍራት ስሜቱን በመደበቅ ፋንታ፥ የሚሰማውን ስሜት ያለፍርሃት በግ ልጽ ተናግሮ መፍትሄ ለማግኘት ይሞክራል። ቤተሰብ ውስጥ የሚፈጠረው አንዳንድ ግጭት ከቁጥጥር ከወጣ ግን፥ በቤተሰቡ ላይ ጉዳት ማድረሱ ብቻ ሳይሆን፥ በውጪ ከምናየው ግጭት በጣም የከፋ፥ ይኸውም መፈናከት፣ በጩቤ መዋጋት፣ በጥይት መታኮስ፣ ማጥፋትና መጥፋት ያስበት በጣም አደገኛ ሥፍራ ሊሆን ይችላል። የሚያስደንቀው ጠቡ፥ እርስ በርስ በጩቤ መዋጋቱና መፈነካከቱ የሚታየው ከማያውቁት ሰው ጋር ብቻ ሳይሆን፥ አንድ አካል በሆኑና በጣም ተቀራርበው በሚኖሩ ባልና ሚስት፥ እንዲሁም ከአብራካቸው ከወጡ ልጆቻቸው ጋር መሆኑ ነው። በቤተሰብ ውስጥ ብርቱ የሆነው ደካማውን በሥጋውም ሆነ በሥነ ልቦናው ላይ ጥቃት ማድረስ የለ በትም። በአካል ላይ የሚደርስው ጉዳት ቶሎ ይድናል። በስሜት ወይም በሥነ ልቦና ላይ የሚደርሰው ጉዳት ግን በዓይን የማይታይ ቢሆንም፥ ቁስሉ ወይም ጠባሳው ለረጅም ጊዜ ሊቆይ ይችላል። አንዳንድ አስቸጋሪ ሰዎች በቤተሰባቸው ውስጥ የሚፈጥሩት ችግር ከመጠን ያለፈ ሲሆን፥ ቤተ ሰቡ የግድ የፖሊስ፥ የፍርድ ቤት ዳኛን፥ ወይም የሥነ አዕምሮ ሊቃውንት ዕርዳታን መፈለግ እንዳለበት ግልጽ ነው።

የቤተሰብ ግጭት በጊዜው መስመር እንዲይዝ ካልተደረገ፥ ችግሩ የበለጠ እየከፋ ይሄዳል። የተጎዳው ሰው "ተጎዳሁ" ካላለ፥ ስሜቱን ውስጡ ደብቆ መኖር ከጀመረ፥ ከውጪ ሲታይ ሁሉም ነገር መልካም የሆነ፥ ሰላም ያለ ይምሰል እንጂ፥ ከሁለት አንዳቸው በውስጣቸው ቅሬታና መራራነት



እያጠ ራቀሙ በመሆናቸው፥ ቀደም ሲል እንደገለጽነው፥ አንድ ቀን ሞልቶ ሲፈስ ከከፋ ችግር ውስጥ ሁለቱንም ሊከታቸው እንደሚችል ማወቅ አለባቸው። የመራራነት መንፈስ ሥር ሳይሰድ ቶሎ በውይይት ካልተፈታ፥ ችግሩ በአ ጭሩ አይቆምም። ጥላቻና መራራነት በስው ልብ ውስጥ በቆየ ቁጥር ቁስሉ ያመረቅዝና፥ ሁለቱን ወገን ለማስታረቅ አስቸጋሪ የሚሆንበት ጊዜ አለ። ሐዋርያው ጳውሎስ ***"ምንም ያህል ብትቆጡ ኃጢአት አትሥሩ፤ ቁጣችሁም ሳይወገድ ጸሐይ አይጥለቅባችሁ"*** (ኤፌ. 4፥26) ያለው ለዚህ ነው። ይህንን ቃል በትክክል ባለመረዳት ብዙ ጉዳት ውስጥ ያለፉ ሰዎች አሉ። ጳውሎስ ይህን ሲል *"ለሰላም ስትሉ፥ አስቸጋሪ ለሆነው ሰው ሁልጊዜ እሺ በሉ፤.... እጃችሁን ስጡ...አስቸጋሪው ሰው ይረጋግጣችሁ፥ ወይም ጉዳት ሲያደርስባ ችሁ፥ ዝም በሉ..."* ማለቱ አይደለም። የእግዚአብሔር ዓላማና ፍላጎት፥ በቤ ተሰቡ ውስጥ አንዱ ብቻ በሰላም እንዲኖር፥ የአንዱ ፍላጎት ብቻ እንዲሟላ፥ ሌላው ግን እየተጨነቀ፥ ራሱን የመሆን መብት እየተነፈገው እንዲኖር አይ ደለም። የእግዚአብሔር ዓላማና ፈቃድ ሁሉም በእኩልነት ተስማምተው እን ዲኖሩ ነው። *"የእኔ ፍላጎት ብቻ ይጠበቅ፥ እኔ የምለው ብቻ ይሰማ፥ እኔን እስከተመቸኝ ድረስ ሌላው ባይመቸው ግድ የለኝም..."* የሚል ሰው አብሮት ለሚኖረው ሰው "አስቸጋሪ" ነው። ከእንዲህ ዓይነቱ ሰው ጋር መኖር ታዲያ የምንችለው እንዴት ነው? ለዚህ ጥያቄ መልስ ይሆናሉ ብለን ያመንባቸውን አንዳንድ አሳቦች በሚቀጥሉት ምዕራፎች ላይ በሰፊው ስለገለጽን በጥንቃቄ ይመልከቱ።

## 2. አብረውን ይሠራሉ

የሥራ ማጣት ችግር ጎልቶ በሚታይበት በአሁኑ ዘመን፥ ኑሮአቸውን የሚያሸንፉበት፥ ራሳቸውንና ቤተሰባቸውን የሚያስተዳድሩበት የገቢ ምንጭ ያላቸው ሰዎች ባላቸው የዕለት ሥራ ደስ ሊላቸው ሲገባ፥ ብዙዎች በሥራቸው ደስተኞች አይደሉም። በቅርቡ በተደረገው ጥናት፥ ከመቶ አርባ ስድስቱ (46%) አሜሪካውያን ሥራቸውን እንደሚጠሉ ተረጋግጧል። ጥዋት ከእንቅልፋቸው ነቅተው ወደ መሥሪያ ቤታቸው ለመሄድ ሲያስቡ፥ ውስጣቸው በጭንቀትና በፍርሃት ይሞላል። ምክንያታቸው ምን ይሆን? ምክንያታቸው የሚሠሩት የሥራ ዓይነት ሳይሆን፥ አብረዋቸው የሚሠሩት የሥራ ባልደረባዎቻቸው ወይም፥ የሥራ አለቆቻቸው "አስቸጋሪ ሰዎች" ስለሆኑባቸው እንደሆነ፥ ጥናቱ ያረጋግጣል።

ለይ በአገራችን በኃላፊነት ወይም በሥልጣን ላይ ያሉ አንዳንድ ሰዎች የሚጠቀሙበት፥ ውጤታማ ነው ብለው የተቀበሉት የአመራር ሥልት አለ። ያም ሠራተኛውን በማስፈራራትና በማስደንገጥ (Management by Terror) ማስተዳደር ነው። ይህን ዓይነት የአመራር ሥልት ይጠቀሙበት ከነበሩት ሰዎች መካከል አንደኛው የንግድ ሥራ ትምህርት ቤት ዋና ድሬክተር የነበሩት ሰው ናቸው። እኚህ ድሬክተር ሰው ሁሉ እንዲፈራቸውና እንዲንቀጠቀጥላቸው የሚያደርጉበት የራሳቸው የሆነ መንገድ የነበራቸው ሰው ነበሩ። ስምንት ዓመት አብሬአቸው ስለ ሠራሁ በደንብ አውቃቸዋለሁ። በተፈጥሮዬ በራሴ የምተማመን ሰው ብሆንም፥ በዕድሜ ገና ልጅ ስለነበርኩ ቢሮአቸው ጠርተውኝ ከፊታቸው ስቆም የምፈራበት ምክንያት ባይኖረኝም እንዲሁ በጣም እፈራና እደነግጥ ነበር። ሌላው ቀርቶ በስልክ እንኳን ድምጻቸውን ስሰማ፥ ምንም ያጠፋሁት ነገር ባይኖርም፥ እንዲሁ እደነግጥ ነበር። የፈራሁት ልጅ በመሆኔ ነው ብዬ እንዳልል፥ ከእኔ በዕድሜ ብዙ የሚበልጡና ብዙ ዓመት የሠሩትም ሲፈሯቸውና ሲንቀጠቀጡላቸው አይ ነበር። "ለምን እንደዚህ እፈራቸዋለሁ?" በማለት ራሴን ብዙ ጊዜ የታዘብኩበት ጊዜ ነበር። ወደ ሥራ ለመሄድ ጥዋት ከዕንቅልፌ ስነሳ ወደ አዕምሮዬ እየመጡ ደስታ እንዲሸሸኝ ከሚያደርጉኝ ሰዎች መካከል አንደኛው እኚህ ሰው ነበሩ።

ለረጅም ጊዜ በድሬክተርነት ስላገለገሉ፥ ተማሪ በነበርኩበት ዘመን ስለማውቃቸውና እንደ እኔ ዓይነት ትንሽ ልጅ ቢፈራቸውና ቢንቀጠቀጥላቸው ምንም አይደለም። የሚደንቀው ግን በዕድሜ የገፉትም ሰዎች ቢሮአቸው ሲሄዱ በፍርሃት የሚንቀጠቀጡ መሆናቸው ነው። እኚህ ድሬክተር ሰው ሁሉ እንደሚፈራቸው ያውቁታል። ይሁን እንጂ እርሳቸውን ስለጠቀማቸው "እኔ ጅብ አይደለሁምI ለምን ትፈሩኛላችሁ?" በማለት ሰውን እንዲዝናና አያደርጉትም። እንዲያውም በመፈራታቸው ደስ የሚላቸው ይመስላሉ። አንድ የማልረሳው ትዝታ አለኝ። ከእኔ በፊት አስተዳዳሪ የነበሩት ሰው በዕድሜ የበሰሉ፥ በሰውነታቸው በጣም ተለቅ ያሉ ሰው ነበሩ። እኚህ ሰው ወደ ድሬክተሩ ቢሮ ተጠርተው ሲሄዱ እየፈሩና እየተንቀጠቀጡ ነበር። ድሬክተሩ የበለጠ እንዲፈሩና እንዲከበሩ ለማድረግ ይመስላል፥ እኛ ሰው ቢሮአቸው ሲመጡ "ቁጭ በል" ሳይሏቸው ሁለት ሰዓት ሙሉ እግራቸውና ወገባቸው እስኪንቀጠቀጥባቸው ድረስ ያስቆሟቸው ነበር። እኛ ሰው ወንበር ስበው ቢቀ መጡ "ተነስ!" ብለው እንደማያስነሷቸው እርግጠኛ ነኝ። ይሁን እንጂ ከፍርሃታቸው የተነሳ "ተቀመጥ" ሳይሉኝ እንዴት እቀመጣለሁ?" በማለት ብቻ ለመቀመጥ ድፍረት አልነበራቸውም።



እኚህ ድሬክተር በወቅቱ ለብዙዎች ሠራተኞች አስቸጋሪ አለቃ ነበሩ። በእርሳቸው አካባቢ ሰው ተዝናንቶ ያለፍርሃት መኖር አይችልም። እንደ እርሳቸው ዓይነት ሠራተኛውን በማሸቆጥቆጥ የሚያምን፥ የራሱን ድካም ወደ ሌላው ለመግፋት የሚሞክር አለቃ የሚወረውረው የሰድብ ቃል፥ ወይም ስለ ሠራተኛው የሚሰጠው አስተያየት ወደ ውስጣችን ገብቶ እንዳይጎዳን የምንከላከልበት መንገድ፥ ድፍረት ሳናጣ፥ ጤናማ የሆነ አስተያየት ወይም ሥርዓቱን ያልለቀቀ መልስ በመስጠት ነው። ሥርዓት ያለው መልሰ መስጠት በቁጣ ተሞልቶ ክፉ ቃል የሚሰነዝረውን አለቃ ሲገታ አይቻለሁ። አንድ ቀን አንዱን በቅርቡ የተቀጠረ አዲስ አስተማሪ እኚሁ ድሬክተር ቢሮአቸው ጠርተው በቁጣና በንዴት ተሞልተው "አንተንና ጓደኞችህን በመቅጠሬ የራስ ምታት አተረፍኩኝ" አሉት። እኚህ ሰው በዚህ ዓይነት ሁኔታ አዲሱን አስተማሪ ማስደንገጥ የፈለጉት ምናልባት "እንዳትደፍረኝ! እዚህ ግቢ እኔ አምላክህ ነኝ!" በማለት ኃይላቸውንና ሥልጣናቸውን እንዳይንቅ ለማድረግ ይሆናል። ወይም ሌላ ምክንያት ይኖራቸዋል! ያም ሆነ ይህ፥ ያ አዲስ አስተማሪ እርሳቸው እንዳሰቡትና እንደጠበቁት አልደነገጠላቸውም። ምንም ዓይነት ድንጋጤና ፍርሃት ሳያሳይ፥ *"ራስ ምታት ከሆነብዎት፥ ሊያሰናብቱን ይችላሉ እኮ!..."* አላቸው። ስምንት ዓመት በቆየሁበት ጊዜ ውስጥ ይህን ዓይነት መልሰ ደፍሮ ለእኚህ ድሬክተር ሲሰጥ ያየሁት ደፋር ሰው ቢኖር ያ ወጣት አስተማሪ ብቻ ሳይሆን አይቀርም። እርሳቸውም የሰጣቸው መልስ አበሳጭቷቸው የበለጠ በመቆጣትና በዚያ አስተማሪ ላይ ሌላ እርምጃ በመውሰድ ፈንታ፥ ከዚያን ቀን ጀምሮ ትምህርት ቤቱን ለቅቆ እስከ ሄደበት ጊዜ ድረስ ያንን አስተማሪ ያከብሩት ነበር።

ያ ወጣት አስተማሪ ለድሬክተሩ የሰጣቸው መልስ ሥርዓት በለቀቀ ሁኔታ፥ ጨዋነት በጎደለው መልክ አልነበረም። እንደ ትምህርት ቤቱ ባለሥልጣን የሚገባቸውን አክብሮት አልነፈጋቸውም። ይሁን እንጂ፥ እንደ አስተማሪ የሚገባውን ክብር እንዲከለክሉት ደግሞ አልፈቀደላቸውም። ያንንም እንዲያውቁ ያደረገው ተቆጥቶ በመናገር ሳይሆን፥ ጨዋነት ባልጎደለው መልክ ተገቢውን መልስ በመስጠት ነው። ብዙ ሰዎች ሥርዓት በለቀቀ መንገድ የሚናገሯቸውን፥ የሰድብ ቃል የሚወረውሩባቸውን አለቆቻቸው አስፈላጊውን መልስ በመስጠት ፈንታ የሚያስተናግዱቸው በፊታቸው በፍርሃት በመንቀጥቀጥ ነው። ይሄን ዓይነት ባሕሪያቸው፥ አስቸጋሪ ባሕሪ ያላቸውን አለቆቻቸውን አይለውጥም። እንዲህ ዓይነት አስቸጋሪ አለቃ ያላቸው ሰዎች ዘወትር ወደ መሥሪያ ቤታቸው ለመሄድ ሲያስቡ ሁልጊዜ ውስጣቸው በጭንቀት የተሞላ

# ፭

# ሰዎች ግጭታቸውን የሚፈቱት እንዴት ነው?

- *"...ባል ሚስቱን በሽጉጥ መትቷት የሞተች ስለ መሰለው፥ ራሱን ገደለ። ሚስቱም በአስጊ ሁኔታ ላይ ትገኛለች።"*
- *"...የ18 ዓመት ወጣት በወላጆቹ ተቆጥቶ፥ ቤታቸውን በእሳት አቃጠለው። ወላጆቹም በእሳቱ ተቃጥለው ሞቱ።"*
- *"... አንድ አባት የ8 ወር ልጁ እያለቀሰ ሲያስቸግረው፥ ልጁን ወርውሮ ከግድግዳ ጋር አጋጭቶ ገደለው።"*

በምዕራቡ ዓለም ውስጥ የዕለቱን የጋዜጣ አምዶች የሞሉት፥ የቴሌቪዥኑንና የሬዲዮኑን ፕሮግራሞች ያጣበቡት፥ ከላይ ያየናቸውን ዓይነት ዜናዎች ናቸው። እነዚህ ለሰሚው በጣም የሚዘገንኑና አሳዛኝ የሆኑ ወንጀሎች፥ በሰዎች መካከል በተፈጠሩ ግጭቶች (conflicts) ምክንያት የደረሱ ናቸው። እነዚህ ወንጀሎች፥ በስሜታቸው መጎዳት ምክንያት የደረሰባቸውን ግጭት ሥርዓት ባለው መንገድ መፍታት ያቃታቸው፥ በጥላቻ መንፈስ የተሞሉ አንዳንድ ሰዎች የሚፈጽሟቸው ናቸው። ከውስጣቸው የሚሰማቸውን የስሜት ጉዳት መታገስ አቅቷቸው፥ አጥፊ በሆነ መንገድ ጎዳን በሚሉት ሰው ላይ አጸፋውን ለመመለስ የሚነሳሱ ሰዎች፥ ከምንጊዜውም የበለጠ ቁጥራቸው የበዛበት ዘመን ቢኖር፥ ይሄ እኛ ያለንበት ዘመን እንደሆነ ግልጽ ነው። ይሄን ዓይነቱ ችግር ያለው በምዕራቡ ዓለም ውስጥ ብቻ ሳይሆን፥ በዓለም ዙሪያ የሚታይ "ወረርሽኝ በሽታ" (epidemic) ነው። የግጭቱ ጥልቀትና ስፋት ይለያይ እንጂ፥ ከግጭት ነጻ የሆነ ሰውም ሆነ አካባቢ የለም።

## 1. ከግጭት ነጻ የሆነ ሰው የለም

ከላይ እንደ ምሳሌ የጠቀስናቸውን ግጭቶችን የመሳሰሉ አይሁኑ እንጂ፥ ከጥዋት እስከ ማታ ድረስ የእኛን ውሳኔ የሚጠይቅ የተለያየ ዓይነት ግጭት ሁላችንም በየጊዜው ያጋጥመናል። ጥዋት ገና ከዕንቅልፋችን ስንነቃ፥ "ልነሳ ወይስ ትንሽ ልተኛ?" ብለን ከራሳችን ጋር ሙግት የምንገጥምበት ጊዜ አለ። በአንድ በኩል ተኝቶ ማርፈዱ ደስ ሲለን፥ በሌላ በኩል ደግሞ ተነስተን ወደ ሥራችን ካልሄድን ሥራችንን የምናጣ መሆናችንን እናውቃለን። "መነሳት... ወይም አለመነሳት..." በሚለው ሁለት የተለያዩ ምርጫዎች ምክንያት በውስጣችን ትግል ይፈጠራል። ይሄ ቀላል ጉዳይ ቢሆንም፥ በውስጣችን መለስተኛ የሆነ ግጭትን ሊፈጠር እንደሚችል የታወቀ ነው። በዚህ ዓይነት ሰው በራሱ የግል ህይወት ውስጥ ሁለት ዓይነት ምርጫዎች ወይም አሳቦች ይኖሩና በውስጡ ከፍተኛ ግጭት ሊፈጠር እንደሚችል ግልጽ ነው። በዚህ ዓይነት ቀኑን ሙሉ ትላልቅ፥ መለስተኛና እንዲሁም ጥቃቅን የሆኑ ግጭቶች ሊያጋጥሙን ይችላሉ። አንዳንዶቹ በመጠኑ አዕምሮንና ስሜትን የሚጠይቁ ሲሆኑ፥ አንዳንዶቹ ደግሞ ጨጓራን እስከ መላጥ ሊያደርሱ እንደሚችሉ የታወቀ ነው። ማናችንም ብንሆን፥ ከማን ጋር፥ ወይም እንዴት መጋጨት እንዳለብን ቁጭ ብለን ዕቅድ አውጥተን እንደማንጋጭ የታወቀ ነው። ለምሳሌ፥ *"ዛሬ በዚህ ሰዓትና በዚህ ሁኔታ ከኑሮ ጓደኛዬ ጋር እጣላለሁ"* ብለን ፕሮግራም አናወጣም። ምክንያቱም ማንም ግጭትን፥ ጠብን፥ ወይም ጠርነትን ሆን ብሎ የሚፈልግ ሰው ስለሌለ ነው። ይሁን እንጂ በዓለም ውስጥ በሕይወት እስከ ኖርን ድረስ ከግጭት ነጻ ሆነን መኖር እንደማንችል እናውቃለን። "ዛሬ ጥሩ ቀን ነው" የምንለው፥ ምንም ዓይነት ግጭት ሳይደርስብን በሰላም የምናልፍበት ቀን ይሆን? ይህ ከሆነ ለመሆኑ ፍጹም ባልሆነ ዓለም ውስጥ ፍጹም የሆነ ቀን ሊኖር ይችል ይሆን?

ወደድንም ጠላንም፥ ክርስቲያኖች ብንሆንም ባንሆንም፥ ምን ጊዜም ቢሆን ከግጭት ነጻ ሆነን መኖር አንችልም። አንዳንዶቻችን ግጭት ሲገጥመን፥ ግጭቱ እንዳልተፈጠረ አድርገን ችላ ብለነው ለማለፍ እንሞክራለን። ይሁን እንጂ፥

ንዴት ደብቀው፥ ከውጪ ፈገግታ በማሳየት ምንም ዓይነት ችግር በመካከላቸው እንደሌለ የሚያስመስሉበት ጊዜ አለ። ውስጣቸው ግን ያልተፈወሰ፥ በመራራነትና በቅሬታ መንፈስ የተሞላ እንደሆነ ግልጽ ነው። ዝም በመባባላቸው ለጊዜው ቁጣቸውን ያበረዱ ሊመስላቸው ይችላል። ለችግራቸው መፍትሄ ለመፈለግ በመወያየት ፈንታ ስሜታቸውን በውስጣቸው ቀብረው ሲያስቀሩት፥ ቀስ በቀስ መራራነት በውስጣቸው እየበቀለና እያደገ እንደሚመጣና እንዲሁም ጊዜ ጠብቆ አንድ ቀን ሲፈነዳ፥ ሁለቱንም ወገን ሊጎዳ እንደሚችል የተረዱት አይመስሉም። እንዳንዶቻችን አንድ ዓይነት ቅሬታ በሌላው ሰው ላይ ሲኖረን፥ ቅር ያሰኘንን ሰው ፊት ለፊት መናገር ወይም መውቀስ ስለምንፈራ፥ ጉዳታችንን በውስጣችን ደብቀን ማስቀመጥ ልማዳችን አድርገነዋል። እንዲህ ዓይነት ባህሪ ሊኖረን የቻለበት ምክንያት ምን ይሆን? ከእደግንበት ሕብረተሰብ እምነት የመጣ ሊሆን ይችላል። ኢትዮጵያ ውስጥ ተወልደው ያደጉ ልጆች ምንም ያህል ጉዳት ቢደርስባቸው፥ ጉዳታቸውን ገልጸው እንዲናገሩ ምንም ዓይነት ነጻነት አይሰጣቸውም። ያላጠፉትን እንኳን "አጥፍታችኋል" ሲባሉ፥ "ለአዋቂ መልስ መስጠት ትክክል አይደለም" ስለሚባል፥ "አላጠፋሁም" ብለው ምክንያታቸውን እንዲገልጹ ዕድል አይሰጣቸውም። ያላቸው ምርጫ ዝም ማለት ብቻ ነው። ይሄ ሁኔታ ካደጉም በኋላ ተከትሏቸው ስለሚመጣ፥ የበደላቸውን ሰው "በደልከኝ! ጎዳኸኝ!" ብለው በመናገር ፈንታ፥ ጉዳታቸውን ችለው ዝም ማለቱን ይመርጣሉ። የሚያሳዝነው፥ ችግራችንን ለበደለን ወይም ላስቀየመን ሰው ለመንገር ድፍረት አይኑረን እንጂ፥ ጉዳታችንን አካባቢያችን ላሉት ሰዎች፥ ነገሩ ለማይመለከታቸው ሁሉ ነጻነት ተሰምቶን ማውራታችን አይቀርም። ከሌሎች ሰዎች ጋር ነጻ ሆነን በማውራታችን ችግራችንን ያቃለልን መስሎ ሊሰማን ይችላል። ይሁን እንጂ፥ ችግሩ ከሚመለከተው ሰው ጋር ለመወያየት ፈቃደኞች እስካልሆንን ድረስ፥ ችግራችንን ለጊዜው ደበቅነው እንጂ፥ እውነተኛ መፍትሄ አልሰጠነውም። ከሌላው ሰው ጋር ያጋጠመንን ችግር ገልጸ ለመወያየት አስቸጋሪየሚሆንብን ሌላው ምክንያት፥ ልናነጋግረው የምናስበው ሰው አስቸጋሪ፥ በቀላሉ በንዴት የሚገነፍል፥ ከሰላም ይልቅ ጠብ የሚቀናው ሰው መሆኑን ስለምናውቅ ይሆናል። ይሁን እንጂ፥ አለመስማማታችንን መደበቅ፥ ከሁኔታው መሸሽ ግጭታችንን የምንፈታበት ጤናማ የሆነ መንገድ አይደለም።

በግልጽ ከመወያየት ይልቅ ሁልጊዜ መሸሽ የሚያመጣው ጉዳት ከፍተኛ እንደሚሆን ግልጽ ነው። የእኛ መሸሽ፥ አስቸጋሪ የሆኑትን ሰዎች አይለውጣቸውም። ሁልጊዜ በአካል ወይም በውስጠ አዕምሮአችን ከሁኔታው የምንሸሽ ከሆነ፥ ሌሎች ያለንን ሀሳብና የሚሰማንን ስሜት ማወቅ ያቅታቸዋል። በጉዳዩ ላይ ምን ዓይነት አቋም እንዳለን አይታወቅም። የራሳችን ፍላጎት ሊሟላልን ስላልቻለ ብቻ የምንሸሽ መስለን ልንታይ እንችላለን። የማንወደውን ነገር "አልወደውምI ትክክል አይደለም" ለማለት ፈርተን ዝም ማለታችን ራሳችንን እንድንጠላና እንድንታዘብ ያደርገናል። "አልረባም! ፈሪ ነኝ! ስረገጥ 'ተረገጥኩ' ለማለት እንኳን ድፍረት የሌለኝ ሰው ነኝ" በማለት ራሳችንን መጥላት እንጀምራለን። ሌላው ደግሞ "ግጭት ያመጣብኛል" ብለን በመፍራት ዝም ስንል፥ አንድ ቀን ያልጠበቅነው ክፉ ነገር በህይወታችን ሊደርስብን ይችላል። በተጨማሪ "አስቸጋሪ" ለሆነብን ሰው የፈቀደውን ነገር በእኛ ላይ እንዲያደርግ ነጻነት መስጠታችን ይሆናል። ይሄም መከራችንን (ችግራችንን) ያብሰዋል እንጂ አይቀንሰውም። በየቤቱ ስንቱ ይሆን ችግሩን ዋጥ አድርጎ ሁሉም ነገር ሰላም የሆነ እስመስሎ የሚኖር? የሽሽት ኑሮ ለአንዱ ብቻ፥ ያውም አስቸጋሪ ለሆነው ሰው የፈለገውን እንዲያደርግ ዕድል ይሰጠዋል እንጂ፥ ለተቸገረው ሰው ዘላቂ የሆነ መፍትሄ አያስገኝለትም።

ኬን ሳንዲ (Ken Sande) የተባሉ ጸሐፊ፥ ሰው ግጭት ሲያጋጥመው ከሚወስዳቸው ሦስት ዓይነት እርምጃዎች ውስጥ አንድኛው "መሸሽ" (Escape) እንደሆነ ጠቅሰዋል።[13] ሰዎች ግጭት ሲያጋጥማቸው፥ ላጋጠማቸው ግጭት መፍትሄ በመፈለግ ፈንታ፥ በተለይ በክርስቲያኖች መካከል ወይም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከሁኔታው መሸሽን ይመርጣሉ። የዚህ ትልቁ ምክንያት ማንኛውም ዓይነት ግጭት ትክክል አይደለም፥ ወይም አደገኛ ነው ብለው ስለሚያምኑ ነው። ክርስቲያኖች ሁልጊዜ መስማማት አለባቸው፥ ወይም ግጭት ያላቸውን ግንኙነት ያበላሻል ብለው ስለሚፈሩ ነው። ስለ ግጭት ከላይ እንደ ገለጽነው የተሳሳተ እምነት ስላላቸው፥ ግጭት ሲያጋጥማቸው ግጭቱን የሚያስወግዱበት የራሳቸው መንገድ አላቸው። ይኸውም፥

- *አንደኛ፥ ክህደት (Denial) ነው – ግጭትን ለማስወገድ የሚሞክሩበት አንደኛው መንገድ፥ ግጭት እንደሌለ አድርጎ ማመን ነው። በአግባቡ ለግጭቱ መፍትሄ አይፈልጉለትም። "ግጭቱ የለም" ብለው በመካዳቸው፥ ለጊዜው ግጭቱን በመሸፈናቸው ምክንያት ግልጽ ሆኖ አይታይ እንጂ፥ ዘለቄታ ያለው መፍትሄ አያስገኝላቸውም።*
- *ሁለተኛ፥ ሽሽት (Flight) ነው – ግጭትን የሚያስወግዱበት ሌላው መንገዳቸው ሸሽቶ መሮጥ ነው። ይኸውም ከተጣሉት ሰው ጋር ያላቸውን ግንኙነት ማቋረጥ፥ ሥራን ጥሎ መሄድ፥ ጋብቻን ማፍረስ ወይም ቤተ ክርስቲያን መቀየር ይሆናል። ፈጽሞ ሊስተካከል ወይም ሊታረቅ በማይቻልበት ሁኔታ ላይ ሽሽት አስፈላጊ ሆኖ የሚገኝበት ጊዜ አለ።*

---

[13] Sande, Ken. The Peacemaker. Baker Books, Grand Rapids, MI c1991.

*ንም። አንዳንድ ሰዎች ወደ ማጥቃቱ የሚሄዱት ልክ ግጭት እንዳጋጠማቸው ሲሆን፥ ሌሎች ደግሞ ግጭታቸውን በሌላ መንገድ መፍታት የማይችሉ ሲመስላቸው ነው። ከዚህ በኋላ ግጭታቸውን በምንም ዓይነት ችላ ብለው ማለፍ፥ መሸሽ፥ ወይም መሸፈን እንደማይችሉ ሲያውቁ፥ በማጥቃት ግጭታቸውን ለመፍታት ይሞክራሉ።*

ሁልጊዜ "ማሸነፍ አለብኝ" የሚሉ ሰዎች ትኩረት የሚያደርጉት በራሳቸው ላይ ብቻ ነው። አሸናፊዎች ካልሆኑ፥ እንኳን ሰው እግዚአብሔርም የሚቀበላቸው አይመስላቸውም። "ሁልጊዜ ትክክል መሆን አለብኝ" ብለው ያምናሉ። እንዲህ ዓይነቶቹ ግጭትን መሰመር ለማስያዝ የሚመርጡት መንገድ "ሁል ጊዜ በማሸነፍ" ነው። "ዝም አልልም፤ ወደ ኋላ አላፈገፍግም፤ ትንሽም ብትሆን የራሴን አላስነካም" የሚሉ ናቸው። የሚፈልጉትን ካላገኙ፥ ሁልጊዜ ካላሸነፉ ሰላም አይኖራቸውም። ለሌላውም ሰላም አይሰጡም። ዓላማቸው ሁልጊዜ ማሸነፍ ስለሆነ፥ የሌላው ሰው አሳብ ከነርሱ ይበልጣል ብለው በምንም ዓይነት አምነው አይቀበሉም። የአሳብ ልዩነት ተፈጥሮ ውይይት ሲያደርጉ ሁልጊዜ እነርሱ ማሸነፍ አለባቸው። በአሳባቸው የማይስማማ ሰው ቢኖር፥ ከፍተኛ ጦርነት ያካሂዱበታል። ሁልጊዜ ማሸነፍ ስለሚፈልጉ በንግግራቸውና በቁጣቸው ብዙዎቹን ያሰቀይማሉ። የሌላውን አሳብ ለመቀበል አዕምሮአቸው በመዘጋቱ፥ እነርሱን ተናግሮ ማሳመን ስለማይቻል፥ ውይይቱን ማራዘም ጥቅም የለውም። በማንኛውም አለመስማማት ውስጥ አሸናፊና ተሸናፊ አለ። የእነዚህን አስቸጋሪ ሰዎች ፈቃድ ለመፈጸም "እምቢ!" የሚል ሰው ከፍተኛ ጦርነት ይገጥመዋል። አስቸጋሪ ሰዎች፥ በመካከላቸው አለመስማማት ሲፈጠር የሚች ሰው በሌላ ምክንያት ሳይሆን፥ የእነርሱን ትክክለኛ አሳብ ሰዎች መረዳት ስለሚያቅታቸው ነው ብለው ያምናሉ። ትኩረታቸው ማሸነፍ ላይ ስለሆነ፥ የሚፈልጉትን ለማግኘት የማያደርጉት ነገር የለም። ለውይይት ፈቃደኛ ቢሆኑም እንኳን ውይይቱን ሊመሩ የሚፈልጉት በእነርሱ አሳብ ዙሪያ እንጂ፥ ትክክል በሆነው ነገር ላይ አይደለም።

ታፈሰና እመቤት አንድ ቀን ከአንድ ወዳጆቻቸው ቤት ራት ተጋብዘው፥ ጥሩ ምሽት አሳልፈው ሲመለሱ፥ ከልጆቹ መካከል አንደኛው አባቱን "አባባ አይስ ክሬም እፈልጋለሁ" አለ። ታፈሰም "ጠግበህ ከበላህ በኋላ አይስ ክሬም ተሰጥቶህ በልተህ የለም እንዴ! እንዴት ለሁለተኛ ጊዜ አይስ ክሬም ብለህ ትጠይቃለህ" አለው። በዚህ ወቅት እመቤት ጣልቃ ትገባና፥ "የጠየቀውን ግዛለት" ትለዋለች። ታፈሰም "የለም በልቷል! አልገዛለትም" አለ። እዚህ ላይ ታፈሰና እመቤት የተለያየ አሳብ እንደነበራቸው በግልጽ ይታያል። ታፈሰ "አይሆንም" በማለቱ፥ እርሷ ያለችው ባለመሆኑ ተበሳጭታ፥ መኪናውን ይነዳ የነበረው ታፈሰ ስለነበረ፥ "አንተ እምቢ ካልክ እኔ እገዛለታለሁና ወደ አይስክሬም ሱቅ ንዳ" አለችው። ታፈሰም "አይሆንም ያልኩት ገንዘብ ስለሌለኝ ሳይሆን፥ አሁን በልቶ ወጥቶ እንደገና ይገዛልኝ እንዴት ይላል በማለት ትምህርት እንዲሆነው ብዬ ነው" ይላታል። በዚህን ጊዜ እመቤት ተቆጥታ "እርሱ የራስህ ጉዳይ ነው! ውሰደኝ ብዬሃለሁ፤ የማትወስደኝ እንደሆነ ዋ!" አለችው። እመቤት በተፈጥሮዋ ሁልጊዜ "በማሸነፍ" የምታምን ነች። የምትፈልገውን ነገር ካላገኘች፥ ዓለም ይገለባበጣል እንጂ፥ በቀላሉ አትተውም። ታፈሰ ብዙ ጊዜ ለሰላም ሲል "እሺ!" እያለ እጁን ይሰጣል። በዛን ዕለት ግን ምን እንደነካው አይታወቅም፥ "አይሆንም" ብሎ ቀጥ ብሎ ይዟቸው ወደ ቤት ሄደ።

ሁልጊዜ "በማሸነፍ" የምታምነዋ እመቤት፥ በዚያን ዕለት ባለማሸነፏ፥ እንደምትፈልገው ስላልሆነላት፥ ታፈሰ "ሁለተኛ አይለምደኝም! የጠየቅሽውንና የፈለግሽውን ሁሉ አደርጋለሁ" እስከሚል ድረስ በከፋ ሁኔታ ተበቀለችው። እየተሳደበችና እየተመናጨቀች መኝታ ቤት ገብታ ከውስጥ ቆለፈችበትና ሳሎን ሶፋ ላይ እንዲተኛ አደረገችው። ሁለት ሳምንት ሙሉ አኮረፈችው። "ሁልጊዜ ማሸነፍ አለብኝ" የሚሉ ሰዎች ከሌሎች ሰዎች ጋር ያላቸውን ግንኙነት እንደሚያበላሽባቸው፥ ለሌላው ሰው "አስቸጋሪዎች" እንደሚያደርጋቸው የሚገነዘቡት አይመስሉም። እንደነዚህ ዓይነት ሰዎች የሚፈልጉትን ለማግኘት ልዩ ልዩ ዘዴዎችን ይጠቀማሉ። በማባበል፥ በማግባባት፥ በማልቀስና በማኩረፍ፥ ካልሆነላቸው ደግሞ ባላቸው ኃይል በመጠቀም የሚፈልጉትን ሁሉ ለማግኘት ይሞክራሉ። ከሰው ጋር የሚኖራቸውን ግንኙነት እንደሚያበላሽባቸው ግን አይገነዘቡትም። ሁልጊዜ "ማሸነፍ አለብኝ" የሚል አቋም መያዝ፥ ግንኙነትን እንደሚያሻክር፥ ኅብረትን እንደሚያፈርስ፥ ጥርጣሬንና አለመተማመንን እንደሚፈጥር ብዙዎች የተረዱት አይመስሉም። እርግጥ ነው "ማሸነፍ አለብኝ" የሚለውን አቋም መያዝ የሚያስፈልግበት ጊዜ አለ። ይኸውም፥

*(1) በጣም ዋናና እንዲሁም አስፈላጊ የሆኑ ውሳኔዎችን እንዲሁም፥ በጣም አስቸጋሪ የሆኑ ውሳኔዎችን በምንወስንበት ወቅት፥*

*(2) ትክክለኛው የእኛ ውሳኔ (አሳብ) መሆኑን መቶ በመቶ እርግጠኞች ስንሆን፥*

*(3) ውሳኔ ለመወሰንና የተወሰነውን ውሳኔ በሥራ ላይ ለማዋል ሙሉ ስልጣን ሲኖረን፥ እንዲሁም*

*(4) ሌሎችን መንገዶች ሁሉ ተጠቅመን ከውሳኔ መድረስ ሲያቅተን ይህንን መንገድ መጠቀም እንችላለን።*

ያላቸው ከብቶች እንዲሰጠኝ እመኛለሁ" አለ። የመጀመሪያው ሰው ወንድሙ የተመኘውን ሲሰማ፣ "ይህን ያህል ብዛት ያላቸው ከብቶች እግዚአብሔር እንዲሰጥህ የተመኘኸው ምን ልትመግባቸው ነው?" ብሎ ጠየቀው። ለተጠየቀው ጥያቄ መልስ ሲሰጥ፣ "ሣር እንዲግጡ ወደ አንተ መሰክ ከብቶቼን እልካቸዋለሁ" አለው። ወንድምየውም ይህን ሲሰማ ተናዶ፣ "ምቼ ነው ቆሜ ያንተ ከብቶች እኔ መሰክ ገብተው የሚግጡት" አለው። በዚህ ምክንያት በመካከላቸው ከፍተኛ ጭቅጭቅና ጠብ ተነስቶ አንደኛው ሌላውን ወንድሙን ገደለው። ምሳሌው ተረት ይምሰል እንጂ፣ ብዙዎች እርስ በርሳቸው የሚጋጩበት ምክንያት ምን ያህል ደካማ እንደሆነ ያሳያል።

አንዳንድ ግጭቶች በምንም ዓይነት ሊወገዱ አይችሉም። ግጭቱ እንዳይፈጠር ምንም ያህል ብንጥር፣ ሁላችንም የተለያየ ምርጫና ፍላጎት ያለን በመሆናችን፣ ፍላጎታችን ከሌላው ሰው ፍላጎት ጋር የማይስማማ ከሆነ፣ መጋጨታችን አይቀርም። በህይወታችን ምንም ያህል ግልጽ የሆነ ዓላማና መመሪያ ያለን ብንሆንም፣ ዓላማችንን ከግቡ ለማድረስ ስንታገል፣ በመንገዳችን ላይ አንዳንድ እንቅፋቶች ሊያጋጥሙን ይችላሉ። ከሌላው ሰው አንድ ነገር በጠየቅን ቁጥር እምቢ ከተባልን፣ ወይም ሌላው ሰው እኛን አንድ ነገር በጠየቀን ቁጥር፣ መልሳችን "እምቢ!" የሚል ከሆነ፣ ፍላጎቱ ባልተሟላለት ሰው ምክንያት በመካከላችን ግጭት ሊፈጠር እንደሚችል ግልጽ ነው። ችግራችን ማናችንም "እሺ!" እንጂ "እምቢ!" መባልን ስለማንፈልግ ነው። ግጭትን ማስወገድ የማንችለው ከሆነ፣ ግጭታችንን (አለመስማማታችንን) በአግባቡ መያዝ ወይም መጠቀም የምንችልበት መንገድ ምን ይሆን? ብለን መጠየቃችን አይቀርም። ከማንኛችውም ዓይነት ግጭት ነጻ ሆኖ የኖረ ወይም የሚኖር ሰው የለም። ሁላችንም ነፍስ ካወቅንበት፣ ማለትም ከልጅነታችን ዘመን ጀምሮ፣ አሁን እስከደረስንበት ዕድሜ ድረስ፣ በተለያዩ ግጭቶች ውስጥ አልፈናል። አልፈን የመጣንበትን ሕይወት ወደ ኋላ መለስ ብለን ስንመለከት፣ ብዙዎቹን በቀላሉ ያለፍናቸው ሲሆኑ፣ አንዳንዶቹ ግን መራራና ሥር ነቀል የሆነ ለውጥ በሕይወታችን ያስከተሉብን ግጭቶች እንደ ነበሩ እናስታውሳለን። በአንዳንዶቹ ግጭቶች ውስጥ ብርቱዎች ሆነን በመገኘታችን አሸናፊዎች አንሁን እንጂ፣ ከሌሎች ጋር ያለንን ግንኙነት እንዳሻከሩብንና ፍጹም የሆነ መራራቅን እንዳስከተሉብን እናውቃለን። "ችላ ብንላቸው በራሳቸው ይጠፋሉ" ብለን በማሰብ አልፎ አልፎ ንቀን ያለፍናቸውም ግጭቶች አሉ። ከነዚህ ውስጥ እርግጥ ነው ችላ ስንላቸው አውቀው የጠፉም አንዳንድ ግጭቶች እንደነበሩ እናስታውሳለን።

መኖር ብዙ አስተምሮናል። ግጭትን (አለመስማማትን) ትክክለኛ የሆነ መስመር በማስያዝ ወይም በመፍታት አሳብ ላይ ከሌሎች ሰዎች ብዙ ተምረናል። ወላጆቻችን፣ ዘመዶቻችን፣ አስተማሪዎቻችን አለመስማማትን ለማስወገድ መፍትሄ ሲሰጡ አይተናል። "ሌላው በአንተ ላይ ሊያደርግብህ የማትፈልገውን፣ በሌላው ሰው ላይ አታድርግ" የሚለውንም ወርቃማውን ሕግ ጠንቅቀን አውቀናል። "ጥርስን በጥርስ፣ ዓይንን በዓይን" የሚለውን የብሉይ ኪዳን ሕግ በመከተል ፈንታ፣ "አንዱን ጉንጭህን ለሚመታህ፣ ሌላውን ጉንጭህን ስጠው" የሚለውን የወንጌሉን ቃል በተግባር ለመተርጎም ሞክረናል። "የዋሆች ብፁዓን ናቸው፤ ምድርን ይወርሳሉ" (የማቴ. 5፥5) የሚለውን የክርስቶስን የተራራው ትምህርት በሕይወታችን ለመለማመድ ሞክረናል። በዚህ ምክንያት አንዳንዶቻችን ማንኛውንም ግጭት መፍታት የምንችለው ሁልጊዜ የሌላውን ሰው ጥያቄ "እሺ!" በማለት፣ ፍላጎቱን በማሟላት ብቻ ይመስለናል። ከማንም ሰው ጋር ያለመስማማት ማሳየት የለብንም በማለት ለተጠየቅነው ነገር ሁሉ፣ እኛን ቢጎዳንም እንኳን "እሺ!" የሚል መልስ መስጠት ያለብን ይመስለናል።

ሁላችንም በግጭት ውስጥ የምናልፍበት ምክንያቶች ብዙ ናቸው። አሳባችን፣ ምርጫችን፣ ውሳኔያችን ከሌሎች ሰዎች የተለየ እስከ ሆነ ድረስ፣ ከግጭት ነጻ ሆነን መኖር አንችልም። እግዚአብሔር ሁላችንንም በመልክ፣ በቁመት፣ በምርጫ ወዘተ. አንድ ዓይነት አድርጎ አልፈጠረንም። ቢሆን ኖሮ ዓለም በጣም የሚሰለች ወይም የሚቸከ ስፍራ ይሆን ነበር። በሌላ በኩል ደግሞ ይሄ ልዩነታችን የግጭታችን ምክንያት ሊሆን እንደሚችል መዘንጋት የለብንም። የሁላችንም "የመገንዘብ ችሎታ" (perception) - ሁኔታዎችን የምናይበት፣ የምንሰማበት፣ የምናሸትበት፣ የዓለምን ሁኔታ ለይተን የምናውቅበት ችሎታችን ይለያያል። ሁለት ሰዎች አንዱን ነገር የሚያዩት በተለያየ ሁኔታ ነው። አንዱ ያየውንና የሰማውን፣ ሌላው ጎረቤቱ አያይም፤ አይሰማም። የሰው ሁሉ አመለካከቱና አስተያየቱ በተፈጥሮ የተለያየ ቢሆንም፣ የግጭታችን ምክንያት መሆኑ በጣም ያስደንቃል። ከአብራኩ የወጡ፣ በአንድ ጣራ ሥር ያደጉ፣ ከአንድ ገበታ የተመገቡ አራት ልጆች አሉኝ። አራቱም ልጆቼ እኔን አባታቸውን ሁሉም እኩል ያውቁኛል ብዬ አምናለሁ። ይሁን እንጂ፣ "አባታችሁ ምን ዓይነት ሰው ነው?" ተብለው ቢጠየቁ የአራቱም አስተያየት መቶ በመቶ አንድ ዓይነት ይሆናል ብዬ ግን አልጠብቅም። አንዱ "ሁላችንንም እኩል ይወደናል" ቢል፣ ሌላው ደግሞ "ለሁላችንም እኩል የሆነ ፍቅር የለውም። ልጆቹን ያበላልጣል፤... ለወንድማችን እከሌ ያደላል..." ማለት ይችላል። ልጆቼ ስለ አባታቸው የተለያየ አመለካከትና ግምት ስላላቸው፣ እርስ በርሳቸው ጠላቶች ናቸው ማለት አይደለም። ይህንን እውነት ካልተረዱ፣ በመካከላቸው ትልቅ ግጭት ሊፈጠር እንደሚችል የታወቀ ነው።

ሰውን ከሌላው የተለየ የሚያደርገው ሌላው ምክንያት የሚኖረው የእምነት አቋም ነው። ሁላችንም አንድን ነገር በተደጋጋሚ ስናይ፣ ያን ያየነውን ነገር "እንዲህ ነው" ብለን የማመን ዝንባሌ አለን። ለምሳሌ፣ ከልጆቼ መካከል

ነው። ይህንን ማድረግ የሚቻልበት እንደኛው መንገድ፥ የራስን መብት ስለዚያ ሰው ሲባል በመተው ብቻ ነው። ይህን ዓይነት ምሕረት ለሌሎች ያሳዩ ብዙ ሰዎች እንዳሉ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እናያለን። በአብርሃምና በሎጥ ሠራተኞች መካከል በተፈጠረው ግጭት ምክንያት ወደ በለጠ ግጭት እንዳያደርሳቸው አብርሃምና ሎጥ የግድ መለያየት ነበረባቸው። አብርሃም ለሎጥ የመጀመሪያውን ምርጫ ሲሰጠው፥ የራሱን መብት መተው እንደነበረበት ግልጽ ነው (ዘፍ. 13፥5-12)። እንዲሁም ዮሴፍ ባሪያ እንዲሆን ለግብጻውያን የሸጡትን ወንድሞቹን ላደረሱበት ጉዳት ብድራታቸውን መመለስ ሲገባው፥ እንደበደላቸው አልተበቀላቸውም (ዘፍ. 50፥19-21)። ኢየሱስም በራሱ ሕይወት ብዙ ምሳሌዎችን ትቶልናል።

በሌላ በኩል ግን መብታችንን ከመተው ይልቅ መብታችንን ማስጠበቅ ወይም ምህረት አለመስጠቱ በሌሎች ሰዎች ሕይወት ውስጥ የተሻለ ውጤት የሚያስገኝበት ጊዜ አለ። ይኸውም፥

(1) አንዳንድ ጊዜ አንዳንድ ሰዎች ግዴለሽነት ለሞላበት ሕይወታቸው ዋጋ መክፈል እንዳለባቸው፥ በወሰኑት ውሳኔ ምክንያት ለሚደርሰው መጥፎ ነገር ተጠያቂ መሆናቸውን እንዲማሩ ምሕረት አለማሳየቱ የሚጠቅምበት ጊዜ አለ። መጽሐፍ ቅዱስም ይህንን አሳብ ይደግፈዋል። *"ቁጡ ሰው ቢናርር የቁጠኛነቱን ዋጋ እንዲያገኝ ተወው፤ አንድ ጊዜ ከችግሩ ልታወጣው ብትሞክር፥ ሌላ ጊዜም እንዲሁ ማድረግህ አይቀርም"* ይላል (ምሳሌ 19፥19)።

(2) አንዳንዴ የራስን መብት ማስጠበቅ፥ ለቤተሰባችን ደህንነት አስፈላጊ የሚሆንበት ጊዜ አለ። *"ስለ ክርስቶስና ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ስል ሁሉን እተዋለሁ"* በማለት፥ ያለአግባብ ቤተሰቦቻችን እንዳይጎዱ የመጠበቅ ኃላፊነት እንዳለብን መዘንጋት የለብንም።

የራሳችንን መብት የምንተውበት ምክንያት እንዲሁ ሳይሆን፥ የእግዚአብሔርን መንግሥት ለማስፋፋት፥ ለሰዎች በጎነትና ለእግዚአብሔር ክብር ሲንል መሆን አለበት። የራሳችንን መብት እያጉረመረምን ሳይሆን ደስ ብሎን መተዋችን፥ የክርስቶስን መንግሥት እንዳናስፋፋ እንቅፋት ሊሆንብን ከሚችለው፥ አስፈላጊ ካልሆነ ግጭት ሊያድነን ይችላል።

# 6

# ሁሉንም ሃሳብ "እሺ" የማለት መፍትሄ የለሽነት

በኢትዮጵያውያን ሕብረተሰብ መካከል አንድ ሰው የሚሰማውንና የሚያስበውን ነገር ሳይደብቅ በግልጽ ቢናገር "ምላሰኛ"፥ ወይም "ለፍላፊ" ያሰኘዋል። የሚሰማውን ገልጾ ካልተናገረ ግን፥ "ጨዋ" ወይም "ጥሩ ሰው" የሚል ስም ይሰጠዋል። በተለይ ሴት ልጅ፥ ብዙ የማትናገር ከሆነ፥ ወይም ዓይን አፋር ከመሰለች፥ *"ክብሯን ጠብቃ የምትኖር ጨዋ ሴት"* ተብላ ትጠራለች። መጽሐፍ ቅዱስም ይህንኑ አሳብ የሚደግፈው ይመስላል። *"ከብዙ ንግግር ውስጥ ስሕተት አይጠፋም፤ ስለዚህ አስተዋይ ሰው ብዙ ከመናገር ይቆጠባል"* (ምሳሌ 10፥19) … *"ሳያስብ በችኮላ ከሚናገር ሰው ይልቅ አእምሮ የጎደለው ሰነፍ ሰው የተሻለ ተስፋ አለው"* ይላል (ምሳሌ 29፥20)። ይሁን እንጂ፥ መጽሐፍ ቅዱስ "ከብዙ ንግግር ውስጥ ስህተት አይጠፋም" ሲል፥ "ንግግራችን ሚዛኑን የለቀቀ አይሁን" ማለቱ ነው እንጂ፥ ጨርሶ መናገር የለብንም ማለቱ አይደለም። ስለዚህ

ሁልጊዜ ዝም ማለት፥ ወይም በልባችን ውስጥ ያለውን እውነት፥ እንዲሁም የሚሰማንን መጥፎም ሆነ ጥሩ ስሜት ገልጦ አለመናገር የአስተዋይነት ወይም የጥሩ ሰውነት መመዘኛ ወይም ምልክት እንዳልሆነ መረዳት ይገባናል። መናገር ሲገባቸው በግልጥ የማይናገሩትን፥ ወይም እውነቱን በውስጣቸው የሚሸሽጉትን መጽሐፍ ቅዱስ በማመስገን ፈንታ "ሁከት ፈጣሪዎች" በማለት ይገልጻቸዋል። *"እውነትን በግልጥ የማይናገር ሰው ሁከትን ይፈጥራል፤ በግልጥ የሚነቅፍ ግን ሰላም እንዲገኝ ያደርጋል"*(ምሳሌ 10፥10) ይላል። ጨዋነት በመናገር ወይም ባለመናገር ላይ የተመሠረተ ሳይሆን፥ መናገር በሚገባ ጊዜ አስፈላጊውን ነገር በመናገር፥ እንዲሁም ዝም ማለት በሚያስፈልግበት ጊዜ ደግሞ ዝም በማለት ላይ የተመሠረተ ነው። ይህንኑ አሳብ ጠቢቡ ሠለሞን ሲገልጽ፥ *"ተገቢውን ቃል በተገቢው ቦታ መናገር እጅግ ያስደስታል"* ይላል (ምሳሌ 15፥23)።

# 1. የሚሰማንን አለመናገር መንፈሳዊነት አይደለም

ያለአግባብ የሚገፋንና የሚያስጨንቁንን፥ መብታችንን የሚገፉትን፥ እንዲሁም እግዚአብሔር የሰጠንን የመፍቀድና የመምረጥ ነጻነታችንን የሚወስዱብንን ሰዎች ዝም ማሰት ፈሪነትና ሞኝነት እንጂ መንፈሳዊነት ወይም ጨዋነት አይደለም። ለምሳሌ አንድ ሰው በማወቅም ሆነ ባለማወቅ እግራችን ላይ ቢቆም፥ *"እረገጥከኝ፥ እባክህን እግርህን ከእግሬ ላይ አንሳ"* ብሎ አለመናገር፥ ሞኝነት እንጂ ጨዋነት እንዳልሆነ ከማንም የተሰወረ አይደለም። የሚቆረቁረን ነገር ሲያጋጥመን "ቆረቆረኝ" አለማለት፥ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚለው በተገቢው ጊዜ ተገቢውን ቃል አለመናገር እንጂ፥ ትዕግሰተኛ መሆን አይደለም። ግጭትን በመፍራት ብቻ አንዳንዶቻችን አግባብ ያልሆነ ነገር ሲደረግብን ዝም ማለታችን፥ ለጊዜው ዝምታችን ሰላምን የሚያመጣ ይምሰለን እንጂ፥ በዚያ ሰው ላይ በውስጣችን የምናጠራቅመው ቅሬታ ሞልቶ አንድ ቀን ሲፈነዳ፥ እኛንም ሆነ ቅሬታ የያዝንበትን ሰው እንደሚጎዳ የታወቀ ነው።

አንዳንድ ሰዎች ዝም በማለታቸው ትዕግሰተኛ ይምሰሉ እንጂ፥ በውስጣቸው በደልን የማጠራቀም ዝንባሌ ሊኖራቸው እንደሚችል መዘንጋት የለብንም። በደልን በውስጣቸው ከሚያጠራቅሙ ሰዎች መካከል እንደ ምሳሌ አድርገን ያቀረብናት ሴት፥ ሐረግ ወይን ትባላለች። ሐረግ ወይን በመካከለኛ ዕድሜ ውስጥ ያለች ሴት ስትሆን፥ በአካባቢዋ ባሉት ሰዎች ዘንድ የምትታወቀው በዝምተኛነት ባሕሪዋ ነው። የልቧን ገልጻ ሰለማትናገር በኑሮዋ ደሰተኛ መሆን አለመሆኗን ማንም ሰው አያውቅም። እውነተኛውን እርሷነቷን በደንብ የማያውቁ፥ ዝምተኛነቷን ብቻ በማየት ሁሉ ነገር የተሟላላት፥ በኑሮዋ ደስተኛ ሴት እንደሆነች አድርገው የሚገምቷት ሰዎች እንደሚኖሩ እርግጠኞች ነን።

ይሁን እንጂ፥ ሐረግ ወይን በሰው ዓይን የማይታይ የራሷ የሆነ ችግር አለባት። ይኸውም፥ ውስጧ በቁጣ፥ በንዴት፥ በመራራነትና እንዲሁም በአዕምሮ ጭንቀት (depression) የተሞላ፥ እውነተኛ ደስታ የሌላት ሴት ናት። ሐረግ ወይን ቁጣቸውን መቆጣጠር እንዳቃታቸው ሰዎች በመጮኽ፥ በመሳደብ፥ ዕቃ አንስቶ በመወርወር ቁጣዋን ሰለማትገልጽ፥ "ትዕግሰተኛ፥ በሰላም የተሞላች ሴት ናት" ብለው የሚያስቡ አንዳንድ ሰዎች እንደሚኖሩ ግልጽ ነው። "ሰላማዊ ሴት" ናት ብለው የሚያስቡትም ቁጣዋን ከላይ በገለጽነው ዓይነት ሁኔታ ሰትገልጽ ሳላላዩ ነው። ሐረግ ወይን አሁን ያላትን ዓይነት ጠባይ፥ ይኸውም የሚደርስባትን ክፉም ሆነ ደግ በልቧ ይዛ መቀመጥ የቻለችው፥ ያደገችበት ቤተሰብና እንዲሁም በአሁኑ ጊዜ ያለችበት የኑሮ ሁኔታ እንደዛ አድርጎ ሰለቀረጻት ነው።

ሐረግ ወይን ወላጅ አባቷ የሞተው በሕጻንነቷ ስለ ነበር፥ ያደገችው ከወላጅ እናቷና ከእንጀራ አባቷ ጋር ነው። የእንጀራ አባቷ፥ *"ልጆች ሥርዓት ያላቸው እንዲሆኑ፥ ወይም ጥሩ ጠባይ እንዲኖራቸው፥ በደንብ ተቀጥተው ማደግ አለባቸው"* የሚል እምነት ያለው ሰው ነበር። በመሠረቱ ልጆች ጥሩ ጠባይ ይዘው እንዲያድጉ ማድረግ መጥፎ አይደለም። ነገር ግን "ፍጹምነትን" ከልጆች ጠብቆ፥ እንደ ልጆች ተጫውተው እንዳያድጉ አስፈላጊውን ነጻነት መከልከል ግን፥ ካደጉ በኋላ በሕይወታቸው ላይ ምን ዓይነት ተጽንኦ ሊያሳድር እንደሚችል የሐረግ ወይን ወላጅ እናትም ሆነች የእንጀራ አባቷም የተረዱት አይመሰለንም። ለምሳሌ ሐረግ ወይን ስትጫወት የለበሰችው ልብስ ትንሽ ቆሻሻ ቢነካው የሚደርሰባት ቅጣት ምን ያህል ከባድ እንደሚሆን ሰለምታውቅ፥ እንደ ልጆች እንደ ልቧ ተዝናንታ ተጫውታ አታውቅም። ምግብ ሰትበላ፥ ውጥ ድንገት ልብሷ ላይ ጠብ ቢል፥ "ዝርክርክ" ተብላ ሰለምትገረፍ፥ ከፍርሃት የተነሳ የሚቀርብላትን ምግብ እንኳን ደስ ብሏት አትበላም ነበር። የእንጀራ አባቷ *"ልጅ ለአዋቂ መልስ መስጠት የለበትም"* የሚል ጥብቅ እምነት ሰለ ነበረው፥ ያለጥፋቷ እንደ ጥፋተኛ ሆና ስትቀጣ፥ ስሜቷን ገልጻ ለመናገር ነጻነት አልነበራትም። ሌላው ቀርቶ ሐረግ ወይን ስሟ ሲጠራ ፈጥና "አቤት!" ወይም "እመት!" ባትል፥ ከፍተኛ ቅጣት ይደርሰባት ነበር። ሐረግ ወይን የልጅነት ዘመኗን ያሳለፈችው ከላይ እንደ ገለጽነው በፍርሃትና በሰጋት ውስጥ ነው። "ጥሩ ልጅ" ለመባል ምንም ያህል ጥረት ብታደርግ፥ የእንጀራ አባቷን ደስ ማሰኘት አትችልም ነበር። በትንሹም በትልቁም፥ ምክንያት እየፈለገ ነፍሷ እሰኪወጣ ድረስ ይገርፋት ነበር። በወቅቱ ከፍተኛ መራራነት፥ ሀዘንና ቂም የነበራት በእንጀራ አባቷ ላይ ብቻ ሳይሆን፥ በወላጅ እናቷ ላይም ነበር። ምክንያቱም አስፈላጊውን ፍቅር እንደ እናት በማሳየት ፈንታ ባሏን ብቻ ለማስደሰት ሰትል ሐረግ ወይንን ከእንጀራ አባቷ ባላነሰ ሁኔታ የምታሰጨንቃት

ትና ፈቃድ መግዛት መጥፎ የሆነውን ያህል፥ ሁልጊዜ "እሺ! አንተ እንዳልክ..." ማለትም በዚያው መጠን ትክክል አይደለም። ሌላውን ሰው በትህትናና ዝቅ ብሎ ማገልገል፥ርህራሄና ቸርነት ማሳየት፥ ከሌላው ጋር በሰላም ለመኖርና ጤናማ የሆነ አንድነት ለመፍጠር ይረዳል። ሌላውን በቁጥጥሩ የማዋል ፍላጎትና ጥማት ባለውና፥እንዲሁም ሌላውን ደስ ለማሰኘት ሲል የራሱን ፈቃድ ችላ በሚል ሰው መካከል የሚመሠረተው ሕብረት በእኩልነት ላይ የተመሠረተ ሳይሆን፥ በአንድ አቅጣጫ ሚዛኑ ያጋደለ፥ አንዱን ጠቅሞ ሌላውን የሚጎዳ እንደሆነ ግልጽ ነው። የራሱን ፍላጎት ወደ ጎን አድርጎ ሁልጊዜ ሌላውን ደስ እያሰኘ የሚኖር ሰው፥ በፍርሃት፥ በቅሬታና በበደለኛነት ስሜት ተሞልቶ የሚኖር እንጂ ደስተኛ ሰው አይደለም።

ለትምህርታችሁ እንዲሆን በልጅነቴ ካደረግሁት የሞኝነት ሥራ፥ ምንጊዜም ከአዕምሮዬ የማይጠፋውን አንዱን ታሪኬን ላጫውታችሁ። በተለያዩ ጽሑፎቼም ሆነ በማስተምረው ትምህርት ላይ ደጋግሜ እንደገለጽሁት፥ የወላጆቼን ፍቅር አግኝቼ አላደግሁም። አባቴ በልጅነቴ ስለ ሞተ ያደግሁት ከአባቴ እኅት ጋር ነው። ወላጆቼ አለመሆናቸውን ስለማውቅ፥ ልጆች በወላጆቻቸው ላይ እንደሚሞላቀቁት፥ እኔም ወላጆቼ ባልሆኑት አሳዳጊዎቼ ላይ ያንን ዓይነት ጠባይ ማሳየት እንደሌለብኝ፥ የህጻን አዕምሮዬ በደንብ አውቆታል። በመሞላቀቅ ፈንታ፥ አሳዳጊዎቼን በጣም ማስደሰት አለብኝ ብዬ ስላመንኩና ስለተቀበልኩ፥ እነርሱን ለማስደሰት ከመስመሬ ወጥቼ የማላደርገው ነገር አልነበረም። ስለ ራሴ ፍላጎት፥ ስለ ራሴ ምቾት ፈጽሞ አላስብም ነበር። እኔ የተፈጠርኩት፥ እግዚአብሔር እኔን ሲሠራኝ፥ ዋና ዓላማው፥ አሳዳጊዎቼን ብቻ ደስ አሰኝቼ እንድኖር መስሎ ይሰማኝ ነበር። እንደ ማንኛውም ልጅ የራሴ ፍላጎት ቢኖረኝም፥ የምፈልገውን ነገር ለራሴ ማድረግ ባለመቻሌ ሁልጊዜ ውስጤ ያዝን ነበር። ከውስጤ ባርነት እንጂ፥ ነጻነት ፈጽሞ አይሰማኝም ነበር። ጓደኞቼ የሚፈልጉትን ወላጆቻቸው የሚሰጧቸው መሆናቸው ብቻ ሳይሆን፥ የራሳቸው የሆነውንም በነጻነት የሚጠቀሙ መሆናቸውን ሳይ፥ እኔ ግን የሚሰጠኝ ባይኖር እንኳን፥ የራሴ የሆነውን እንደ ፈለግሁት መጠቀም ባለመቻሌ ልቤ እጅግ በጣም ያዝን ነበር።

በአንድ ወቅት መንደራችን ውስጥ የአንድ ዕድር ጸሐፊ ነበርኩ። የጸሐፊነቱን ኃላፊነት ከመቀበሌ በፊት፥ የዕድሩ ዳኛ በየሳምንት ለምሰጣቸው አገልግሎት በዓመቱ መጨረሻ ላይ እያንዳንዱ የዕድሩ አባል ሃያ አምስት ሳንቲም እንደሚሰጠኝ ተነገረኝ። ያ በወቅቱ በጣም ትልቅ ገንዘብ ነበር። የዕድሩ አባሎች ከመቶ በላይ ስለሆኑ፥ እያንዳንዳቸው ሃያ አምስት ሳንቲም የሚሰጡ ከሆነ ቢያንስ ሃያ አምስት ብር ወይም ከዚይ በላይ እንደማገኝ ተነገረኝ። በዚሁ ስምምነት የጸሐፊነት ሥራዬን ጀመርኩ። ዓመቱ መጨረሻ ላይ የተወሰኑ ሰዎች ለጸሐፊው የሚገባውን የተጠየቁትን ሃያ አምስት ሳንቲም ሰጡ። ይሁን እንጂ፥ የተጠየቁትን ገንዘብ የከፈሉት ሰዎች በጣም አነስተኛ ስለነበሩ የጠበቅሁትን ያህል ገንዘብ አላገኘሁም። ብዙም ሆነ ትንሽ ባገኝ ተጠቃሚው እኔ ሳልሆን አሳዳጊዎቼ በመሆናቸው ይህን ያህል ሊያሳስበኝ አይገባም ነበር። እኔን ግን በጣም አሳሰበኝ። "ሁልጊዜ ማስደሰት አለብኝ" የሚል እምነት ስለነበረኝ፥ በገንዘቡ ማነስ አሳዳጊዎቼ ቅር እንዳይላቸው አንድ ነገር ማድረግ እንዳለብኝ ተሰማኝ። ተጨማሪ ገንዘብ የማገኝበት ሌላ መንገድ ስላልነበረኝ፥ ያለችኝን የለበስኳትን አንድ ጥሩ ሹራብ አውልቄ ጨርቅ ተራ ወስጄ ሸጥኳት። ገንዘቡን ካገኘሁት የዕድር ገንዘብ ጋር ጨምሬ ላሳዳጊዎቼ "በዕድር ጸሐፊነት ያገኘሁት ነው" ብዬ ሰጠኋቸው። ይህንን ሳደርግ ደስ ብሎኝ ሳይሆን፥ ውስጤ በጣም እያዘነና ቅር እያለኝ ነበር።

ከላይ የልጅነት ታሪኬን እንደ ገለጽኩላችሁ፥ ልክ እንደ እኔ አንዳንድ ሰዎች ሁልጊዜ ሌላውን ሰው ለማስደሰት የሚሞክሩ፥ ኃላፊነት በሌላቸው ነገር ሁሉ ላይ ኃላፊነትን በራሳቸው ላይ ሲጭኑና ራሳቸውን ጎድተው ሌላውን ሲጠቅሙ ይታያሉ። በመሠረቱ በሁለት ሰዎች መካከል መልካም የሆነ ግንኙነት ለመፍጠር፥ ሁለቱም ወገን እያንዳንዱ በራሱ በኩል ያለበትን ኃላፊነት በትክክል መወጣት አለበት። ለምሳሌ ቁጡ ባሕሪ ያለው ሰው፥ ቁጣውን አለአግባብ በመግለጽ ሌላውን ሰው ቢጎዳ፥ "ጎጂ በሆነ መንገድ ቁጣዬን በመግለጼ ትክክል አይደለሁም። ምንም እንኳን ሁኔታው የሚያስቆጣ ቢሆንም፥ ስሜቴን በአግባቡ መግለጽ ነበረብኝ" ማለት ሲገባው፥ የተጎዳው ሰው ራሱን ለሰውየው ተቆጪነት ተጠያቂ ማድረግ የለበትም። ሰውን ሁልጊዜ አስደስተው መኖር የሚፈልጉ፥ ሌሎች ሰዎች ለሚፈጥሩት ችግር ራሳቸውን ተጠያቂ ወይም ምክንያት ማድረግ ባሕሪያቸው ነው። እነርሱ ተጎድተው ሌላው ሰው ጥሩ ስሜት እንዲሰማው ማድረግ ግዴታ ያለባቸው መስሎ ይመስላቸዋል። ይህን ዓይነት አስተሳሰብ እንዲኖራቸው ምክንያት የሆነባቸው፥ አስቸጋሪ የሆነው ሰው የሚያደርስባቸው ግፊት እንዲሁም የሚሰማቸው የበደለኛነት ስሜት ነው። በእነርሱና በሌላው ሰው መካከል ሊኖር የሚገባው ግንኙነት፥ ወይም ሰላም የተጠበቀ እንዲሆንና እንዲዘልቅ ኃላፊነቱ እነርሱ ላይ ብቻ የተጣለ ይመስላቸዋል። ከላይ ታሪኳን እንደሰማነው ሐረገ ወይን፥ አስቸጋሪ የሆነው ባሏ የሚያሳየው ጠባይ የቤቱን ሰላም የሚያደፈርስ በመሆኑ፥ ስለ መጥፎ ጠባዩ ራሱ ተጠያቂ መሆን ሲገባው፥ የቤተሰቡን ሰላም ለመጠበቅ ስትል ሁልጊዜ የጠየቀውን ወይም የፈለገውን ነገር "እሺ!" ማለቷ ትክክል አይደለም። ምንም ያህል ዋጋ ቢያስከፍላትም ቁጣውን ስለምትፈራ ብቻ እንዳይቆጣ ወይም እንዳይበሳጭ የማድረግ ኃላፊነት ያለባት ይመስላታል። የራሱን መጥፎ ባሕሪ መቆጣጠር የተሳነው ባሏ ተጠያቂ መሆን ያለበት እርሱ ራሱ እንጂ፥ እርሷ እንዳልሆነች አልተገነዘበችም።

ሰው፥ ሁለቱም ወገን የሚያገኘው ብቻ ሳይሆን የሚሰጠው ነገር ሲኖር ነው። አንደኛው ወገን ሰጪ፥ ሌላው ተቀባይ ብቻ ከሆነ፥ ሕብረቱ (ግንኙነቱ) ወደ አንድ ወገን ያጋደለ ስለሚሆን፥ ኃላፊነት የተጫነበት ወገን ደስተኛ ሳይሆን፥ ወይም ቅር እያለውና እያዘነ እንዲኖር ይሆናል። ጤናማ በሆነ ሕብረት (ግንኙነት) ውስጥ ያሉ ሁሉ፥ ሁለት ዓይነት ምርጫ አላቸው። አንደኛ፥ የሚያደርጉትን ነገር በፈቃዳቸው፥ መርጠውና ደስ ብሏቸው ማድረግን፥ ሁለተኛ፥ "ከእኔ ይጠበቅብኛል..." በሚል ስሜት ብቻ ደስ ሳይላቸው የሚያደርጉት ናቸው። "ሁልጊዜ ሰውን ሁሉ ደስ ማሰኘት አለብኝ" ብለው የሚያምኑ ሰዎች ከላይ ከገለጽናቸው ከሁለቱ መካከል፥ ከልባቸው የሚፈልጉት የመጀመሪያውን ቢሆንም፥ ሁለተኛውን እንደ መመሪያ አድርገው ሲይዙት ይታያሉ። ውሳኔ አሰጣጣቸው በምርጫ ሳይሆን፥ *"ግዴታዬ ነው!... ማድረግ ያለብኝ ነው... ከእኔ የሚጠበቅ ነው..."* በሚል ስሜት ነው። ከእነዚህም መካከል ለሚያደርጉት ነገር ምክንያቱ የዚህ ዓይነቱ ስሜት መነሳሳት እንደሆነ እንኳ የማያውቁ አሉ።

ሁሉን ለማስደሰት የሚፈልጉ ሰዎች፥ የሌላውን ሰው ሕይወት በቁጥጥሩ ሥር ማድረግ ከሚፈልግ፥ ሰውን መውቀስ እንጂ ማመስገን ከማይሆንለት፥ የተለዋዋጭነት ባሕሪ ከሚታይበት ሰው ሕይወት ጋር ሕይወታቸው የተያያዘ ነው። ከአስቸጋሪው ሰው ጋር ያላቸው ሁኔታ አሁን ካሉበት የበለጠ የከፋ እንዳይሆን፥ በመካከላቸው ጦርነት እንዳይፈጠር፥ ሕይወታቸውን በቁጥጥሩ ሥር ላደረገው ኃይለኛ ሰው እጆቻቸውን ሰጥተው የጠየቀውን ሁሉ አሟልተው ከመኖር በስተቀር ሌላ ምርጫ የሌላቸው ይመስላቸዋል። ፈቃዳቸውን ሌላው ሰው ስለሚጫነው፥ የተሰፋቢስነት ስሜት የሚያጠቃቸው ናቸው። ሌላውን ሰው ደስ ለማሰኘት ይሞክሩ እንጂ፥ ራሳቸው ደስተኞች አይደሉም። የግል ፈቃድና ምርጫ እንዳይኖራቸው፥ በሌላው ፈቃድ ሥር እንዲኖሩ በእግዚአብሔር የተወሰነባቸው መስሎ ይሰማቸዋል። አብሯቸው ስለሚኖረው አስቸጋሪ ሰው ሲናገሩ፥ *"ከእንቅልፌ ከተነሳሁበት ሰዓት ጀምሮ፥ መሽቶ ወደ አልጋዬ ተመልሼ እስከምሄድበት ጊዜ ድረስ እርሱን ደስ ለማሰኘት ምንም ያህል ብደክም፥ ላስደስተው አልቻልም። ተለዋዋጭ ባሕሪ ስላለው ሥራ ሄዶ ወደ ቤት ሲመለስ ምን ዓይነት ሰው ሆኖ እንደሚመጣ አላውቅም። አሁን ስቆና ተጫውቶ እንደ ሆነ ጥቂት ቆይቶ ሲበሳጭና ሲያማርር እሰማዋለሁ። ስለ ራሱ ፍላጎት እንጂ ስለ እኔ ፍላጎት ፍጹም ግድ የለውም። እንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ ፍጹም እየታከተኝ ነው"* ይላሉ። ሰውን ለማስደሰት የሚጥር ሰው ከላይ በገለጽነው ሁኔታ ደስተኛ ባይሆንም፥ አብሮት ለሚኖረው አስቸጋሪ ለሆነበት ሰው ቅሬታውን ሳይገልጽ፥ ደስተኛ መስሎ ለመኖር ይሞክራል። ሕይወት እንደሌለው እሻንጉሊት እንደፈለጉት ቢያደርጉት፥ መሬት አስተኝተው ቢረማመዱበት፥ "ተንዳሁ!" ብሎ ስሜቱን ገልጾ አይናገርም። ከላይ እንደገለጽነው ሰው በአስቸጋሪው ሰው ምክንያት የግል ነጻነታችንን አጥተን የምንኖር መሆናችንን ለማወቅ ከዚህ በታች የዘረዘርናቸውን ጥያቄዎች ራሳችንን እንጠይቅ፥

- *ብዙውን ጊዜዬን የማጠፋው ሌላውን ለማስደሰት ነው?*
- *ችግር ይፈጥራል፥ ወይም ጦርነት ያስነሳል ብዬ በመፍራት ስሜቴን ገልጬ መናገር ድፍረት የለኝም?*
- *ቅሬታዬን ባሰማ፥ ወይም ስሜቴን ገልጬ ብናገር የሚቀበለኝ ሰው አይኖርም የሚል ፍርሃት አለኝ?*
- *"በዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ መኖር አለብህ" ተብዬ በተሰጠኝ ክልል ወይም ገደብ ውስጥ መኖር ያለብኝ መስሎ ይሰማኛል?*
- *የማደርጋቸው ውሳኔዎች ሁሉ እኔን ደስ የሚሉኝን ሳይሆን፥ ሌላውን ደስ እንዲለው ነው?*
- *የትኛው እንደሚበጀኝና እንደማይበጀኝ የሚወስንልኝ ሌላ ሰው ነው?*
- *ምንም ያህል ጥሩ አድርጌ ብሠራ፥ መነቀፌ አይቀርም የሚል ፍርሃት በውስጤ አለ?*
- *ከሌላው ሰው ጋር በሰላም መኖር እንድችል ስል ብቻ የማላምንበትን ነገር አደርጋለሁ?*

ለእነዚህ ጥያቄዎች ለአብዛኛዎቹ የምንሰጣቸው መልሶች "አዎን!" የሚል ከሆነ፥ እግዚአብሔር ራሱ የሰጠንን የግል ፈቃዳችንንና ነጻነታችንን የሚጫን፥ ሕይወታችንን በቁጥጥሩ ሥር የሚያደርግ አስቸጋሪ ሰው በሕይወታችን እንዳለ እንረዳለን።

## 9. አስቸጋሪውን ሰው ለማስደሰት ነጻነታችንን ማጣት የለብንም

ለማንኛውም ጤናማ ግንኙነት (relationship) ነጻነት በጣም አስፈላጊ ነው። በባዕድ አገዛዝ ሥር የኖረ ሕዝብ ለነጻነቱ የሚሰጠው ሥፍራ ከፍተኛ ነው። በምዕራቡ ዓለም የሚኖሩ ሰዎች የግል ነጻነታቸው እንዲነካባቸው አይፈልጉም። በኃይልና በሥልጣን ሲገዛቸው ወይም ሲያስተዳድራቸው ለሚ

ፈልግ ባለሥልጣን ምቹ አይደሉም። እግዚአብሔር ለሰው ሙሉ ነጻነትን ሰጥቶ እንደ ፈጠረው ያምናሉ። በሥልጣን ላይ የሚቀመጡትም ሰዎች ኃላፊነታቸው ያንን ነጻነት መጠበቅ ነው። ነጻነት በአገር ደረጃ ብቻ ሳይሆን በግልም፣ ሰዎች እርስ በርስ በሚኖራቸው ግንኙነትም ላይ አስፈላጊ መሆኑን ብዙዎቻችን የተረዳን አንመስልም። ሰውን ሁልጊዜ ለማስደሰት የሚሞክሩ ሰዎች፣ ከሌላው ሰው ጋር በሰላም ለመኖር ሲሉ ብቻ የግል ነጻነታቸውን ቢያጡ ፈጽሞ ግድ የሌላቸው ናቸው። ሌላውን በቁጥጥራቸው ሥር የማዋል ጥማት ያሰባቸው አንዳንድ ሰዎች፣ አብረዋቸው የሚኖሩትን ሰዎች ለእነርሱ እንዲመቹ አድርገው ለመቅረጽ ሲሞክሩ ይታያሉ። ሰውን ሁሉ ለማስደሰት የሚጥሩ ሰዎች፣ መንገዳቸው ሻካራ ሲሆንባቸው፣ ሌላውን ለማስደሰት ሲሉ ነጻነታቸውን አሳልፈው እንደሚሰጡ የታወቀ ነው። የመጨረሻ ውጤታቸውም የአዕምሮ ጭንቀት፣ ተስፋ መቁረጥ፣ በፍርሃትና በስጋት መሞላት ነው።

ሰው የግል ነጻነቱን ሲያጣ፣ በሌላው ወገን ተቀባይነት እንዳላገኘ ይሰማዋል። ራሱን በሌላው ሰው ቁጥጥር ውስጥ ሲያስገባ፣ "አሁን ባሰሁበት ሁኔታ ከእርሱ ጋር ለመሆን ብቁ አይደለሁም..." የሚሰውን አሳብ የሚያስተላልፍ መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል። ሰውን ለማስደሰት ጥረት የሚያደርጉ ሰዎች ያልተረዱት እውነት ቢኖር፣ ምንም ያህል ጥረት ቢያደርጉ፣ አስቸጋሪ ሰዎችን ሊያስደስቷቸውና ልክ እንዳሉ እንዲቀበሏቸው ማድረግ የማይችሉ መሆናቸውን ነው። እንዲሁም ሌላውን ለማስደሰት ሲሉ ፈቃዳቸውንና ነጻነታቸውን መስዋዕት ቢያደርጉ፣ እግዚአብሔር ልዩ አድርጎ የሰጣቸውን ተፈጥሮ አልቀበልም ማለታቸው እንደሆነ አይገነዘቡትም። በግል ነጻነታችን የምናምን ከሆነ፣ ራሳችንን ልክ እንዳለነው መቀበል መቻል አለብን። ሌላው እንዲመቸው ብቻ መሠረታዊ የሆነውን እኛነታችንን ፍጹም ለውጠን ማቅረብ አለብን ማለት አይደለም። በምን ዓይነት ሁኔታ መለወጥ እንዳለብን ለማወቅ፣ በአዕምሮአቸው ውስጥ የሚመላለሰውን አሳብ አንብበን መረዳት አያስፈልገንም። የሆንነውን ሆነን ለመገኘት ሙሉ ነጻነት ሊኖረን ይገባል። አስቸጋሪ ሰዎች ዓላማቸው፣ እነርሱ እንደሚፈልጉት ሆነን እንድንገኝላቸው ብቻ ነው።

ሰው በአስቸጋሪ ሰው አማካኝነት ነጻነቱን ሲያጣ፣ ወይም በሌላው ሰው ቁጥጥር ውስጥ ሲውል፣ መሠረታዊ የሆነውን መታመንን (trust) ያጣል። አስቸጋሪው ሰው በግልጽ፣ "አልተማመንብህም... አላምንህም... እምነት አልጥልብህም..." ባይልም፣ በድርጊቱ የሚያስተላልፈው መልዕክት ግን ይህንኑ ይመስላል። "እንግዳ ሲመጣ፣ እንዲህ ማለት አለብህ... ስትነገር ትልቅ ትልቁን አትጉረስ... እየበላህ አታውራ... ቀና ብለህ ተቀመጥ..." የሚል ምክር መሳይ ትዕዛዝ ይሰጠዋል። ሰውን ማስደሰት የሚፈልገው ሰው፣ "ራሴን በትክክሉ መምራት፣ ችሎታ እንዳለኝ በእኔ እምነት የለህም ወይ?...ምን መናገር እንዳለብኝና እንደሌለብኝ.. ሕጻን ይመስል ምን ዓይነት ልብስ መልበስ እንዳለብኝና እንደሌለብኝ እንዴት ትነግረኛለህ?" ብሎ ቢጠይቅ ደስ ይለው ነበር። ነገር ግን "አስቀይመው ይሆናል" ብሎ በማሰብ የሚሰማውን ስሜት በውስጡ ይዞ ፈገግ ብሎ ማለፍ ይፈልጋል። ማድረግ ያለበትም ነገር ካለ ጦርነት እንዳይፈጠር ሲል የተባሰውን ሁሉ ያደርጋል። ይሁን እንጂ፣ "ራሴን ችዬ ማሰብ እንደማልችል ቆጠረኝ..." በማለት ከልቡ ያዝናል። ሰውን ለማስደሰት የሚጥሩ አንዳንድ ሰዎች አስቸጋሪው ሰው የሚሰጣቸውን ምክርም ሆነ ትዕዛዝ ባይወዱትም፣ እምነት የማይጣልባቸው ሆነው ቢታዩም፣ እራሳቸውን ችሰው ማሰብ እንደማይችሉ ቢቆጠሩም፣ "ማሰብ የማልችል፣ እምነት የማይጣልብኝ አድርጎ ቢመለከተኝም፣ ጸብ እንዳይፈጠር ስል ብቻ ማድረግ ያለብኝን አደርጋለሁ..." የሚሉ አሉ። ሕይወታቸውን የሚቆጣጠረውን ሰው ጠባይ ባይወዱትም፣ በሌላ በኩል ግን እርሱን ደስ ለማሰኘት ጥረት ሲያደርጉ ይታያሉ። አስቸጋሪው ሰው "አድርጉ" ያላቸውን ሁሉ ዝም ብለው ሲያደርጉ፣ የግል ነጻነታቸውን መስዋዕት ከማድረጋቸውም ሌላ፣ ያም ሰው አስቸጋሪ የሆነውን ጠባዩን ይዞ እንዲቀጥል የበለጠ ነጻነት መስጠታቸው እንደሆነ አይረዱትም።

*ንመሳሰልባቸው ነገሮች ውስጥ አንደኛው ከሰው ጋር ባለን ግንኙነት ውስጥ ሁላችንም የራሳችን የሆነ ችግር ያለን መሆናችን ነው።*

(4) *"አሁንስ አዕምሮዬን ልስት ነው" እንላለን። "ነገሮችን በቀላሉ አረሳሁ... በትክክል ማሰብ አልችልም... እንቅልፍ በቀላሉ አይወስደኝም..." እንላለን። ከሰው ጋር ያለን ግንኙነት አስቸጋሪ ሲሆንብን፥ በጉዳት ውስጥ ስናልፍ፥ አንዳንድ ሁኔታዎችን ማስታወስ ከባድ ይሆንብን እንጂ፥ ቀጥተኛ የሆነ አስተሳሰባችንን አናጣም።*

(5) *"ተጎጂሁ!" እንላለን። ይህንን ስንል "..እጅግ በጣም ጎዳኝ/ጎዳችኝ.. ይህን ዓይነት ጉዳት በእኔ ላይ ያደርሳል/ታደርሳለች ብዬ አላምንም ነበር" ማለታችን ነው። እርግጥ ነው ስንገፋ፥ ያስአግባብ ስንያዝ ሰዎች የገቡልንን ቃል ሲዳን ሲያጥፉብን...ውስጣችን ይጎዳል። ይሁን እንጂ፥ ይህን ዓይነቱ ስሜት ሀቀኞች፥ እውነተኞች፥ የፍቅር ሰዎች እንድንሆን ትምህርት ይሰጠናል። በጉዳት ውስጥ ካለፍን፥ ሌላው በተመሳሳይ ሁኔታ ለሚያልፍ ሰው የማዘንና የመራራት ልብ እንዲኖረን ያደርጋል።*

(6) *"ከደለኛ ነኝ" እንላለን። የበደለኛነት ስሜት ሲሰማን፥ "...ይህ እንዳይሆን ምን ማድረግ ነበረብኝ?" ብለን እንጠይቃለን። የበደለኛነትን ስሜት በትክክል ከተጠቀምንበት፥ ምን መለወጥና እንዲሁም ምን ማድረግ እንዳለብን ሊያሳየን ይችላል። ከማንኛውም ዓይነት ስሜት የበለጠ ይሄኛው ገንቢ ነው። ምክንያቱም እኛ ለፈጸምናቸው ድርጊቶች ሁሉ ኃላፊነት ወይም ተጠያቂነት እንዳለን የሚያመለክተን ስለሆነ ነው።*[17]

ስለ ስሜታችን ሌላው ሰው ግድ ከሌለው፥ እኛ ስሜታችንን ለበጎ ልንጠቀምበት ይገባል። ከአስቸጋሪ ሰው ጋር ባለን ግንኙነት ምክንያት ስሜታችንን በትክክል ካልገለጽን፥ ከውስጥ እንደተቀቀለ እንቁላል እንሆናለን። ዕንቁላል ሲቀቀል፥ ውጪው ከመቀቀሉ በፊት ያለውን ዓይነት ይመስላል። ከውስጡ ግን ፈሳሽ በመሆን ፈንታ የጠጠረ ወይም የጠነከረ ይሆናል። ሰውም የሚሰማውን ስሜት ከውስጡ ቀብሮ ዝም ሲል፥ ልቡ በመራራነት፥ በቅሬታ፥ በጥላቻ፥ በአዕምሮ ጭንቀት ወዘተ. የጠጠረ ሊሆን ይችላል።

[17] Elizabeth B. Brown. Living Successfully with Screwed-up People. Fleming H. Revell, Grand Rapids, Michigan, c1999.

# 5. የአኩራፊነት ባሕሪ ካለው ሰው ጋር እንዴት መኖር ይቻላል?

"ኩርፊያ" አስቸጋሪ በሆኑ ሰዎች ውስጥ ከሚታዩት ልዩ ልዩ ጠባዮች መካከል አንደኛው ነው። በተለይ ኩርፊያ ከባድ የሚሆነው በአንድ ጣራ ሥር አብረው የሚኖሩ፥ አንድ ገበታ አብረው የሚቀርሱ፥ አንድ አልጋ ላይ፥ አንድ አንሶላና የብርድ ልብስ ለብሰው በሚተኙ ባልና ሚስት መካከል የሚታይ ከሆነ ነው። አስቸጋሪው ሰው የሚፈልገውን ነገር ካላገኘ፥ ወይም ለጠየቀው ጥያቄ "እሺ!" ካልተባለ፥ የኑሮ ጓደኛውን ወይም የሥራ ባልደረባውን ለማጥቃት ብዙ ጊዜ ኩርፊያን እንደማጥቃያ መሣሪያ አድርጎ ሲጠቀምበት ይታያል። ኩርፊያ የሌላውን ሰው ሕይወት እንደሚያጨልም፥ ምን ያህል ውስጡን እንደሚያስጨንቅ ስለሚያውቅ፥ ሌላውን ሰው በቁጥጥሩ ሥር ማድረግ አቅም ሲያጣ፥ የሚፈልገውን ሥልጣን በትክክል ማግኘት ሲያቅተው፥ ኃይሉን ማሳየት የሚፈልገው በማኩረፍ ነው። ማኩረፍን እንደ መሣሪያ አድርጎ የሚጠቀም አስቸጋሪ ሰው፥ የሚፈልገውን ነገር በትክክል ጠይቆ ማግኘት ካልቻለ፥ ጥቃቅን ምክንያት እየፈለገ ያኮርፋል። "ኩርፊያው... ኩርፊያዋ ፈጽሞ መረረኝ..." የሚሉ ሰዎች ቁጥራቸው ጥቂት አይደለም። አስቸጋሪ የሆነች ቤት "ኩርፊያዬን ስለሚፈራ አድርግ ያልኩትን ሁሉ ያደርጋል" ብላ ስለምታምን፥ ከባሏ የምትፈልገውን ነገር ለማግኘት ኩርፊያን ብዙ ጊዜ ትጠቀማለች። ብዙ ጊዜ ኩርፊያ ከሴቶች ጋር የተያያዘ ይሁን እንጂ፥ ማኩረፍን እንደ መሣሪያ አድርገው የሚጠቀሙበት ሴቶች ብቻ ሳይሆኑ፥ አንዳንድ ወንዶችም እንደሚጠቀሙበት የታወቀ ነው።

ኩርፊያ ሰዎች የሚፈልጉትን ነገር ለማግኘት ብቻ የሚጠቀሙበት መሣሪያ አይደለም። አንዳንዶቹ ከአንዳንድ ነገር የሚሸሹበት መንገድ ነው። ችግራቸውን ገልጠው በመናገር ፈንታ፥ በዝምታ ወይም በኩርፊያ ከሁኔታው ለመሸሽ ይሞክራሉ። በተለያየ ምክንያት ከሚስቱ ጋር የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት መፈጸም የሚፈራ ወንድ፥ ችግሩን ገልጾ ከሚስቱ ጋር በመነጋገርና ዕርዳታ በመፈለግ ፈንታ ከሁኔታው ለመሸሽ የሚሞክረው በኩርፊያ ነው። ይሄ ችግር በወንዱ ወገን ብቻ ሳይሆን በሴቷም በኩል ሊኖር እንደሚችል ሳንጠቅስ ማለፍ አንፈልግም። ይሄን ዓይነት ችግር ያለባቸው ባልና ሚስት ንግግራቸው በጣም የተወሰነ ነው። አብረው ማዕድ ሲቀርሱ "...ጨውን አቀብይኝ.. አቀብለኝ" ከማለት ያለፈ አይደለም። ኩርፊያን የሚጠላ ሰው ከአኩራፊው ጋር የሚኖረው ሁልጊዜ በፍርሃትና በስጋት ነው። ብዙ ጊዜ ምን እንደሚያስኮርፈው አይታወቅምና እንዳያኮርፍ በማለት የሚናገረውን በጣም እየመረጠ፥ የሚያደርገውን ነገር ሁሉ እየተጠነቀቀ ነው። ይሄም ሆኖ አስቸጋሪውን ሰው እንዳያኮርፍ አያ

ደርገውም። እንዲህ ዓይነቱን አስቸጋሪ ሰው ለመለወጥ ምን ያህል ከባድ እንደሆነ በዚህ ሕይወት ውስጥ አልፋችሁ ያያችሁት ታውቃላችሁ። ይሁን እንጂ፥ ደስታችሁ እንዳይደፈርስ፥ ሰላማችሁን እንዳታጡ ራሳችሁን የምትከላከሉበት የተለያዩ መንገዶች አሉ። አስቸጋሪ ሰዎች ኩርፊያቸውን ለመጠቀም ሲፈልጉ፥ ያኮረፉትን ሰው የሚመለከቱት፥ አብሯቸው አንድ ክፍል ውስጥ፥ አንድ አልጋ ላይ ቢሆንም፥ ፍጹም እንደሌለ አድርገው ነው። ሊያስተላልፉለት የሚፈልጉት መልዕክት በንግግር ሳይሆን በመላ ሰውነታቸው ነው። ቀኑን ሙሉ አንድ ክፍል ውስጥ አብሯቸው ቢቀመጥ፥ ዓይናቸው በዝምታቸው ሊቀጡት የፈለጉትን ሰው አያይም። ጥያቄ ጠይቋቸው መልስ መስጠት የግድ ካለባቸው፥ ወይም እነርሱ የሚጠይቁት ጥያቄ ካለ መሬት መሬቱን፥ ግድግዳውን፥ በመስኮት በኩል ውጪ ውጪውን እንጂ፥ ዓይናቸውን ዓይኑ ላይ አሳርፈው አይደለም። በዚህ ዓይነት ላኮረፉት ሰው ማስተላለፍ የሚፈልጉት መልዕክት፥ "...አትረባም! ደካማ ነህ... ላይህና ላነጋግርህ አልፈልግም..." የሚል ነው።

በዝምታቸው ሊቀጡት የፈለጉትን ሰው የሚያስጨንቁት ምን እንደሚያስቡ፥ ለምን እንዳስኮረፈው ፍንጭ በመከልከል ነው። በወቅቱ ምን እንደሚያስቡ በአፋቸው ገልጸው ባይናገሩም፥ የሚያስቡት አፍራሽ እንጂ ገንቢ እንዳልሆነ ግልጽ ነው። ማንም ችላ መባልን ወይም መኮረፍን የሚወድ የለም። ይሁን እንጂ፥ በሌላው ሰው ላይ የሚጠላውን መጥፎ ጠባይ የመለወጥ ኃይል ያለው ሰው የለም። ይህ የሚቻል ቢሆን ኖሮ ብዙዎች ሰላም በማጣት ሕይወት ውስጥ አይኖሩም ነበር። ሌላውን ሰው መለወጥ አይቻሉ እንጂ፥ ራሳቸውን ከሁኔታው ጋር ማስተካከል፥ ወይም የአስቸጋሪ ሰዎች የመቅጫ በትር እንዳይጎዳቸው የማድረግ ችሎታ አላቸው። የማኩረፍ ጠባይካላቸው አስቸጋሪ ሰዎች ሰላማቸው ሳይደፈርስ መኖር የሚችሉበት የተለያየ መንገድ አለ። ጥቂቶቹን ከዚህ በታች ለመጠቆም እንሞክራለን።

## (1) <u>የደስታችንን ማብሪያና ማጥፊያ ቁልፍ አንስጣቸው</u>

አስቸጋሪ ሰዎች በፈለጉበት ጊዜ እንዲያበሩን፥ ባልፈለጉበት ጊዜ ደግሞ እንዲያጠፉን አንፍቀድላቸው። ይሄ እኔ የፈጠርኩት ቋንቋ ስለሆነ ምን ማለቴ እንደሆነ ትንሽ ግር ሳይላችሁ አይቀርም። ሐዋርያው ጳውሎስ አንድ ጥሩ የሕይወት መመሪያ ሰጥቶናል። ያም *"በቀረውስ በጌታ ደስ ይበላችሁ"*(ፊልጵ. 3፥1) የሚለው አሳብ ነው። "...በጌታ ደስ ይበላችሁ..." ሲል፥ የደስታችንን ማብሪያና ማጥፊያ ቁልፍ የያዘው ጌታ ኢየሱስ እንደሆነ መግለጹ ነው። በውስጣችን ለሚሰማን ደስታ ወሳኝ ሌላ ነገር ሳይሆን እርሱ ብቻ ነው። የሁኔታዎች መለዋወጥ የእኛን ደስታ ሊወስኑት አይገባም። አንድ ሰው ሲያነጋግረን ደስ የሚለን፥ ሲያኮርፈን ደግሞ እንድናዝን የሚያደርገን ከሆነ፥ የደስታችንን ቁልፍ በእጃቸው መስጠታችን ይሆናል። በሕይወታችን አስፈላጊ የሆነውን ቁልፍ እንዲይዙ ከፈቀድንላቸው፥ መቼ ደስ እንዲለንና ደስ እንዳይለን ወሳኞቹ እነርሱ እንዲሆኑ ማድረጋችን ነው። ማብሪያና ማጥፊያውን በእጃቸው ከሰጠናቸው፥ እነርሱን ደስ ሲላቸው ደስ እንዲለን፥ እነርሱን አንድ ነገር ቅር ሲያሰኛቸው ደግሞ እኛም ቅር እንዲለንና እንድናዝን የማድረግ ችሎታና ኃይል ይኖራቸዋል ማለት ነው። ለመሆኑ በሕይወታችን ይህን ዓይነቱን ትልቅ ሥልጣን የሰጣቸው ማን ነው? ብለን መጠየቅ አለብን። ይህን ስንል ሌላው በሚያደርገው ክፉ ነገር እኛ አንጎዳም ማለታችን አይደለም። ይሁን እንጂ፥ ምክንያት ፈልገው ባኮረፉ ቁጥር እኛ ላይ የሚጨልምብን፥ ዓለም በላያችን ላይ የተደፋብን ከመሰለን፥ በሳቁና በተጫወቱ ቁጥር ደግሞ ዓለምን በእጃችን የጨበጥን መስሎን ደስ የሚለን ከሆነ፥ የሕይወታችንን አቅጣጫ ወሳኞቹ፥ በሕይወታችን ከፍተኛ ሚና የሚጫወቱ እነርሱ ናቸው ማለት ነው። የደስታችንን ማብሪያና ማጥፊያ ቁልፍ በእጃቸው አንስጣቸው ያልነው ለዚህ ነው።

## (2) <u>ራሳችንን እንመርምር</u>

በሁለት ሰዎች መካከል ኩርፊያ ሲኖር፥ ኩርፊያውን የጀመሩት ከሁለት አንዳቸው መሆን እንዳለባቸው ግልጽ ነው። አልፎ አልፎ የኩርፊያውን ምክንያት ብቻ ሳይሆን፥ ኩርፊያውንም የጀመረው ማን እንደሆነ በግልጽ የማይታወቅበትም ጊዜ አለ። ለዚህ ነው ብዙ ጊዜ አንዱ ሌላውን "...ያኮረፈው እርሱ ነው...እርሷ ነች" በማለት ዝምታውን ለመስበር አንዱ ከሌላው የሚጠብቀው። አስቸጋሪ ሰው ለምን እንዳኮረፈ ሲጠየቅ፥ ለጥያቄው ትክክለኛ መልስ በመስጠት ፈንታ በቁጣ "...ራስህን ጠይቅ... እኔን አትጠይቀኝ..." የሚል መልስ የሚሰጥበት ጊዜ አለ። ይህ ከሆነ ኩርፊያው ከመጀመሩ በፊት የተፈጸሙ አንዳንድ ሁኔታዎችን፥ ለኩርፊያው ምክንያት ይሆናል ብሎ የሚታሰቡትን ነገሮች መመርመር ይጠቅማል። ይህን ማድረግ የሚገባው ለአስቸጋሪው ሰው የሚያኮርፍበትን ምክንያት ወይም ቀዳዳ ላለመስጠት ብቻ ነው። ራስን መመርመር አስፈላጊ ነው። ይሁን እንጂ፥ አስቸጋሪ ሰዎች በአኮረፉ ጊዜ ሁሉ "ምን ተናግሬ ይሆን?... ምን አድርጌ ይሆን?..." እያልን ራሳችንን ማስጨነቅ አለብን ማለት አይደለም። ይሄ የሚያስጨንቀን መሆኑን ሲያዩ አስቸጋሪ ሰዎች ብዙ ጊዜ እንደ ማጥቂያ መሳሪያ አድርገው እንደሚጠቀሙበት የታወቀ ነው። ብዙ ጊዜ ችግሩ ከእኛ ሳይሆን ከራሳቸው የመነጨ ስለሚሆን በኩርፊያቸው ይህን ያህል መጨነቅ የለብንም።

ማድረግ የሚገባትን በትክክል የምታደርገው? እስከ መቼ ድረስ ነው እኔ የእርቧን ኃላፊነት የምሸከመው?..." ብሎ በውስጡ ማሰብና መጠየቅ ጀመረ። ወዲያው "ይህ ዓይነት ጠባይዋ የግድ ከዛሬ ጀምሮ መለወጥ አለበት" ከሚል ውሳኔ የደረሰ ይመስላል። እንደተለመደው "...ግድ የለም ዕራት እኔ እሠራለሁ..." በማለት ፈንታ፣"ያልጨረስኩት ሥራ ስላለኝ ወደ ቢሮ ተመልሼ መሄዴ ነው..." ብሎ ባለችበት ሁኔታ ልጆቹን ትቶላት ወጣ። ዘዴዋ የለመደችውና ዓይነት ውጤት እንዳላስገኘላት ስታውቅ፣ ከተኛችበት ተነስታ እራት ሠርታ ልጆቿን አበላች።

## (V) *"እምቢ!" ለማለት አንፍራ*

"እምቢ!" ማለት መቻል ድፍረትን ይጠይቃል። ጊዜያችንና ጉልበታችንን በአግባቡ መጠቀም ያስችለናል። በእኛና በሌሎች መካከል ያለውን ግንኙነት ጤናማነቱን ይወስናል። "እምቢ!" ማለት ያለአግባብ በሰዎች መጠቀሚያ እንዳንሆን ይረዳናል። ከእኛ ፍላጎት፣ ጊዜና ሁኔታ ጋር የሚጋጨውን፣ አስፈላጊ ያልሆነውን፣ እንዲሁም አግባብነት የሌለውን መምረጥ ያስችለናል። "ጓደኛዬ ታገባለች። ከእኔ ስጦታ ትጠብቃለች። እኔ ደግሞ ገንዘብ የለኝም። ስጦታ የምገዛበት ገንዘብ እባክሽን ስጪኝ" ብላ ለምትጠይቀዋ ሴት የምትሰጣት መልስ ምን ዓይነት ይሆን? "ገንዘብ ቢኖርሽም፣ ያንን ገንዘብ ያጠራቀምሽው የቤት ዕቃ ለመግዛት ብለሽ ይሆናል። ታዲያ ለዚያች ሴት የምትሰጪት መልስ "አልችልም" ነው? በዚህ ዓይነት "እምቢ! አልችልም" የሚል መልስ ቢሰጡ የበደለኛነት ስሜት የሚያስጨንቃቸው ሰዎች አሉ። መልስሽ "እሺ!" የሚል ከሆነ፣ የግል ፕሮግራምሽ፣ እንዲሁም የራስሽ ፍላጎት ሳይሟላ ይቀራል። ኃላፊነት ከሌለብን ለተጠየቅነው ጥያቄ "እሺ!" የሚል መልስ ባለመስጠታችን የበደለኛነት ስሜት ሊሰማን አይገባም። ከራሳችን የተረፈ ጊዜም ሆነ ገንዘብ ሳይኖረን ለሌሎች ማድረግ ትክክል አይደለም። በትህትና "አልችልም..." ለማለት ድፍረት ይኑረን። የተጠየቅነውን ባለማድረጋችን የበደለኛነት ስሜት ቢሰማን፣ የተሰማን ስሜት ትክክል አለመሆኑን እንወቅ።

## (vi) *ልባችንን ብቻ ሳይሆን አዕምሮአችንንም እንጠቀም*

አንዳንዶቻችን ለሰዎች የሚያዝን ልብ ስላለን፣ ችግራቸውን ሲነግሩን ልባችን ስለሚራራ የሚጠይቁንን "እምቢ!" ለማለት ይከብደናል። ልባችን ከአእምሮአችን ጋር በሕብረት ካልሠራ፣ ትልቅ ችግር ውስጥ ራሳችንን እንጥላለን። አንድ ጊዜ አንድ ሰው ስልክ ደወለና እያለቀሰ የደረሰበትን ችግር አጫወተኝ። ሁኔታው በጣም ልቤን ስለነካኝ አዕምሮዬን ሳላማክር፣ ወይም እንደሚገባው ሳላስብ፣ በርህራሄ ስሜት ተሞልቼ ያ ሰው የጠየቀኝን ነገር አደረግሁለት። ከአእምሮዬ ጋር ብማከር ኖሮ፣ ያ ሰው ገንዘቡን ያለአግባብ፣ ወይም አስፈላጊ ባልሆነ ነገር ዝም ብሎ የሚያባክን መሆኑን ተረድቼ፣ "...አዝናለሁ.... ልረዳህ አልችልም..." እለው ነበር። ይህን ማለት ብችል ኖሮ ገንዘቤንም ሆነ ከዚህ ሰው ጋር ያለኝን ግንኙነት ማዳን እችል ነበር። ይህ ሰው በችግሩ ጊዜ የደረስኩለት ባለውለታ አድርጎ በማየት ፈንታ ገንዘቡን ባለመክፈሉ የተነሳ በተቻለው መጠን ከእኔ እንደሚሸሽ የታወቀ ነው። ልባችንን በማስቀደም ለውሳኔ ከመሮጣችን በፊት፣ የሰውየውን ሁኔታ ለመመርመር አዕምሮአችንን እንጠቀምበት። ልባችን ከአዕምሮአችን ጋር ሕብረት ሳይኖረው በምንወስደው እርምጃ መታለላችን ብቻ ሳይሆን፣ እንረዳዋለን ያልነውን ሰው የምናበላሸው መሆናችንን፣ ራሱን ችሎ እንዳይቆም የምናደርገው መሆናችንን ማወቅ አለብን።

## (vii) *ፊት ለፊት መጋፈጥ (confrontation) የሚያስፈልግበት ጊዜ እንዳለ እንወቅ*

የብዙዎቻችን ችግር 'አስቸጋሪ ነው" ከምንለው ሰው ጋር ፊት ለፊት መጋፈጥ ድፍረት ስለማይኖረን ነው። ፊት ለፊት ለመጋፈጥ ድፍረት በማጣት የአስቸጋሪው ሰው መጠቀሚያ በመሆናችን፣ በውስጣችን የምናጠራቅመው ቅሬታ ትልቅ ጉዳት ላይ የሚጥለን መሆኑን አንገነዘብም። በውስጣችን ያጠራቀምነው እያደገ ሄዶ አንድ ቀን ፈንድቶ ችግር ውስጥ ይጥለናል። "...ከራስህ በስተቀር ሌላ ማየት አትችልም... አሁንስ ልታሳብደኝ ነው..." ብለን የምንጮኽበት ጊዜ ይመጣል። ትክክለኛው መንገድ አስቸጋሪውን ሰው ፊት ለፊት በመግጠም መጥፎ ስሜት እንዲሰማን ያደረገን መሆኑን መግለጽ ይገባል። "ፊት ለፊት መግጠም" የሚያስፈራ ቢሆንም፣ በውስጣችን ቅሬታ ከማጠራቀም ግን ይሻላል። ፊት ለፊት መግጠም፣ አስቸጋሪ ሰዎች ራሳቸውን እንዲያዩ ፊት ለፊታቸው መስታወት ማቅረብ ማለት ነው። አንዳንዶቹ ጠባያቸው የሚፈልጉትን ነገር ያስገኝላቸው እንጂ፣ በሌላው ሰው ሕይወት ውስጥ የሚያመጣው ጉዳት ምን ያህል ትልቅ እንደሆነ ግን አያውቁም። እነርሱ ያጋጠማቸውን ችግር በነጻነት ለመናገር ድፍረት ካላቸው፣ እኛም የራሳችንን ችግር ለመናገር የምንፈራበት ምክንያት የለንም።

# 7 የተለዋዋጭነት ባሕሪ ካለው ሰው ጋር እንዴት መኖር እንችላለን?

አንዳንድ አስቸጋሪ ሰዎች ስሜታቸው ቶሎ ቶሎ ስለሚለዋወጥ እውነተኛው አቋማቸው በትክክል አይታወቅም። የግልፍተኛነት፣ የማኩረፍ፣ "አትንኩኝ" ባይነታቸውና፣ እንዲሁም ቶሎ ቶሎ የመለዋወጥ ባሕሪ ያላቸው በመሆናቸው

ከእነርሱ ጋር ተዝናንቶ መኖር ከባድ ነው። እንዲህ ዓይነት የተፈጥሮ ባሕሪ ያላቸውን ሰዎች፥ እንግሊዝኛ ተናጋሪዎች፥ "ስሜቷን በእጅጌዋ ለብሳዋለች" "She wears her feelings on her sleeve" የሚል አነጋገር አላቸው። ስሜታዊነታቸው ተገልጾ ሲታይ መካከለኛነትን የያዘ ሳይሆን፥ ሁልጊዜ ከመጠን ያለፈ (extreme) ነው። ስሜታዊነት ያለባቸው ሰዎች የሚሰጡትም መልስ ሆነ፥ ሆነው የሚገኙት "ናቸው" ተብለው እንደሚጠበቁት አይደለም። አብሯቸው ያለ ሰው ሁልጊዜ "ዛሬ ምን ይሆኑ ይሆን?" እያለ በስጋትና በፍርሃት የሚኖር ነው። ከላይ የገለጽነውን ዓይነት ተለዋዋጭ ባሕሪ ካለው ሰው ጋር ታርቆ በሰላም መኖር ማለት፥ "ሚስማር የቀደደውን ጎማ በዓየር እንደ መሙላት" ነው። አሁን ደህና ናቸው ሲባሉ፥ ትንሽ ቆይተው ይተነፍሳሉ። አብረዋቸው የሚኖሩ ሰዎች ውሳኔ አሰጣጣቸው የእነርሱን ስሜት እየተከተሉ እንዳይሆን አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው። ምናልባት "ዛሬ" ጥሩ ሆነው ሲያገኟቸው መለወጣቸው ነው ብለው በማሰብ ራሳቸውን ዝርግፍግፍ አድርገው ለአስቸጋሪው ሰው እንዳይሰጡ፥ ወይም ያበጁትን ድንበር (boundary) እንዳያፈርሱ መጠንቀቅ አለባቸው።

ስሜታቸው በተለዋወጠ ቁጥር አብሯቸው የሚኖረውም ሰው ስሜት መለዋወጥ የለበትም። እነርሱ የሀዘን ስሜት ከተሰማቸው፥ በአካባቢያቸው የሚኖሩት ሰዎች ሁሉ ሀዘንተኛ እንዲሆኑ የማድረግ ዝንባሌ ያላቸው ስለሆኑ፥ የደስታቸውም ሆነ የሀዘናቸው ማብሪያና ማጥፊያውን ለአስቸጋሪ ሰዎች መስጠት የለባቸውም። እነርሱ ካዘኑ፥ ሌላው ሁሉ ማዘን አለበት፥ እነርሱ ከተጨነቁ፥ ሌላው ሁሉ መጨነቅ አለበት። እነርሱ ካላቸው ስሜት ውጪ የተለየ ስሜት ካለው ያ ሰው የችግራቸው ሁሉ ምክንያት አድርገው ስለሚመለከቱት በትንሹም ሆነ በትልቁ "ውሃ ቀጠነ" በማለት ሲቃዩን ያበሉታል። ከአስቸጋሪ ሰዎች፥ ጠባያቸው እንደ እስስት በየደቂቃው ከሚለዋወጥ ሰዎች ጋር ተቀራርበው የሚኖሩ ሰዎች በተቻላቸው መጠን፥ የአስቸጋሪው ሰው ስሜት እነርሱ ላይ እንዳይረጭ ራሳቸውን መከላከል አለባቸው። በስሜታቸው ተለዋዋጭ የሆኑ ሰዎች የራሳቸውን ጉልበት በሚረባውና በማይረባው ነገር ጨርሰው፥ አጠገባቸው የሚኖረውን ሰው ጉልበት ለማዳከም የሚፈልጉ ናቸውና ለእነርሱ "የእጅ ጥም ዘዛ ዘዴ" እምቢ! ማለት መቻል ያስፈልጋል።

ተለዋዋጭ ባሕሪ እንዳላቸው የሚታወቀው ድንገት በሚያሳዩት ቁጣ ወይም ንዴት ነው። ብዙ ጊዜ ምን እንደሚያስቆጣቸው አይታወቅም። ቀረብ ብሎ ለማያውቃቸው፥ ወይም ለሩቅ ሰው ደግ፥ ትሁት፥ ፍጹም ልዝብ ምላስ ያላቸው፥ በጥሩ ጠባያቸው ተወዳዳሪ የሌላቸው ይመስላሉ። አብሯቸው ለሚኖረው ሰው ግን "እንደ እሳተ ጎሞራ" የሚፈነዳ ቁጣ የሚታይባቸው ናቸው። በአንድ ዓይነት ምክንያት ቁጣቸው ከውስጥ ሲገነፍል፥ ለቁጣቸው ምክንያት ነው ብለው በሚያስቡት ሰው ላይ አጠገባቸው ያለውን ዕቃ አንስተው ሲወረውሩ፥ ከአፋቸው የሚወጣው ስድብ፥ ክፉ ቃል ፍጹም ሌላ ነው። ራሳቸውን መቆጣጠር ፈጽሞ አይችሉም። ይሁን እንጂ ቁጣቸው ሲበርድ፥ አንዳንዶቹ በራሳቸው ድርጊት አዝነው ቁጭ ብለው ያለቅሳሉ። የጎዱትንም ሰው ይቅርታ ይጠይቃሉ። ይህን ዓይነት ባሕሪ ካላቸው ጋር ቁጭ ብሎ መወያየት፥ ወይም አጸፋውን ስመመለስ ከእነርሱ ጋር መጯጯኽ ፈጽሞ ጥቅም የለውም። በጸጸት አልቅሰው ይቅርታ ሲጠይቁ፥ "ተለወጡ! ከዚህ በኋላ ችግር አይኖርባቸውም..." ብሎ ማሰብና መገመት ትክክል አይደለም። ከጥቂት ሰዓት በኋላ ቀደም ሲል ካደረጉት የበለጠ የከፋ ነገር ሲያደርጉ ይታያሉ። እንደነዚህ ዓይነቶቹን ይለወጣሉ ብሎ ማሰብም ሆነ ለመለወጥ መሞከር በጣም ከባድ ነው። ሆኖም በሚያደርሱት ጉፋት ምክንያት ከጉዳት ለማምለጥ አብሯቸው የሚኖረው ሰው ብርቱ ጥንቃቄ ማድረግ አለበት።

በቁጣቸው ወቅት የሚወረውሩት አፍራሽ ቃል፥ አጠገባቸው ሆኖ የሚያዳምጠው ሰው፥ "ስለ እኔ የተናገረው ነገር ልክ ነው..." ብሎ እንዳይቀበል ራሱን መጠበቅ አለበት። እነዚህ ከተደባደቡ፥ ከተሳደቡ፥ የልባቸውን ካደረሱ በኋላ መልሰው የሚያለቅሱ *"የተቃወሰ ገጸባሕሪ" (character disorder)* ያለባቸው ሰዎች የሥነ-ልቦና ችግር ያለባቸው ሰዎች በመሆናቸው፥ አብሯቸው በሚኖረው ሰው ላይ የበለጠ አደጋ ሊያደርሱ ስለሚችሉ ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረጉ ይጠቅማል። የፈለጉትን ለማድረግ ድፍረት ያላቸው ሰዎች መሆናቸውን ተመልክተን፥ ብርቱዎች፥ ሁሉን ነገር በቁጥጥራቸው ማዋል የቻሉ ይምሰሉን እንጂ፥ ገልጸው ባይናገሩትም ስለ ራሳቸው ያላቸው አስተያየት በጣም ዝቅተኛ፥ ደስታ የሸሻቸውና ሁኔታዎች እንደሚፈልጉት ያልሆነላቸው ሰዎች ናቸው። ባደረጉት ነገር ተጸጽተው ቢያለቅሱ ይቅርታ መስጠት እንጂ፥ "ተለውጠዋል... መጥፎ ጸባያቸው ከዚህ በኋላ አይታይም..." በሚል እምነት ከእነርሱ ጋር የነበረውን የገደብ መስመር ማፍረስ፥ ራስን ችግር ውስጥ መክተት ይሆናል። ይቅርታ ሲጠይቁ መከልከል የሌለባቸው ምክንያት፥ ተጠቃሚዎቹ ይቅርታ ሰጪው ሳይሆን እነርሱ ናቸው። ይቅርታ መስጠት ማለት በጥፋ ሲጠፋፉ፥ በእርግጫ ሲረገጡ፥ እርግጫውንም ሆነ ጥፊውን ዝም ብለው መቀበል አለባቸው ማለት አይደለም። እንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ እነርሱንም ቢሆን ይጎዳቸዋል እንጂ አይጠቅማቸውም።

ሳዋኝ..." ብለን እንውቀሳቸው። ይሄ ሁኔታውን የበለጠ ያባብሰዋል እንጂ ኢያሻሽለውም።

(3) ሌላውን የመቆጣጠር ፍላጎት ላለው ሰው፥ የበለጠ እንዲያውቀን ዕድል እንስጠው። ለጥቃቅኑ ነገር ሁሉ መመሪያ መስጠትና መቆጣጠር ለሚፈልግ የሥራ አለቃ ተበሳጭተን፥ "...ሥራዬን እንድሠራ፥ ኃላፊነቴን እንድፈጽም... ራሴን ችዬ እንድሠራ ለቀቅ አድርገኝ...." ማለቱ አይጠቅምም። ራሳችንን ችለን፥ እንዲሁም ጥሩ አድርገን እንደምንሠራ እንዲያይ ለአለቃችን ዕድል እንስጠው። ሌላውን የመቆጣጠር ፍላጎት ወይም ጥማት ካላቸው ሰዎች ጋር በመጠኑም ቢሆን ከተባበርን፥ መዝናናት ስለሚችሉ ቁጥጥራቸውን ማላላት ይጀምራሉ። ሊቆጣጠሩን ሲሉ ረጋ ብለን ሥራችንን መሥራታችንን ሲያዩ፥ በእኛ ላይ ያላቸው እምነት ይጨምርና በእኛ ላይ የሚያደርጉትን ቁጥጥር ይቀንሳሉ።

(4) ሌላውን የመቆጣጠር ፍላጎት ያላቸው ሰዎች፥ ቁጥጥራቸውን የምናከሽፍበት ሌላው መንገድ ከእኛ ምን እንደሚፈልጉ ለናውቅ ነው። አንዳንድ ሰዎች አለቃ መሆናቸውን፥ኃይልና ሥልጣን እንዳላቸው ሌላው ሰው እንዲያውቅላቸው ይፈልጋሉ። የራሳችንን ፍላጎት ችላ ሳንል፥ የሚፈልጉትን አውቆ መስጠት በመካከላችን ያለውን ግንኙነት ኢያሻክርም።

(5) ሌላውን የመቆጣጠር ፍላጎት ካላቸው ሰዎች ጋር የተቀራረበ ግንኙነት ካለን፥ በአንድ ጉዳይ ላይ በመደጋገም መጨቃጨቃችን ወይም መከራከራችን አይቀርም። ሁልጊዜ የምንከራከርበትን ጉዳይ ለይተን ካወቅን፥ ቁጭ ብለን መወያየት ይጠቅማል። ለምሳሌ "መኪና ስትነዳ እንዲህና እንዲያ አድርግ..." ኢያለ የሚተች ከሆነ፥ ይህንን በማድረግ ፈንታ፥ አብረው በሚሄዱበት ሥፍራ ሁሉ የተሻለ ሹፌር ነው የሚባለው ሰው እንዲነዳ ማድረግ የተሻለ ነው። በስምምነት አንዱ እንዲነዳ ከተደረገ በኋላ በሌላ ጊዜ መተቸት ሲጀምር፥ "ከዚህ በፊት ተወያይተን እኔ መኪና እንድነዳ ስለተወሰነ አንተ ምንም ማለት የለብህም..." ማለት እንችላለን። በዚህ ዓይነት በመካከላችን ግጭት እንዳይፈጠር ማድረግ እንችላለን።

(6) በአንዳንድ ሁኔታዎች ላይ፥ ሌላውን የመቆጣጠር ፍላጎት ያላቸው ሰዎች ምንም ብናደርግ አይለወጡም። ሁሉን ነገር ሞክረን የማይለወጡ መስሎ ከታየን፥ እነርሱን ለመለወጥ ወይም ለማሻሻል ዝም ብለን መታገሉ መልሶ የሚጎዳው እኛኑ ነው። ለምሳሌ የመሥሪያ ቤት አለቃችን እንዲህ ዓይነት ባሕሪ ካለው፥ ሥራችንን እንድንጠላው እንደሚያደርገን የታወቀ ነው። መሥሪያ ቤቱን ጥለን ብንሄድ የሚደርሰብን ጉዳት የበለጠ መስሎ ከታየን፥ ሁኔታውን ተቀብለን በትዕግሥት ማለፍ አለብን።

## 9. የተበቃይነትና የቂመኛነት ባሕሪ ካለው ሰው ጋር እንዴት መኖር እንችላለን?

በደል ወይም ጉዳት ባደረሰበት ሰው ላይ የበቀል እርምጃ መውሰድ የሰው ሁሉ ዝንባሌ ነው። አጸፋውን የሚመልሰበትም የራሱ የሆነ መንገድ አለው። አንዳንዱ የበደለውን ሰው በመበቀል ፈንታ "በቀል የጌታ ነው" በማለት ነገሩን የተወ ይምሰል እንጂ፥ የደረሰበትን በደል በልቡ የማያጠራቅም፥ ቂም የሚይዝ አለ። ሌላው ደግሞ "በደለኝ" የሚለውን ሰው ባይበቀልም፥ የጎዳው ሰው በበደለኛነት ስሜት እንዲጨነቅ የሚያደርግ ነው። በተበቃይነታቸውና በቂመኛነታቸው አሰቸጋሪ ሰዎች ናቸው የምንላቸው ከላይ ከገለጽናቸው በጣም ይለያሉ። በተበቃይነታቸው አሰቸጋሪ የሆኑ ሰዎች ራሳቸውን ለመከላከል፥ ወይም "አጠቃን" ብለው በሚያስቡት ሰው ላይ የሚወሰዱት እርምጃ ትክክል መሆኑን ለማሳመን "እኔ ጥቃት አልወድም፤ ያጠቃኝን መልሼ ሳላጠቃ እንቅልፍ አይወስደኝም" በማለት የራሳቸውን እርምጃ ይወስዳሉ። በመሠረቱ ጥቃት ሲደርስበት ደስ የሚለው ወይም የማይቆረቁረው ሰው ማንም የለም። ይሁን እንጂ፥ ጥቃት የደረሰበት ሁሉ "አጠቃኝ" የሚለውን ሰው መልሶ ማጥቃት በግንኙነታቸው ላይ ያለውን ችግር ያቃልላል ማለት አይደለም።

በቀል ለጊዜው ራስን ከጥቃት የሚጠብቅ፥ እርካታን የሚሰጥ ይምሰል እንጂ፥ እንዴ ከገቡበት መውጣት አስቸጋሪ ነው። ቻይናዎች "ለመበቀል ራሱን የሚያዘጋጅ ሰው አስቀድሞ ሁለት መቃብር መቆፈር አለበት" የሚል አባባል አላቸው። ይህንን ሲሉ አንዱ መቃብር ለራሳቸው፥ ሌላው ደግሞ ለሚበቀሉት ሰው ማለታቸው ነው። ለመበቀል የሚሰማን ግፊት፥ ጠላታችን በእኛ ላይ ኃይል እንዲኖረው ጉልበቱን ያጠነክርለታል። አንድ ሰው "አሲድ የበለጠ የሚጎዳው የፈሰሰበትን ሰው ሳይሆን፥ አሲዱን የያዘውን ዕቃ ነው" አለ። ብዙ ጊዜ በቀልን "በቀል" ብለን በመጥራት ፈንታ፥ "ራስን መከላከል፥ ሊጎዳን ከሚሞክረው ሰው ራስን መጠበቅ ነው እንላለን። አንድ ክርስቲያን ጸሐፊ "ራስን መከላከል ለተጠቃሚው ጥሩ ይምሰል እንጂ፥ ሌሎች እንዳይጠጉን የሚያደርግ ነው። ራስን መከላከል ልባችንን ይሸፍናል፤ እንዲያውም ለሚያጠቁን ሰዎች መሳሪያ ያስታጥቃል" አለ። እርግጥ ነው የምንኖረው "ያጠቃውን መልሶ ማጥቃት" የሚል ፍልስፍና ባየለበት ዘመንና ሕብረተሰብ ውስጥ ነው። "ክብራ

ችን እንዳይደፈር መከላከል አለብን" በሚል ካባ ሰዎች እርስ በርሳቸው ጥርስ ሲሳበሩ ማየት የተለመደ ሆኗል።

ከሁሉም የተሻለው የክርስቶስ መንገድ ነው። ያም በቀልን በበቀል በመመለስ ፈንታ አስቸጋሪ የሆነብንን ሰው ለመውደድ ራስን በማለማመድ ነው። አስቸጋሪ ሰዎች በጣም የሚጠቅማቸውን ሰው፣ "ያለ እርሱ መኖር አልችልም" የሚሉትን ሰው፣ "ሊጎዳኝ ይህንና ያንን አድርጎብኛል..." በማለት መበቀል ይፈልጋሉ። እነርሱ እንደሚያደርጉት መልሶ እነርሱን መበቀል ክርስቲያናዊ መንገድን መከተል አይደለም። ኢየሱስ የመረጠልን መንገድ መበቀል ሳይሆን፣ መውደድ ነው። *"...እኔ ግን እንዲህ እላችኋለሁ፤ ጠላቶቻችሁን ውደዱ፤ ስደትና መከራ ለሚያደርጉባችሁ ጸልዩላቸው"* ይላል (የማቴ. 5፥44)። ጠላቶቻችንን መውደድ በሰው ግምት የሚቻል አይመስልም። ይሁን እንጂ፣ ኃይል ሳይሰጠን እንዲሁ የማንችለውን ነገር "አድርጉ" ብሎ ስለማያዘን፣ ጠላትን መውደድ ይቻላል። ኢየሱስ ከሞተና ከተቀበረ አራት ቀን ያለፈውን፣ ሕይወት የሌለበትን ሰው "አልአዛር ና ውጣ..." አለው። ለሞተ ሰው ይህን ዓይነት ትዕዛዝ መስጠት በሰው ዘንድ ሞኝነት ይመስላል። ይሁን እንጂ፣ ኢየሱስ በውስጡ ሕይወትንና ኃይል እንደ ገና ስላኖረ አልአዛር በመታዘዝ ከመቃብር ወጣ። ልክ እንደዚሁ ኢየሱስ "ጠላቶቻችሁን ውደዱ..." የሚል ትዕዛዝ ሲሰጥ፣ መውደድ የምንችልበትን ኃይል ይሰጠናል። እዚህ ላይ ጥያቄው ጠላታችንን መውደድ እንችላለን ወይ? የሚል ሳይሆን፣ ለመውደድ ፈቃደኞች ነን ወይ? የሚል መሆን አለበት። ማየት ያለብን ስሜታችንን ሳይሆን፣ ፈቃደኞች መሆናችንን ነው።

8

# ከአስቸጋሪ ሰው ጋር መኖር የማይቻል ከሆነስ?

አስቸጋሪ ከሆነብን ሰው ጋር ያለን ግንኙነት አሳሳቢ የሚሆንብን፣ በእኛና "አስቸጋሪ ሆነብን" በምንለው ሰው መካከል ያለው ግንኙነት (relationship) ወይም አንድነት በሕይወታችን ውስጥ ከፍተኛ ሥፍራ የምንሰጠው ሲሆን ብቻ ነው። ከዚህ ሰው ጋር ያለን ግንኙነት ይህን ያህል የማያስፈልገን ከሆነ፣ ስለሚያደርገውና ስለማያደርገው ነገር ይህን ያህል አንጨነቅም። ግንኙነቱ (አንድነቱ) ይህን ያህል በጣም የሚያስፈልገን መስሎ ካልታየን፣ ከሁኔታው ገለል ብለን ትርፋችንና ኪሳራችንን መመዘን እንችላለን። እንዲሁም እንዳንንዳ ከአስቸጋሪው ሰው አካባቢ መሸሽ የምንችልበትን ሁኔታም ሆነ ዘዴ እንፈልጋለን። በግንኙነቱ ውስጥ ምን እንደምንፈልግ ራሳችንን ጠይቀን ከተረዳን በኋላ፣ በሌላው ወገን ያለው እንጂ እኛ የምንፈልገውን ማግኘት የማንችል መስሎ ከተሰማን፣ በግንኙነቱ ውስጥ ወደ ፊት ላለመቀጠል መወሰን እንችላለን። ባለን ግንኙነት (relationship) ውስጥ ኃይለኛ ግፊት ወይም ችግር እንዳለ ሲሰማን፣ ራሳችንን

ላይ በዕሁድ ምሽት ስብሰባቸው ላይ፥ ዶክተር ሀሮልድ ስሚዝ ባለፉት አም ስት ዓመት በቤተ ክርስቲያናቸው ውስጥ በጣም ትልቅ ችግር ያደረሰባቸውን ሰው ስም ገልጠው የሚናገሩ መሆናቸውን ዕሁድ ዕሁድ በሚወጣው የከተማው ሳምንታዊ ጋዜጣ ላይ ማስታወቂያ አወጡ። ይህም ብዙዎችን ያስደነቀና ያስደ ነገጠ ማስታወቂያ ነበር። ይሁን እንጂ፥ በቅርብ ከሚያውቋቸው ሰዎች መካከል ዶክተር ሀሮልድ ይህን አያደርጉም ብሎ የተጠራጠራቸው ሰው አልነበረም። ከቤተ ክርስቲያኒቱ አባሎች መካከል "አስቸጋሪ ሰው የሚለው እኔን ከሆነ እከ ሳለሁ" በማለት የራሳቸውን የሕግ ጠበቃ ቤተ ክርስቲያን ይዘው የመጡ ክርስ ቲያኖችም ነበሩ። በዚያን ምሽት ቤተ ክርስቲያኗ ጢቅ ብላ ሞልታ ነበር። ዶክተር ሀሮልድ ስሚዝ የምሽቱ የስብከታቸው ክፍል ከሮሜ 7፥24 ላይ የተወ ሰደ፥ *"...እኔ ምንኛ ጎስቋላ ሰው ነኝ፥ ወደ ሞት ከሚወስደኝ ከዚህ ሰውነትስ ማን ያድነኛል?..."* የሚለው ነበር። ሕዝቡም ማንን ሊጠቅሱ ነው ብሎ በስጋትና በድንጋጤ ላይ እያለ፥ *"ባለፉት አምስት ዓመት በዚህች ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ትልቅ ችግር የፈጠረብኝ ሰው፥ ሀሮልድ ስሚዝ ነው..."* በማለት የራሳቸውን ስም ጠቀሱ። እኚህ ታላቅ ሰባኪ በአገልግሎቴ ውስጥ አስቸጋሪ የሆነብኝ ሰው ሌላ ሰው ሳይሆን እኔው እራሴ ነኝ" ማለታቸው ነበር። የብዙዎቻችን የችግራ ችን ዋና ምክንያት ሌላ ሰው ሳይሆን፥ እኛው ራሳችን ልንሆን እንችላለን። ስለ ዚህ ከሰዎች ጋር ያለን ግንኙነት ጤናማ ያልሆነበት ምክንያት እኛው ራሳችን መሆን አለመሆናችንን በቅድሚያ ራሳችንን መመርመሩ፥ ለችግራችን አፋጣኝ የሆነ መፍትሄ ሊያስገኝልን ይችላል።

አንድ ሌላ የቤተ ክርስቲያን መጋቢ፥ *"ቃሉን ፊት ለፊት በግልጽ በማስተ ማሬ ምክንያት ከአገልግሎቴ ተባረርኩ"* በማለት ለአንድ ሰው አጫወቱት። ያ ሰው አኛ ፓስተር ሲሰብኩ ሰላልሰማቸው "እንዴት ቃሉን በመስበካቸው ከአገ ልግሎታቸው ያባርሯቸዋል?" በማለት በጣም አዘነላቸው። አንድ ቀን የእኛን መጋቢ ስብከት ለመስማት ዕድል አጋጠመው። የእኚህ መጋቢ ስብከት የራብ መመጻደቅ የበዛበት፥ ሌላውን የሚኮንን፥ መሆኑን ከሰማ በኋላ የቤተ ክርስቲ ያኑ ምዕመናን እኚህን ሰው ማባረራቸው ልክ ነው፤ እኔም ድምጽ ስጥ ብባል 'ይሂዱ' እል ነበር አለ። ብዙዎቻችን ብዙ ጊዜ አዕምሮአችን በብዙ ነገር ስለተሞላ፥ የራሳችንን ሕይወት ለማየትም ሆነ ለመመርመር ጊዜ የለንም። ዳዊት ከእግዚአብሔር ጋር የድብብቆሽ ጨዋታ በሚጫወትበት ዘመን፥ ኃጢአቱን ሸፍኖ፥ አረሳስቶ ለማለፍ ያደረገውን ከፍተኛ ጥረት እናስታውሳለን። እግዚአ ብሔር መልዕክተኛውን ናታንን ልክ አንድ ሃብታም ሰው የድኻውን አንዲት በግ አርዶ እንግዳውን እንዳስተናገደበት ሲነግረው፥ ያን ዓይነት ግፍ የሚሠራ ሰው "እኔ አሆናለሁ..." ብሎ ሰላልገመተ፥ *"...ዳዊት በሀብታሙ ሰው ታሪክ ኢጅግ ተቆጥቶ ይህን ያደረገው ሰው ሞት እንደሚገባው በሕያው እግዚአብሔር ስም እምላለሁ..."* (2 ሳሙ. 12፥5) በማለት ፍርዱን ወዲያው ማስተላለፉን እናው ቃለን። የዳዊትን ፍርድ ከሰማ በኋላ ናታን "ያ ሰው አንተ ራስህ ነህ!" አለው። ዳዊት ያ ሰው እርሱ ራሱ መሆኑን አስቀድሞ ቢያውቅ ኖሮ ያንን የመሰለ ፍርድ አያስተላልፍም ነበር። አስቸጋሪው ሰው በሌላው ወገን ያለው ሰው ነው ከማለት በፊት "ችግሩ ያለው እኔው ላይ ይሆን?" በማለት በቅድሚያ ራሳችንን መመርመር ጠቃሚ ነው።

ከአስቸጋሪ ሰው ጋር ስንኖር፥ ወይም ስንቀራረብ ራስን መመርመር በጣም ጠቃሚ ነው። ራሳችንን መርምረን ችግር ካለብን፥ ችግራችንን ከማስተካከ ላችን ወይም ራሳችንን ከማረማችን በፊት ሌላው ሰው አስቸጋሪ የሆነበትን ምክንያት መረዳት ይከብደናል። ነገር ግን በጥንቃቄ ራሳችንን መርምረን ሌላው ሰው በእኛ ሕይወት ውስጥ የሚጠላው ባሕሪ ምን እንደሆነ አውቀን ራሳችንን ስናስተካክል፥ የመለወጥ ተስፋ ያለው ሰው ከሆነ፥ ራሱን ለመለወጥና ለማስተካ ከል በበኩሉ ጥረት ያደርጋል። የማይስተካከልም ከሆነ፥ የራሳችን ሀሊና ፍጹም ንጹህና የሚቆረቁረን ምንም ነገር እንደሌለ ለማረጋገጥ፥ ካለም በእግዚአብሔር ፊት ንስሀ ለመግባትና እርምጃችንን ለማረም ይረዳናል። ራሳችንን ስንመረምር በጥንቃቄ መመልከት ያለብን ሁኔታዎች አሉ፥

## 1.1. የምንሠራው ትክክል ያልሆነ ነገር እንዳለ ራሳችንን እንመርምር

አስቸጋሪ ሰዎች ሁልጊዜ በደለኞችና የችግራቸው ሁሉ ምክንያት የሚያ ደርጉት እኛን እንደሆነ የታወቀ ነው። እነዚህ አስቸጋሪ ሰዎች ከአፋቸው የሚ ወጣውን ስድብ፥ ወይም "እንዲህ ናችሁ" ብለው የሚከሱንን በመስማት ራሳች ንን ተጠራጥረን ሳይሆን፥ በእግዚአብሔርም ሆነ በሰው ፊት ሁልጊዜ ያለነቀፋ መሆን ስላለብን፥ ልባችንን መመርመርና መጠበቅ የግድ ያስፈልገናል። ራሳ ችንን ስንመረምር ከሰው ጋር ያለንን ግንኙነት ሊያሻክር የቻለ በደል በውስጣ ችን ቢኖር፥ በጌታ ፊት ንስህ ገብተን ራሳችንን እናስተካክላለን። አስቸጋሪ በሆ ነብን ሰው ላይ ያደረግነው ትክክል ያልሆነ ነገር ከሌለ፥ ሀሊናችንን የሚቆረቁ ረን በደል በእነርሱ ላይ ካልሠራን ግን፥ የሚሰድቡን ስድብም ሆነ ክስ እንዳይ ቆረቁረንና ወደ ውስጣችን እንዳናስገባ ራሳችንን መጠበቅ ያስችለናል። የመ ጠራጠርና ያለማመን ችግር (Paranoia) ያለባት ሴት፥ ባሏን "ከሌላ ሴት ጋር ያመነዝራል..." በማለት ትከሰዋለች። ይህን ዓይነት ክስ የሚቀርብበት ባል፥ ሚስቱ እንድትጠራጠር የሚያደርጋት በደል በውስጡ መኖሩን ራሱን መመር መር እንዳለበት ግልጽ ነው። ጤናማው ሰው ራሱን መመርመርና ራሱን ከኃ ጢአት መጠበቅ ያለበት ለአስቸጋሪው ሰው ሲል ሳይሆን፥ ለራሱ የግል መንፈ ሳዊ ሕይወት ሲል መሆን አለበት። ያለማመንና የመጠራጠር ችግር ያለባቸውን ሰዎች ለመርዳት በጣም አስቸጋሪ ነው። አንድ ጊዜ ያለማመንና የመጠራጠር

ጣጠር ወይም የመምራት ኃይል አስቸጋሪው ሰው በሚፈጥራቸው አንዳንድ ችግሮች ምክንያት እንደተወሰደባቸው ይገነዘባሉ። ቀደም ሲል ከዚህ አሁን አስቸጋሪ ከሆነባቸው ሰው ጋር ጥሩ ኅብረትና አንድነት በነበራቸው ወቅት የራሳቸው የሆነ የሚወዱትና የሚጠሉት፥ ወይም "የእኔ ነው" የሚሉት ነገር ነበራቸው። ግንኙነታቸው በመቆየት እየዳበረ ሲሄድ፥ የራሳቸውን ፍላጎት ወደ ጎን አድርገው፥ ያ ሰው የሚፈጥረውን ችግር መስመር ለማስያዝ ሲጣጣሩ የራሳቸውን ፍላጎት መተው ወይም ወደ ጎን ማድረግ ይጀምራሉ። ይህን ለውጥ ሁሉም ወዲያው አይገነዘቡም። "አሁንማ የራሴን ነገር ትቼ የማስበው ስለ እርሱ ወይም ስለ እርሷ ችግር ብቻ ነው..." የማለት ግንዛቤ አይኖራቸውም። እንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ የሚፈጠረው ቀስ በቀስ ስለሆነ፥ ብዙው ጊዜያቸውና ጉልበታቸው አስቸጋሪው ሰው የሚፈጥረውን ችግር ለመፍታት ወይም መስመር ለማስያዝ የሚያጠፉ መሆናቸውን ብዙዎች አይገነዘቡትም። ሕይወታችን የተለያዩ ችግሮችን ለመፍታት ከምናደርገው እንቅስቃሴ ጋር የተያያዘ ነው። ብዙ ጊዜ ጉልበታችንን እና ጊዜያችንን መስዋዕት አድርገን በመስጠት ብዙ አስቸጋሪ የሆኑትን ነገሮች በተሳካ ወይም ውጤት ባለው ሁኔታ መስመር እናስይዛለን። በመሥሪያ ቤታችን አንዳንድ ችግር ሲያጋጥመን፥ ከሚመለከተው ሰው ጋር ተገናኝተን በውይይት እንፈታዋለን። ከጓደኞችን ጋር አንዳንድ ያልተስማማንበት ነገር ካለ ፊት ለፊት ተገናኝተን በመነጋገር ሁኔታዎችን እናስተካክላለን። ከአስቸጋሪ ሰው ጋር የሚኖረንን ችግር ለመፍታት ከላይ እንዳየናቸው ሁኔታዎች ቀላል አይሆኑልንም። ጤናማ የሆነ ውይይት በማካሄድ አስቸጋሪው ሰው እንዲረዳ ለማድረግ የምናደርገው ጥረት ውጤት አይኖረውም። የአስቸጋሪ ሰዎችን ባሕሪና ሁኔታ ትክክለኛ የሆነ መረዳት ስለሌለን፥ "እነዚህ ሰዎች የተለዩ ናቸው" ብለን ዞር በማለት ፈንታ፥ ፍላጎታቸውን ለማሟላት የበለጠ ጥረት እናደርጋለን። ይዘን የነበረውን አንዳንድ ነገር ቀስ በቀስ ለእነርሱ እየለቀቅን እንመጣለን። "ምናልባት ይህን ባደርግ በመካከላችን ሰላም ማምጣት እችል ይሆናል" ብለን ከመንገዳችን ወጥተን እነርሱን ለማስደሰት አንዳንድ ነገሮችን እናደርጋለን። አስቸጋሪ የሆኑብን ሰዎች አማኞች ከሆኑ፥ ምናልባት ዓይናቸውን ይከፍትላቸው ይሆናል ብለን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ እናነብላቸዋለን። በአጋጣመን ችግር ላይ ምክር እንዲሰጡን አንዳንድ ሰዎችን እንጠይቃለን።

ከላይ ያየናቸውን ነገሮች ሁሉ ማድረጋችን ክፉ አይደለም። "ይህን ባደርግ ኖሮ ሁኔታው ይለወጥ ነበር" በማለት ሀሊናችንን እንዳይቆረቁረን በጣም ይረዳናል። ይሁን እንጂ አንዳንድ ጊዜ ከመስመር እንወጣለን። ያለን ጊዜ የተወሰነ ቢሆንም፥ ከምንችለው በላይ ጊዜያችንን እነርሱን ብቻ ለማስደሰት በምናደርገው ጥረት ላይ እናጠፋለን። አስቸጋሪ ሰዎች የሚፈጥሩብንን ችግር ለመፍታት የምናደርገው ጥረት ያለንን ጉልበት ሁሉ ሙጥጥ አድርጎ ስለሚወስድብን፥ ራሳችንን ከሁኔታው ለማላቀቅ አቅም ያንሰናል። ሁኔታችን ልብ ብሎ የሚመለከት ጓደኛ ወይም ወዳጅ ካለን፥ "...ምን ነካህ? የራስህን ሕይወት መምራት አቅቶህ ሌላው ሰው የሚመራህ ትመስላለህና ተጠንቀቅ!" በማለት ይመክረናል። እዚህ ላይ አመለካከታችን ጠባብ መሆኑና አለመሆኑን ራሳችንን መመርመር ይገባናል። ሁልጊዜ የምናስበው አስቸጋሪው ሰው ስለሚያደርስብን ችግር ወይም እንዴት አድርገን ደስ እንደምናሰኘው ብቻ ይሆን? በዚህ ምክንያት ሰፊውን ዓለም እንዳናይ አድርጎን ይሆን? የምናስበውና የምናወራው ሁሉ አስቸጋሪ ስለሆነብን ሰው ብቻ ይሆን? ከላይ ለጠየቅናቸው ጥያቄዎች የምንሰጠው መልስ "አዎን!" የሚል ከሆነ፥ ሕይወታችንን በተሳሳተ አቅጣጫ እየመራነው ስለሆነ፥ በአስተሳሰባችንና በአኗኗራችን "ቀኝ ኋላ" መዞር አለብን። ሕይወታችንን መልካምና ትርጉም ባለው ነገር ማዋል አለብን።

## 5. አስቸጋሪ የሆነብንን ሰው መበቀል? ወይስ በጎ ማድረግ...?

*"ክፉ አደረገብኝ"* የሚለውን ሰው መበቀል የሰው ሁሉ ተፈጥሮአዊ ባሕሪ እንደ ሆነ የታወቀ ነው። የዕለቱን ጋዜጣ ገለጥ አድርገን ስናይ፥ *"ከሥራ የተባረረው ሠራተኛ ከሥራ ያስወጣውን አለቃ ከቢሮ ድረስ መጥቶ ገደለው... ጥላው የሄደችውን ሚስቱን በሽጉጥ መትቶ ገደላት..."* የሚሉትን ዓይነት አርዕስተ ዜናዎችን ስናነብ እንግዳ አይሆንብንም። ከአስቸጋሪ ሰው ጋር መኖር የሰለቸውና የመረረው አንድ ሰው፥ *"ከዚህ በፊት '...ባሏን በሽጉጥ መትታ ገደለች ...ሚስቱን አንቆ ገደላት...' የሚለውን አሳዛኝ ታሪክ ስሰማ፥ 'ሰዎች ይህን ዓይነት ወንጀል ለምን ይፈጽማሉ?' ብዬ እጠይቅ ነበር... አሁን ግን ምክንያታቸው ይገባኛል..."* አለ። አስቸጋሪ የሆነ የሥራ አለቃ ያለው ሰው ለረጅም ጊዜ ውስጡ በደልና ቂም ያጠራቅምና መጨረሻው ደረጃ ላይ ሲደርስ የበቀል እርምጃ ለመውሰድ እንደሚከጅለው የታወቀ ነው። ይሁን እንጂ የሚወስደው የበቀል እርምጃ የሚጎዳው የሥራ አለቃውን ብቻ ሳይሆን የሚበቀለውን ሠራተኛ ውንም ጭምር ነው። ያንን ሰው በመግደሉ በስቅላት ይቀጣል ወይም የተቀረውን ዘመኑን ወህኒ ቤት ያሳልፋል። ከአስቸጋሪ ሰው ጋር በመኖር ብዙ የተሰቃየ ሰው፥ "አስቸጋሪ ሆነብኝ" የሚለውን ሰው ከላይ ባየነው ዓይነት ደረጃ ባይበቀለውም፥ በተለያየ ሁኔታ የበቀል እርምጃ ለመውሰድ ሊቃጣው እንደሚችል የታወቀ ነው። ሰው መራራነት በልቡ ሲያጠራቅም፥ መጨረሻ ላይ በቁጣ ገንፍሎ ከፍተኛ የሆነ እርምጃ ለመውሰድ እንደሚቃጣው አስቀድሞ ማወቅ ያዳግታል።

እንዳንቆጥር፥እንዲሁም በተግባርም ሆነ በእሳብ የመበቀል ስሜት በውስጣችን እንዳይፈጠር ማለት ነው። በእግዚአብሔር ጸጋ ይቅር የማለት አቋም እንይዛ ለን። ይህም ማለት ለበዳዩ እንጸልይለታለን፤እንዲሁም በዳዩ በደሉ ተሰምቶቅ ሲጸጸትና እርቅ ሲፈልግ ለመቀበል ልባችንን ክፍት እናደርጋለን። ይህን ዓይ ነት አቋም ሲኖረን፥ በዳዩ ተጸጽቶ ይቅርታ ለመጠየቅ ረጅም ጊዜ ቢወስድበት እንኳን፥ መራራነትና ቅሬታ በልባችን እንዳይፈጠር ይጠብቀናል።

ሁለተኛውን *"ትራንሳክሽናል ፎርጊቭነስ" (Transactional Forgiveness)* ብለው ጠርተውታል። ይህም ማለት በዳዩ በበደሉ ተጸጽቶ ይቅርታ ሲጠይቅ የሚሰጥ ይቅርታ ነው። *"ከቀን ሰባት ጊዜ ቢበድልህና በቀን ሰባት ጊዜም ወደ አንተ እየመጣ 'በበደሌ ተጸጽቼአለሁ ቢልህ ይቅር በለው"* ሲል፥ በበዳዩና በተበዳዩ መካከል የሚፈጸም መሆኑን ያሳያል (የሉቃ. 17፥4)። ተበዳዩ በዳዩን ይቅር ሲለው፥ *"(1) ስለ ሁኔታው አላስብም፥ (2) የተፈጸመውን ሁኔታ በማስታ ወስ በዳዩን መጉጃ አድርጌ አልጠቀምበትም፥ (3) ስለተፈጸመው በደል ለሌ ሎች አልናገርም፥ (4) ከዚህ በፊት የፈጸምክብኝ በደል በእኔና በአንተ መካከል ሆኖ ግንኙነታችንን እንዲያበላሽ አልፈቅድም"* የሚለውን ተስፋ መግባቱ ነው። በዳዩ ተጸጽቶ ይቅርታ ሳይጠይቅ፥ የመጀመሪያዎቹን ሦስት ተስፋዎችን ተበዳዩ የግድ መጠበቅ አለበት። አስቸጋሪ ሰው ይቅርታ መጠየቅ ከባድ ስለሚ ሆንበት፥ ይቅርታ ባይጠይቅም ከላይ ከገለጽናቸው አራት ተስፋዎቹ ውስጥ የመጀመሪያ ሦስቱን ልንፈጽም ግድ ነው። አራተኛውን ተስፋ መፈጸም የሚገ ባን ግን፥ አስቸጋሪው ሰው በበደሉ ተጸጽቶ፥ ይቅርታ ጠይቆ እውነተኛ የንስሀ ፍሬ ሲያሳይ ብቻ ነው። ይህም ማለት አስቸጋሪ ከሆነው ሰው ጋር የተቀራረበ ግንኙነት አይኑረን እንጂ፥ ይቅርታ ቢጠይቅም ባይጠይቅም ይቅር ማለት እን ዳለብን እናውቃለን።

## ፱

# ድንበር ማበጀትና ድንበር ማስከበር ይጠቅማል

ሁላችንም ሰውን ሁሉ ደስ ለማሰኘት እንዲሁም "ጥሩ ሰው" ለመባል እንፈ ልጋለን። በመሠረቱ ሰውን ደስ ለማሰኘትና ጥሩ ሰው ለመባል ጥረት ማድረግ መጥፎ ባይሆንም፥ ሁልጊዜ የጠበቅነውን ዓይነት ጥሩ ውጤት ግን ያስገኝል ናል ማለት አይደለም። ጥሩ ሰው ለመባል ስንል ብቻ የራሳችን ያልሆነውንና እንዲሁም ከአቅማችን በላይ የሆነውን ሸክም መሸከም፥ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ያመዝናል። ሌሎችን አስደስተን "ጥሩ ሰው" ብንባል፥ የራሳችንን የግል ሕይ ወት ግን ችላ ብንል ምን ይጠቅመናል? የሚያሳዝነው ጊዜና አቅም በማጣት እንደሚገባው መሥራት ባለመቻላችን፥ "እናስደስተዋለን" በማለት የለፋንለትን ሰው ከቁጥጥራችን ውጪ በሆነ ምክንያት ልናስቀይመው የምንችል መሆና ችን ነው። እንዲሁም የሌላውን ሰው ሸክም ስንሸከም፥ ሌላውን እናስደስታለን ብለን መውሰድ የማይገባንን ኃላፊነት ወስደን ቀንና ሌሊት ስንለፋ፥ የራሳች ንን ኃላፊነት መፈጸም አቅቶን መበሳጨታችንና ማዘናችን አይቀርም። በመሠ